# ምድብ አራት
# የመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት

**§ 20**
**መድረኩን ማዘጋጀት**
**(ማር 1÷1፤ ሉቃ 3÷1-2)**

[ማር 1:][1]የእግዚአብሔር ልጅ[u] የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መጀመሪያ::

*[u]1 በአንዳንድ ቅጆች «የእግዚአብሔር ልጅ» የሚለው ሐረግ የለም::*

ከሌሎቹ ወንጌል ጸሐፊዎች በተለየ ሁኔታ ማርቆስ ለወንጌሉ መግቢያ አልጻፈም:: ሆኖም በመግቢያው ላይ የተጠቀመባቸው ቃላት እንደ መለከት ድምፅ ትኩረታችንን መሳብ የሚችሉ ናቸው:: በማርቆስ የመጀመሪያ አንባቢዎች ላይ የፈጠረው ስሜት የሚከተለውን ይመስላል:- «ስሙ፣ ስለ ኢየሱስ የምሥራች ልነግራችሁ ነው!» ሆኖም ይህ የምሥራች የእህል ዋጋ ቀንሷል ወይም ነገ የአየሩ ጠባይ መልካም ይሆናል እንደ ማለት ያለ አይደለም:: በሰብዓ ሊቃናት ትርጉም የምሥራች የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የሚውለው እግዚአብሔር የእስራኤልን ጠላቶች ማሸነፉን ለማብሰር ነበር (1ነገ 1÷42፤ 1ሳሙ 4÷17፤ 2ሳሙ 18÷26):: ስለዚህም የእግዚአብሔርን ማዳን በተመለከተ መለኮታዊ ፋይዳ ያለው አገላለጽ ሆኗል:: (ኢሳ 40÷9፤ 52÷7፤ 61÷1፤ መዝ 96÷2-10 ጋር ያነ):: እንግዲህ የዮሐንስ አንባቢዎች የሚኖሩቸው ግምት እግዚአብሔር በእንቅስቃሴ ላይ ነው፣ በመሆኑም የዳዊትን መንግሥት እንደገና ያቋቁማል የሚል ሊሆን እንደሚችል ይጠበቃል::[1]

ማርቆስ ወደ ዋናው ጉዳይ ለመግባት እየተጣደፈ ነው:: ወዲያውኑ ለኢየሱስ አገልግሎት መድረክ የሚያዘጋጁ ትናንሽ ሥዕላዊ መግለጫዎችን በማቅረብ እንደሚከተለው ይጀምራል፤ መግቢያው ከብሉይ ኪዳን አንድ ጥቅስ፣ የዮሐንስን ስብከትና የኢየሱስን ጥምቀትና በምድረ በዳ ያሳለፈውን ፈተና ያካተተ ነው::

[1] R. Poon, "The Begining of the Gospel: The Introductory Statement of Mark's Gospel (1:2-3)," *Jian Dao* 13 (1999): 103-118.



**ሉቃ 3÷1-2**

[1]ጢባርዮስ ቄሣር በነገሠ በዐሥራ አምስተኛው ዓመት፣ ይኸውም ጳንጥዮስ ጲላጦስ የይሁዳ ገዥ፣ ሄሮድስ የገሊላ አራተኛው ክፍል ገዥ፣ ወንድሙ ፊልጶስ የኢጡርያስና የጥራኮኒደስ የአራተኛው ክፍል ገዢ፣ ሊሳንዮስም የሳቢሳኒስ አራተኛው ክፍል ገዥ፣ በነበሩበት ጊዜ፣ [2]ሐናና ቀያፋም ሊቃነ ካህናት ሳሉ፣ የእግዚአብሔር ቃል ወደ ዘካርያስ ልጅ ወደ ዮሐንስ በምድረ በዳ መጣ::

ሉቃስ፣ «ከዕለታት አንድ ቀን» ብሎ አልጻፈም:: ትረካውን በታሪክ ከሚታወቁ መሪዎች ጋር በማያያዝ ይጀምራል (ቁ 1-2):: እዚህ ላይ ደግሞ በሌላ ስፍራ ካደረገው በተሻለ ሁኔታ አቅርቦታል:: በዚህ የትውልድ ሐረግ ዘገባ ላይ ከሰባት ያላነሱ መሪዎችን ስም ይዘረዝራል::

1. ጢባርዮስ ቄሣር - ከእርሱ በፊት የነበረው አውግስጦስ የሞተው ነሐሴ 19/14 ዓ.ም. ነበር:: ጢባርዮስ ሥልጣን የያዘው ወዲያውኑ ከሆነ በተለመደው የሮማውያን አቆጣጠር መሠረት ታሪኩ[2] የተፈጸመው በ29 ዓ.ም ነበር ማለት ነው::
2. ሄሮድስ - ሄሮድ አንቲጳስ የታላቁ ሄሮድስ ልጅ ነው ከ4 ዓ.ቅ.ክ እስከ 39 ዓ.ም. ገሊላንና ከዮርዳኖስ ማዶ ያለውን አገር ይገዛ ነበር (ሉቃ 3÷19-20፤፣ 13÷31፤ 23÷7 ጋር ያነ)::
3. ፊልጶስ - እንደ ሄሮድስ አንቲጳስ ሁሉ እርሱም የታላቁ ሄሮድስ ልጅ ነበር:: ከ4 ዓ.ቅ.ክ እስከ 33/34 ዓ.ም. ድረስ ከፓለስቲና ሰሜን ምሥራቅ የነበሩትን አጡርያስንና ጥራኮኒደስን ይገዛ ነበር:: የአራተኛው ክፍል ገዥ ማለት በዚያ ዘመን ለአራት ተከፍሎ ከነበረው ፓለስቲና አንደኛውን ክፍል የሚገዛ ማለት ነው::
4. ሊሳንዮስ - ይህ ነው የሚባል የተዘገበ የታሪክ የለውም::

[2] B. Messner, "'In the Fifteenth Year' Reconsidered: A Study of Luke 3:1," *SCJ* 1/2 (Fall 1998): 201-211.

5. ጲላጦስ - ይህ ሰው ከ26 - 36 ዓ.ም. ድረስ አገረ ገዥ የነበረው ጳንጥዮስ ጲላጦስ ነው::
6. ሐና - ከ7-15 ዓ.ም. ድረስ የሊቀ ካህንነትን ሥልጣን ይዞ ነበር በአይሁድ ሕግ መሠረት ሐና በዘመኑ ሁሉ ሊቀ ካህን ሆኖ የቆየ ይመስላል (ዮሐ 11÷49፤ 18÷13፤ ሐሥ 4÷6 ጋር ያነ):: ኃይለኛና ሰዎችን ማግባባት የሚችል ስለ ነበር አምስት ልጆቹንና (Josephus, *Ant.* 20.9.1) የልጁ ባል የነበረውን ቀያፋን ከእርሱ በኋላ ተክቶአቸው ነበር:: ምንም እንኳ ልጆቹ ማዕረጉን በያዘበት ወቅት እንኳን ዋናው አስተዳዳሪ እርሱ ነበር ::
7. ቀያፋ በሮም መንግስት ሊቀ ካህን ተደርጐ በይፋ የተሾመ ሰው ነበር (18-36 ዓ.ም):: ከሐና በኋላ ሥልጣን የያዘ አራተኛው ሰው ነበር:: ይሁን እንጂ ሕዝቡ አመራር ለማግኘት የሚጠብቁት ከሐና ነበር

**§ 21**
**የመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት**
**(ማቴ 3÷1-6፤ ሉቃ 3÷3-6) ከዮሐ 1÷19-23 ጋር ያነ)**

[ማቴ 3፡፩1በዚያን ወራት መጥምቁ ዮሐንስ በይሁዳ ምድረ በዳ እየሰበከ መጣ::

[ሉቃ 3፡፩3እርሱም ለኃጢአት ስርየት የሚሆን የንስሐን ጥምቀት እየሰበከ በዩርዳኖስ ወንዝ አካባቢ ወዳሉት ስፍራዎች ሁሉ መጣ::

[ማቴ 3:]2መንግስተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሀ ግቡ የሚል ነበር ስብከቱም

መጥምቁ ዮሐንስ ሲመጣ መሲሐዊ ትንቢቶች ቁልፍ የተዘጋውን እንደሚከፍት የእግዚአብሔር ምስጢር ማለትም የኢየሱስ ክርስቶስ የምሥራች ወንጌል ይተረተር ጀመር:: መሲሑን ማስተዋወቅ የዮሐንስ ሥራ ነበር:: ይህንም ያደረገው በቢታንያ አቅራቢያ በዮርዳኖስ



ወንዝ ዳርቻ ከበታ ቦታ እየተዘዋወረ በማገልገል ነበር (ዮሐ 1÷28፤ 10÷40) በመላው ፓለስቲና የነበሩ ሰዎች እየመጡ ይሰሙት ነበር::

መልእክቱ «የእግዚአብሔር መንግሥት እየመጣች ነው» የሚል በጣም ቀላል ሆኖም ጥልቀት ያለው መልእክት ነበር:: ለሚመጣው መንግሥት በግል ለመዘጋጀት ንስሐ ማድረግና መጠመቅ ነበረባቸው:: የዮሐንስ ጥምቀት የክርስቲያን ጥምቀት ግንባር ቀደም ነበር:: ሁለቱም ለኃጢአት ስርየት የሚሆኑ የንስሐ ጥምቀቶች ነበሩ (ሐሥ 2÷38 ጋር ያነ):: የዮሐንስ ጥምቀት እንደ ብሉይ ኪዳን መስዋዕቶች ሁሉ ከመስቀሉ በፊት እንኳ ለኃጢአት ስርየት የሚሆን ይቅርታን ያስገኙ እንደ ነበር ቅዱሳት መጻሕፍት ያስተምራሉ:: እነርሱም እንደ እኛ በእምነት ይጸድቃሉ (ሮሜ 4÷1-25፤ ገላ 3÷1 ጋር ያነ):: ልዩነቱ እኛ ወደ ኋላ ወደ መስቀሉ ዞረን ስናይ እነርሱ ግን መስቀሉን ወደ ፊት አሻግረው ማየታቸው ነበር:: ሆኖም ሁሉም በእምነት ማለትም በእግዚአብሔር ተስፋ ቃል በመታመን ድነዋል::


አንዳንዶች የዮሐንስ ጥምቀት ሰዎች ወደ ይሁዲነት ሲገቡ ይወስድት ከነበረው ጥምቀት ከኤሴናውያን ለመንጻት ከሚፈጽመት ስርዓት እንዲያውም የዞሮአስተርን እምነት የሚቀበሉ ሰዎች ከሚፈጽሙት ሥርዓት የተወሰደ እንደ ነበር ይናገራሉ:: ምንም እንኳ አንዳንድ ተመሳሳይ ነገሮች ቢኖሩም ልዩነቶቹ ግን ይበዛሉ (1) እነዚያ ራሳቸውን ያጠምቁ ነበር እንጂ ሌላ አጥማቂ አልነበራቸውም (2) እነዚያ ጥምቀቶች የመንጻትን ሥርዓት ለመፈጸም የሚደረጉ ነበሩ (በብሉይ ኪዳን እንደሚደረገው ዓይነት ዘሌ 14÷ 9፤ ዘኁ 19÷19፤ 8÷7):: የዮሐንስ ጥምቀት ግን ያተኰረው ንስሐ ላይ ነበር:: ዮሐንስ ውስጣዊው ሰው ላይ ሲያተኩር እነዚያ ግን ውጫዊው ሰው ላይ ነበር ያተኰሩት (3) የዮሐንስ ጥምቀት ራሳቸውን እንደ ንፁሕ ይቆጥሩ ለነበሩ አይሁድ እንጂ ለአዲስ ጀማሪዎች ወይም አንድ የሃይማኖት ሥርዓት ለሚፈጽሙ የሚደረግ

አልነበረም (4) የዮሐንስ ጥምቀት ሃይማኖታዊ ሥርዓት ከማሟላት ይልቅ የኃጢአት ስርየት ለማስገኘት የሚደረግ ነበር:: ጆሴፈስ የዮሐንስን ጥምቀት በተሰሳሳተ መንገድ በመረዳት በዘመኑ ይደረጉ ወደ ነበሩት የጥምቀት ስርዓቶች ደረጃ ዝቅ አድርጎታል::

> መልካም ሰው ነበር፣ በመካከላቸው ፍቅር እንዲኖር እርስ በርሳቸው ፍትሕን እንዲለማመዱ እግዚአብሔርን በተመለከተም መንፈሳዊነት እንዲኖራቸውና እንደዚያም እያደረጉ ከዚያ በኋላ ለመጠመቅ እንዲመጡ አይሁድን አዘዘ:: ይህም ጥምቀት የሚፈጸሙት ከሆነ በእግዚአብሔር ተቀባይነት ያለው ቢሆንም ኃጢአትን ለማስተሰረይ ግን አይሆንም:: ነፍስ በጽድቅ አማካይነት ፈጽማ የነጻች ከሆነ ጥምቀት ለሰውነት መንጻት የሚውል ነው (*Ant.* 18. 117)::

እርግጥ ነው በቅርጽ ይመሳሰላሉ ትርጉማቸው ግን በፍጹም የተለየ ነው:: የዮሐንስ ጥምቀት በአይሁድ ሥርዓትና በክርስቲያናዊ ምስጢራት መካከል እንደ ድልድይ ያገለግላል::

ሉቃ 3፥4-6
ማር 1፥2-3



[ሉቃ 3:]4ነቢዩ ኢሳያስ በመጽሐፉ እንዲህ ሲል በጻፈው ቃል መሠረት ነበር

[ማር 1:]2«እነሆ መንገድህን የሚያዘጋጅ[u] መልክተኛ ዬን በፊትህ እልካለሁ

3የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አስተካክሉ[n] እያለ በበረሃ የሚጮኽ ድምፅ

[ሉቃ 3:]5ሸለቆው ሁሉ ይሞላል ተራራውና ኮረብታው ሁሉ ዝቅ ይላል ጠማማው መንገድ ቀና ሻካራውም ጉዳና ትክክል ይሆናል

6የሰውም ዘር ሁሉ የእግዚአብሔርን ማዳን[ጠ] ያያል

*[u][ማር 1:]2 ሚል 3፡1 [n]3 ኢሳ 40፡3 [ጠ][ሉቃ 3:]6 ኢሳ 40፡3-5*



ሦስቱም ተወራራሽ ወንጌሎች ከኢሳይያስ 40፥3 ጠቅሰዋል:: ሉቃስ የኢሳይያስ 40፥53ን መጀመሪያ ክፍል በመተው በቁ 4-5 ያለውን ጨምሮአል:: ማርቆስ ስለ ኤልያስ መምጣት ትንቢት ከሚናገረው ከሚልክያስ 3፥1 (እና ዘፀ 23፥20) በመጥቀስ የኢሳይያስን ቃል በመግቢያነት ይጠቅማል:: ከመሲሑ በፊት ኤልያስ ተመልሶ ይመጣል ብለው አይሁድ ይጠብቁ ነበር:: ቀደሞውኑም ኤልያስ በእርግጥ አልሞተም (2ነገ 2፥11):: ሚልክያስ 4፥5 ለመሲሑ መምጣት ዝግጅት ለማድረግ እንደሚመለስ ተንብየዋል:: ኢየሱስም ይህ ቃል ዮሐንስን እንደሚመለከት ተናግሮአል (ማቴ 11፥14)::

ይህ ዘይቤያዊ አነጋገር አንድ ንጉሥ ወይም ሌላ ታላቅ ሰው ሲመጣ የሚደረግ ዝግጅትን የሚገልጽ ነው:: አንድ ንጉሥ በዚያ በኩል እንደሚመጣ ከታወቀ የግንባታ ቡድን ቀደም ብሎ ይሄድና መንገዱን ያዘጋጅ ነበር:: የሚያደናቅፍ ድንጋዮችን ያነሳሉ፣ ጠማማውን ያስተካክላሉ፣ ጉድጓዶችን ይደፍናሉ:: ዮሐንስ በስብከቱ አማካይነት ለኢየሱስ ይህንን አድርጓል:: ኢየሱስን እንዲከተሉ የሰዎችን ልብና አእምሮ የሚያዘጋጁ ለኃጢአት ንስሐ የሚሆን ጥምቀትንና ብዙ መሲሓዊ ጽንሰ ሐሳቦችን አስተዋውቋል:: ተወራራሽ የሆኑት ሦስቱ ወንጌሎች ይህን ጥቅስ የወሰዱት ከዕብራይስጡ ቅጂ አንድ ሁለት ጥቃቅን ልዩነቶች ካሉት ከሰብዓ ሊቃናት ነበር::

በመጀመሪያ፣ «መንገዱን አዘጋጁ» የሚለውን በዕብራይስጥ ቃል በቃል «አምላካችን» ነው የሚለው:: ማቴዎስ 3፥3 ላይ «ጌታ» የሚለውም በዕብራይስጥ «ያሆዋ» የሚለው ትርጉም ነው:: በማጠቃለያው የምናገኘው ሁለቱም ለውጦች ኢየሱስ ያሆዋ አምላክ እንደሆነ ማመልከታቸውን ነው::

ማቴ 3፥4-6

4የዮሐንስ ልብስ የግመል ጠጉር ሲሆን፣ ወገቡንም በጠፍር
ይታጠቅ ነበር። ምግቡም አንበጣና የበረሃ ማር ነበር።
5ከኢየሩሳሌም፣ ከመላው ይሁዳና በዮርዳኖስ ዙሪያ ካለው አገር ሁሉ
ሰዎች ወደ ዮሐንስ ይጐርፉ፣ 6ኀጢአታቸውንም እየተናዘዙ
በዮርዳኖስ ወንዝ በእርሱ ይጠመቁ ነበር።

ማቴዎስና ማርቆስ ስለ ዮሐንስ ስዕላዊ ገለጻ አቅረበዋል። ግር የሚያሰኝ ገጽታ ያለው ባህታዊ ዓይነት ሰው ነበር። የግመል ጠጉር ይለብስ ነበር፤ በወገቡም የቆዳ ቀበቶ ይታጠቅ ነበር። ይመገበው የነበረውም አንበጣና በበረሃ የሚገኝ ማር እጅግም ተቀባይነት የሌለው ነበር። ይሁን እንጂ በዘመኑ ለነበሩ ሰዎች ሳይሆን ለእኛ እንግዳና ያልተለመደ ዓይነት ሰው ሳይሆን አይቀርም። ሌሎች ነቢያትም እንደሀ ያለ ልብስ ይለብሱ ነበር (2ነገ 1፥8 [ሚል 4፥5 ጋር ያነ]፤ ዘካ 13፥4)። አንበጦችም እንዲበሉ ተፈቀዷል (ዘሌ 11፥22)፣ ዛሬም ቢሆን በመካከለኛው ና በሩቅ ምሥራቅ ያሉ ድሆች ይበሏቸዋል። ብዙ ጊዜ ደግሞ ወተትና የበረሃ ማር እንደ ማጣፈጫ ይጨመሩባቸዋል። የዮሐንስ አቀራረብ ኋላ ቀርና ጉልዳፋ ሊሆን ይችላል፤ ጨርሶ የማይታሰብ ነበር ማለት ግን አልነበረም።

§ 22
የመጥምቁ ዮሐንስ ስብከት
(ማቴ 3፥7-10፤
ሉቃ 3፥7-14)

[ሉቃ 3፡]7ዮሐንስም በእርሱ እጅ ሊጠመቁ
የወጡትን ሰዎች እንዲህ ይላቸው ነበር፤ «እናንተ
የእፉኝት ልጆች፣ ከሚመጣው ቁጣ እንድትሸሹ ማን
መከራችሁ? 8እንግዲህ ለንስሐ የሚገባ ፍሬ አፍሩ፤
ደግሞም በልባችሁ፣ አብርሃም አባታችን አለን ማለትን፣
አትጀምሩ፤ እግዚአብሔር ከእነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም
ልጆች ማስነሣት እንደሚችል እነግራችኋለሁና 9አሁን እንኳ
ምሳር በዛፎች ሥር ተቀምጦአል፤ መልካም ፍሬ
የማያፈራም ዛፍ ሁሉ ተቆርጦ ወደ እሳት ይጣላል።



የዮሐንስ ስብከት በተግባር የሚገለጽና ወደ ውስጥ የሚዘልቅ ነበር። ዮሐንስ በተለይ እየተናገረ የነበረው ወደ እርሱ ይመጡ ለነበሩት ጻሐፍትና ፈሪሳውያን እንደ ነበር ማቴዎስ (3፥7) ያመለክታል። አነጋገሩ የዚያን ያህል ኮስታራ የሆነበት ምክንያት ይህ ሊሆን ይችላል። በጣም ርቆ በመሄድ ኢየሱስ ፈሪሳውያንን አስመልክቶ የተጠቀመበትን ዘይቤያዊ አነጋገር ተጠቅሞ (ማቴ 23፥33) የእፉኝት ልጆች በማለት ጠርቷቸዋል። የዮሐንስ ድፍረት የብሉይ ኪዳን ነቢያት ዓይነት ነበር።

ሕዝቡ የመጡት በዮሐንስ ለመጠመቅ እንደነበረ እናውቃለን። ሆኖም ሰዱቃውያንና ፈሪሳውያን የመጡት በእርሱ ለመጠመቅ ነበርን? ማቴዎስ ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን «ወደሚያጠምቅበት ስፍራ *epi ton* ሲመጡ» በማለት ይገልጻል። ምናልባትም ይህ «ለመጠመቅ ይመጡ ነበር» የሚል ትርጉም ሊሰጥ ይችል ይሆናል። ይሁን እንጂ በማቴዎስ ወንጌል በሌሎች ቦታዎች *epi ton* የሚለው «አንድ ነገር ለማድረግ ማቀድ» የሚል ትርጉም የለውም። የግሪክ ቃል *epi ton* «ይህም በመሆኑ» የሚል ትርጉም ሊኖረው ይችላል (ከማቴ 15፥32፤ 22፥34 ጋር ያነ)። ስለሆነም ሊሆን የሚችለው ግንዛቤ ዮሐንስ ያጠምቅ ስለ ነበረ ፈሪሳውያን ወደ እርሱ መጡ የሚል ነው።

ምናልባትም፣ ወደ እርሱ የሄዱት የሚያጠምቀው በማን ሥልጣን እንደ ነበር ዮሐንስን ለመጠየቅ ነበር የሚል አቀራረብ ሊኖርው ይችላል (ዮሐ 1፥24-25)። አንዳንዶቹ ቅኖች ሊሆኑ ይችላሉ፤ ሆኖም አብዛኞቹ ፈሪሳውያንና ሰዶቃውያን ቅኖች መስለው የቀረቡት ከሕዝቡ የተነሣ ብቻ ነበር። ዮሐንስ ራሳቸውን ካለበጡበት ሥር ያለውን ተመልክቶ ወደ እርሱ እንዲመጡ ጠየቃቸው (ሉቃ 3፥7-9)። ስለዚህም ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ቢያንስ እጅግ ብዙዎቹ የዮሐንስን ጥምቀት ለመቀበል ፈቃደኞች አልሆኑም (ሉቃ 7፥30፤ ማቴ 21፥23-27)።

ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን በዮሐንስ ለመጠመቅ መምጣታቸው ትክክል ነበር፤ ግን የልባቸው ዝንባሌ የተሳሳተ እንደ ነበር ግልጽ ነበር። የሚያስፈልጋቸው ተገቢ ፍሬ የሚያፈራ ንስሐ ነበር። ቃል በቃል ከወሰድነው ንስሐ ማለት «የአስተሳሰብ ለውጥ ማድረግ» ማለት ነው። «አእምሮ» የሚለው የግሪኩ ቃል ጽንሰ ሐሳብ ሐሳብን ብቻ ሳይሆን ፈቃድንም ይጨምራል። ስለሆነም አእምሮ የአንድን ሰው ሐሳብና ጸባይ ይቆጣጠራል። ሥራ የሌለው እምነት የሞተ እንደሆነ ሁሉ የጸባይ ለውጥ የሌለው ንስሐም እንዲሁ ትርጉም የለሽ ነው። (ሐሥ 17-30-31፤ 26÷20 ጋር ያነ)። ይህ ማለት ግን ምንም ኀጢአት የሌለባችሁ መሆን አለባችሁ ያ ካልሆነ ግን በእርግጥ ንስሐ አልገባችሁም ማለት አይደለም። ዋናው ጉዳይ አንድ ሰው የደረሰበት የቅድስና ደረጃ ሳይሆን እየተከተለ ያለው አቅጣጫ ነው። ወደ እግዚአብሐር ባሕርይ እየመራን ነው ወይስ ከእርሱ እየራቅን ነው?

እነዚያ ወገኖች አይሁድነታቸው በእግዚአብሔር ዘንድ ስፍራ ሊያስጧቸው እንደሚችል እርግጠኞነት ተሰምቷቸዋል። ዮሐንስ ግን ከእውነተኛ ንስሐ ይልቅ በማንነት ቅርሳቸው ላይ ይበልጥ እንዳይታመኑ አስጠንቀቃቸው። እርግጥ ነው፤ የአብርሃም ዘሮች ናቸው። ይህ ግን የግድ የአብርሃም፤ «ልጆች» አያደርጋቸውም። በአይሁድ ትልቁ ልጅ የአባቱን ባሕሪይ የሚያንፀባርቅ እንዲሆን ይጠበቅ ነበር (ማቴ 23÷24-32 ጋር ያነ)። የፈሪሳውያን ሐሳብ የዘር መስመራቸውና ማንነታቸው በእግዚአብሔር ዘንድ የተለየ ስፍራ እንደሚያስጣቸው ነበር። «ወሳኙ ነገር ምን እንደምታውቅ ሳይሆን ማንን እንደምታውቅ ነው» የሚለው የድሮ አባባል ዓይነት ነው። ገና በአፋቸው ከመናገራቸው በፊት ዮሐንስ ይህን የተሳሳተ አስተሳሰባቸውን አስተካከለ። ከእግዚአብሔር እንጂ ከአባቶቻችን ጋር ካለን ግንኙነት የተነሣ አይደለም ጽድቅን ያገኘነው። እውነተኛ የአብርሃም ልጆች የሚሆኑት በእግዚአብሔር ተስፋ ቃል



የሚያምኑ ናቸው እንጂ በስጋ የተወለዱት አይደሉም (ሮሜ 9÷6-9፤ ገላ 6÷16) «ልጅ» ለሚለው የአረማይኩ ቃል «ባኒ» ('bna') ሲሆን «ድንጋዮች» ለሚለውም ቃል እንዲሁ «ባኒ» ('bnv') ነው። ዮሐንስ ይጠቀምበት ከነበረው ቋንቋና ይዘት ከነበረው አቋም አንጻር ሲታይ በጣም የሰላ ቅኔ ነው።

በቅርቡ ሊመጣ ካለው ፍርድ አንጻር ንስሐ የመግባትን አስፈላጊነት ይበልጥ አስቸኳይ ያደርገዋል። ዮሐንስ መጥረቢያ በዛፎች ስር እንደ ተቀመጠና እርምጃ ለመውሰድ ዝግጁ እንደሆነ ተናገረ።ተገቢ ፍሬ የማያፈራውን ማንኛውንም ዛፍ ይቆረጣል። በኋላም ኢየሱስ ይህንኑ የዮሐንስ ማስጠንቀቂያ ሲያስተጋባ እንመለከታለን (ሉቃ 6÷43-45፤ ዮሐ 15÷1-6) በተጨማሪም «ተቆርጦ» እና «ይጣላል» የሚሉት ግሦች ቶሎ ሊወሰድ ከታሰበው እርምጃ አንጻር የሚያመለክቱት የአሁኑን ጊዜ እንጂ የወደፊቱን አይደለም። በግለሰብ ደረጃ ወደፊት ፍርድ መኖሩ ብቻ ሳይሆን በመላው አይሁድ ሥርዓት ላይ አሁን የሚፈጸም ፍርድ የሚኖር ይመስላል።

ሉቃ 3÷10-14

10 ሕዝቡም፣ «ታዲያ ምን እናድርግ?» ብለው ጠየቁት፤
11 ዮሐንስም «ሁለት ልብስ ያለው ምንም ለሌለው ያካፍል ምግብ ያለውም እንዲሁ ያድርግ» ብሎ መለሰላቸው።
12 ቀረጥ ሰብሳቢዎችም ሊጠመቁ ወደ እርሱ መጥተው «መምህር ሆይ እኛስ ምን እናድርግ?» አሉት።
13 እርሱም «ከታዘዛችሁት በላይ ቀረጥ አትሰብስቡ» አላቸው።
14 ወታደሮች ደግሞ «እኛስ ምን እናድርግ?» ብለው ጠየቁት
እርሱም «የማንንም ገንዘብ በግፍ አትንጠቁ ሰውንም በሐሰት አትክሰሱ ደመወዛችሁ ይብቃችሁ» አላቸው።

ታዲያ ንስሐ ለመግባት ምን ማድረግ አለብን? ይህንኑ ተመሳሳይ ጥያቄ ለመጠየቅ ሦስት ቡድን ሰዎች ወደ ዮሐንስ መጥተው

ነበር (ሉቃ 3÷10-14):- እነርሱም የአይሁድ ኅብረተሰብ፣ ቀረጥ ሰብሳቢዎችና ወታደሮች ናቸው:: ይህ ሁኔታ በሐዋርያት ሥራ 2÷26-37 ካለው ጋር ተመሳሳይ ነው::

በመጀመሪያ ዮሐንስ መልስ የሰጠው ለአይሁድ ኅብረተሰብ ነበር:: እዚህ ላይ «ልብስ» የሚለው መጎናጸፊያ ወይም ከካባ በታች የሚለበስ ነበር:: እያንዳዱ ሰው አንድ ይህን ዓይነት ልብስ ሊኖረው ይገባል ሆኖም ትርፍ ልብስ ባይኖረውም ምንም ማለት አይደለም:: ስለዚህም ከሚያስፈልገው በላይ ካለን ከሚፈለገው በታች ላላቸው ማካፈል ይኖርብናል:: ዮሐንስ እየተናገረ ያለው ዘወትር መኖር ስለለበት ሊጋስነት እንጂ በኩምራን እንደ ነበረው ስላለው ማኅ በረሰብ አይደለም:: ምግብና ልበስ መሰረታዊ ፍላጎቶች ናቸው:: እኛን የመሳሰሉ ሰዎች ሕይወት የሚያስፈሊጋቸውን መሰረታዊ ፍላጐቶች ሲያጡ እያየን ችላ የምንል ከሆነ እንዴት የእግዚአብሔር ወዳጆች መሆን እንችላለን? (2ቆሮ 8÷13-15፤ ያዕ 2÷15-17፤ 1ዮሐ 3÷17)::

ቀጥሎ ዮሐንስ ምላሽ የሰጠው ለቀረጥ ሰብሰቢዎች ነበር:: እንደ ሴተኛ አዳሪዎችና ነፍሰ ገዳዮች ሁሉ በእስራኤል በጣም የሚጠሉት እነዚህ ሰዎች ነበሩ:: እምነታቸውን የካዱ ሰዎች እንደሆኑ ይታሰብ ነበር:: ግሪኮች እንኳን «ቀራጭ» የሚለውን ቃል «ዘራፊ» የሚለው ቃል አቻ አድርገው ነበር የሚያስቡት (ማክጋርቪ፣ ገጽ 76):: በሮማውያን ቀረጥ አሰባሰብ ሥርዓት አንድ አውራጃ በጨረታ ከፍተኛ ዋጋ ለሚያቀርብ በጨረታ ይሸጥ ነበር:: ዋና ቀረጥ ሰብሳቢዎች ዘኬዎስን የመሳሰሉ ሰዎች ነበሩ (ሉቃ 19÷2):: ከአንድ የተወሰነ አካባቢ የተወሰነ መጠን ገቢ በቀረጥ መልክ መሰብሰብ እንደሚችሉ ቃል ይገባሉ:: ከዚያም በኋላ ከየግለ ሰቡ ቀረጥ የመሰብሰቡን ሥራ የሚሰሩላቸውን ሰዎች ይቀጥራሉ:: ዋና ቀረጥ ሰብሳቢዎቹ ለሮ የሚሆናቸውን የሚያገኙት ወደ ሮም መላክ ከሚገባቸው በላይ ገንዘብ በመሰብሰብ ነበር:: ብዙ በሰበሰቡ መጠን ብዙ ያተርፋሉ:: ከውሉታው በላይ የገባው ሁሉ ለእነርሱ ትርፍ ነበር:: በተመሳሳይ መልኩ ተቀጣሪ ቀረጥ ሰብሳቢዎችም ዋናው ቀረጥ ሰብሳቢ ከሚጠይቀው በላይ በመሰብሰብ ለኑሮ የሚሆናቸውን ገንዘብ ያገኙ ነበር:: ስለዚህም ብዙ ባጭበረበሩ መጠን ብዙ ይበለጥጋሉ ማለት ነው:: ከዚህም በተጨማሪ ሥራቸው ብዙ ጊዜ ከሥነ ሥርዓታዊ ንፅሕና አንጻር ንፁሕ እንዳልሆኑ ያስቆጥራቸው ነበር:: በጣም የተጠሉ ብቻ ሳይሆኑ ከማኅበረሰቡም የሚገለሉ ነበሩ::

ዮሐንስ ማኅበራዊ ተሐድሶን ወይም ማመጽን አስመልክቶ ምንም ባለመናገሩ ትዝቡ በመጠኑም ቢሆን ቅር ሳይላቸው አልቀረም:: ንስሐ ፍትሕን ብቻ ይጠይቃል:: ሌላው ቀርቶ ቀረጥ ሰብሳቢዎች እንኳ ለኑሮ የሚያስፈልጋቸውን ማግኘት ይኖርባቸዋል ሆኖም ከሚገባ በላይ በማስከፈል መሆን የለበትም::

በመጨረሻ ምላሽ ለወታደሮች (ቃል በቃል «ለሌላው በመታዘዝ የሚኖሩ») ሰዎችን መዝረፍ እንደማይኖርባቸው ነግሯቸዋል:: ምናልባትም እነዚህ ቀረጥ ለመሰብሰብ የሚረዱ የመቅደስ ጠባቂ ሚሊሻዎች ወይም በፔርያ በሄሮድስ አንቲጳስ ሥር ያገለግሉ የነበሩ ሠራዊት ሊሆኑ ይችላሉ:: ወታደሮቹ በመደበኛ ደረጃ አይሁድ ይሆናሉ:: ሆኖም ከእነርሱ አንዳንዶቹ የተጠሉት ሮማውያን ሊሆኑ የሚችሉበት ሁኔታ ይኖራል:: ከነበራቸው ሥልጣን የተነሳ ሕግ አስፈጻሚዎች ሰዎችን በማስፈራራት ገንዘብ ሊበዘብዙ ይችላሉ ደግሞ በዝብዘዋል:: ዮሐንስ ንግግሩን ሲያጠቃልል «ደመወዛችሁ ይበቃችሁ» ነበር ያላቸው:: የአንድ ሮማዊ ወታደር ዓመታዊ ደመወዝ ሁለት መቶ ሃያ አምስት ዲናር ነበር:: አንድ ዲናር አንድ የቀን ሠራተኛ የሚያገኘው ክፍያ ነበር:: ለወታደሮቹ ምግብ ልብስና ትጥቅ የሚቀርብበት ዋጋ ከደመወዛቸው ይቀነስ ነበር:: ምንም እንኳ ጡረታ ሲወጡ የሮም ዜግነት ቢሰጣቸውም የሚከፈላቸው ዝቅተኛ ነበር:: በደመወዛቸው ደስተኞች እንዳልነበሩ

መረዳት ይቻላል :: ሆኖም ዮሐንስ እንደ ተናገረው ይህ ሌሎችን ለመዝረፍ ምክንያት ሊሆናቸው አይገባም::

ማሳሰቢያ:- ለሌሎች በተለይም በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ላሉት ርኅራኄ የምናደርገው መልካምና ሕግ አክባሪ ክርስቲያኖች ለመሆን ብለን ሳይሆን የእግዚአብሔር መንግሥት በመቅረቧ ምክንያት መሆን እንዳለበት ተመክረናል:: እግዚአብሔር ሊገለጥ ነው:: ስለሆነም እርሱ በሚገለጥበት ጊዜ ሕዝቡ በፈጸሙት ዓመፃዎች ሁሉ ላይ ከሚመጣው የማይቀር ፍርድ እንድናመልጥ ተግባራችንን ብናጸዳ የተሻለ ይሆናል::

ኢየሱስንና ዮሐንስን ማወዳደርና ማነጻጸር እንደ ቀጠለ ነው:: እንደ መሲሕ በመቁጠር ሕዝቡ ዓይናቸውን ዮሐንስ ላይ ቢያሳርፉም እርሱ ግን በአግባቡ ወደ ሌላው ያመለክት ነበር:: እርሱ መንገድ የሚያስተካክል ብቻ ነበር:: መጥመቁ አስገራሚ የነበረ ቢሆንም እንኳ መሲሑ የሚፈጽመው ጥምቀት ደግሞ የበለጠ ብርቱ ሊሆን ነው::

**§ 23**
**በመንፈስና በእሳት መጠመቅ**
**(ማቴ 3÷11-12**
**ማር 1÷7- 8**
**ሉቃ 3÷15-18)**

[ሉቃ 3:]15ሕዝቡ በጉጉት እየተጠባበቁ ሳሉ እርሱ
ክርስቶስ ይሆንን እያሉ[u] ሁሉም በልባቸው ስለ ዮሐንስ
ያስላስሉ ነበር:: 16ዮሐንስ ለሁሉም እንዲህ ሲል
መለሰላቸው እኔ በውሃ አጠምቃችኋለሁ ነገር ግን ከእኔ
የሚበረታ ይመጣል እኔም የእርሱን የጫማ ማሰሪያ
መፍታት የሚገባኝ አይደለሁም፤ እርሱ በመንፈስ ቅዱስና
በእሳት ያጠምቃችኋል 17ወድማውን ፈጽሞ ለማጥራትና
ስንዴውንም ወደ ጎተራው ለመከተት መንሹ በእጁ ነው፤
ገለባውን ግን በማይጠፋ እሳት ያቃጥለዋል:: 18ዮሐንስም
በብዙ ሌሎች የምክር ቃላት ሕዝቡን እያስጠነቀቀ
ወንጌልን ሰበከላቸው::

*[u]15 ወይም መሲሑ*



ሕዝቡ ዮሐንስ መሲሑ ይሆን ብለው መገረም ብቻ ሳይሆን መሲሑ እንዲሆንም ተመኝተዋል::[3] በዚያን ዘመን መሲን የመጠባበቁ ሁኔታ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር:: ከሮማውያን በታች መሆናቸውን በማሰብ ወታደራዊ ኃይል ተጠቅሞ ንጉሥ የሚሆን (መዝ 110) መሲሕ (መዝ 2፤ ኢሳ 9÷6-7) ይመጣል ብለው ተስፋ እያደረጉ ነበር:: የዮሐንስ ታዋቂ እየሆነ መምጣት ይህን መሳይ ንቅናቄ የማስከተል ብቃት ነበረው:: ነቢያት ያልነበሩባቸውን አራት መቶ ዓመታትን በማሰብ ነቢይ የሚሆን መሲሕ እየጠበቁ ነበር (ዘዳ 18÷15-18):: ዮሐንስ የሚጠብቁትን አሟልቶ ተገኝቷል:: የነበረውን ጉስቁላ ማኅበረሰብና የሄሮድሶችን ብልጥግና ከግምት ውስጥ በማስገባት ምድራዊ ብልጽግናን የሚያጐናጽፋቸው መሲሕ ተስፋ እያደረጉ ነበር (አሞጽ 9÷13-15):: የዮሐንስ ባህታዊ ዓይነት አኗኗር ለዚህ ብቁ አያደርገውም ሆኖም ከሦስት መመዘኛ ሁለት ማግኘት ቀላል አይደለም:: ዮሐንስ ክርስቶስ አልነበረም:: ሌላው ቀርቶ የመሲሑን የጫማ ማሰሪያ እንኳ ለመፍታት ብቁ እንደሆነ አልተሰማውም::

በሌላ አነጋገር ዮሐንስ በጣም ዝቅ ባለ አንድ ባሪያ በሚሰራው ስራ እንኳን ኢየሱስን ለማገልገል ብቁ ነኝ ብሎ አያስብም:: ዮሐንስ መሲሕ አለመሆኑን ያውቃል፤ የማጥመቅ ተግባሩ ይህን የሚያረጋግጥ ነበር:: እርሱ በውሃ ብቻ ያጠምቃል:: መሲሑ ግን በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃል ምንም እንኳ ይህኛው አንድን ነጠላ የማንፃት ጥምቀት ብቻ የሚወክል ቢመስልም (Guelich. pp. 27-28) እየተናገረ ያለው ስለ ሁለት የተለያዩ ጥምቀቶች ይመስላል:: መጀመሪያ የምንመለከተው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን ነው:: በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሁለት ጊዜ ተጠቅሶአል፤ ከበዓለ ሃምሳ ጋር በተያያዘ ሁኔታ (የሐዋ 1÷5፤ 2÷1-4) እና በቆርኔሌዎስ ቤተሰብ (ሐዋ 11÷15-17):: ሁለቱም

[3] ሉቃስ 3÷15 ላይ የተጠቀመበት ቃል ምኞታቸውን ወይም ፍላጎታቸውን ያመለክታል::

ወቅት ቤተ ክርስቲያን የተወለደችበት ጊዜ ነበር (የአይሁድ ቤተ ክርስቲያንና የአሕዛብ ቤተ ክርስቲያን)፡፡ በሁለቱም ጊዜያት እግዚአብሔር እነዚህን ሰዎች (ወገኖች) መቀበሉ ተረጋግጧል፡፡ በሁለቱም ወቅቶች ጉዳዩ በልሳን ከመናገር ጋር ተያይዞአል፡፡

የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በውሃ ውስጥ በመጥለቅ ከሚፈጸመው ክርስቲያናዊ ጥምቀት ጋር ተመሳሳይ ነውን? ተመሳሳይ ናቸው ካልን ጳውሎስ ያንኑ የመሰለ አገላለጽ ክርስትያናዊ ጥምቀትን ለማመልከት ተጠቅሟል (1ቆሮ 12÷13፤ ኤፌ 4÷5)፡፡ ዮሐንስ ኢየሱስ ሁሉንም በመንፈስ ቅዱስ እንደሚያጠምቅ የሚያመለክት ይመስላል (ማቴ 3÷11፤ ማር 1÷8፤ ሉቃ 3÷16፤ ዮሐ 1÷33)፡፡ ይሁን እንጂ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትና በክርስቲያናዊ ጥምቀት መካከል አንዳንድ ጉልህ ልዩነቶች አሉ፡- (1) የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በተጠቀሰባቸው በሁለቱም ቦታዎች (ሐሥ 2÷10) ከንስሐ ጋር ሳይሆን ከማስረጃነት ጋር የተያያዙ ነበሩ፡፡ (2) ከክርስቲያናዊ ጥምቀት[4] በፍጹም ከማይያያዘው በልሳን ከመናገር ስጦታ ጋር ተያይዞ ቀርቧል፡፡ (3) የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በተጠቀሰባቸው በሁለቱም ጊዜያት አንድም ጊዜ በውሃ ውስጥ መጥለቅ አልተጠቀሰም፡፡ ስለሆነም መደምደሚያችን በክርስቲያን ጥምቀት በኩል መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን መኖሩ በግልጽ ተስፋ ተገብቶልናል የሚል ነው (ሐሥ 2÷38፤ 19÷1-6፤ ዮሐ 3÷5፤ 7÷38-39፤ ቲቶ 3÷5 ጋር ያነ)፡፡ እዚህ ላይ ሁለቱም አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት (ከአይሁድና ከአሕዛብ የተውጣጡ) በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዳገኙ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የተለየ ዓይነት ማስረጃ ነበር (ሐሥ 2÷10፡፡ «የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት» በሐዋርያት ሥራ 2 እና 10 ላይ ያለውን ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ልምምድና በውሃ ውስጥ መጥለቅን የሚያቅፍ

[4] በየሐዋርያት ሥራ 19÷ 1-7 ካለው የምንመለከከተው በልሳን መናገር ከጥቃቅት ጋር ሳይሆን ከሐዋርያው ጳውሎስ እጆቹን መጫን ጋር የተያያዘ ነበር ፡፡



አጠቃላይ የአገላለጽ ዓይነት ሊሆን ይችላል፤ ሆኖም ሁለቱም በግልጽ የተለያዩ ናቸው፡፡

ኢየሱስ የሚፈጽመው ሁለተኛው ጥምቀት በእሳት ማጥመቅ ነው፡፡ በሐዋርያት ሥራ 2÷3 እንደምንመለከተው መንፈስ ቅዱስ በእሳት ምላሶች ተመስሎ ሐዋርያቱ ላይ በመውረዱ አንዳንዶች በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅና በእሳት መጠመቅ አንድ ነጠላ ልምምድ ናቸው የሚል አተረጓጎም ይዘዋል፡፡ ይሁን እንጂ አንድ አይደሉም፡፡ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ መልካም ነገር ነው፣ በእሳት መጠመቅ ግን መልካም ነገር አይደለም፡፡ በመሠረቱ ፍርድን ነው የሚያመለክተው፡፡ ዓውዱ ገበሬ አውድማውን ለማጥራትና ፋይዳ የሌለውን ገለባ ግን በማይጠፋ እሳት እንደሚያቃጥል ነው የሚያመለክተው፡፡ ክርስቲያኖች እንዲህ ያለውን ሁነት አይጠብቁም፡፡

እዚህ ላይ ሉቃስ እየነገረን ያለው (ቍ 18) የዮሐንስ ስብከት ጥቂት ክፍል ብቻ ነው፡፡ ዋናው የመልእክቱ አንኳር ሃሳብ ግን ከሚመጣው መንግሥትና ከሚመጣው ክርስቶስ ታላቅነት አንጻር ንስሐ አስፈላጊ መሆኑን ነው፡፡

# ምድብ አምስት
# ከዮሐንስ ወደ ኢየሱስ መሸጋገር

§ 24
የኢየሱስ ጥምቀት
(ማቴ 3÷13-17
ማር 1÷9-11
ሉቃ 3 ÷21-23ሀ)

የኢየሱስ መጠመቅ ሁለት ዓላማዎች ነበሩት:: የኢየሱስን የአደባባይ አገልግሎት መጀመር ማመልከቱ ነው:: መንፈስ ቅዱስ ወረደ ዮሐንስም ከመድረኩ ወደ ኋላ ዘወር አለ:: በዚህን ጊዜ የመድረኩን ማዕከላዊ ስፍራ የያዘው ኢየሱስ ነው:: ሁለተኛ የዮሐንስ ማጥመቅ የኢየሱስን ማንነት ይገልጣል:: ሉቃስ የኢየሱስን መጠመቅ ከትውልድ ሐረጉ ጋር አያይዞታል:: ከዮሐንስ ጋር ሲነጻጸር ኢየሱስ እጅግ የላቀ ነበር:: ከሕዝቡ አንጻር ሲታይ እርሱ ክርስቶስ ነው (ከሰማይ የተገለጡት ሦስቱ የተለያዩ ምልክቶች ኢየሱስ መሲሕ መሆኑን ያረጋግጣሉ):: ይህ በዘመኑ በነበሩ ሰዎች ዘንያ እርስ በርሱ የሚቃረን የሚመስል ጉዳይ ቢሆንም ከእግዚአብሔር አንጻር እርሱ የተወደደ የእግዚአብሔር ልጅና አገልጋይ ባሪያ ነበር::

ማቴ 3÷13-15

13በዚያን ጊዜ ኢየሱስ በዮሐንስ ለመጠመቅ
ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ 14ዮሐንስ ግን ይህማ
አይሆንም እኔ ባንተ መጠመቅ ሲያስፈልገኝ እንዴት አንተ
ወደ እኔ ትመጣለህ? ብሎ ተከላከለ::
15ኢየሱስም «ግድ የለም ፍቀድልኝ ይህን በማድረግ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም
ይገባናልና» አለው፣ ዮሐንስም በነገሩ ተስማማ::

ኢየሱስ የተጠመቀው የዮሐንስን ስብከት በመስማቱ አልነበርም:: ከናዝሬት እስከ ቢታንያ የሄደው በዮሐንስ ለመጠመቅ ነበር (ማቴ 3÷13):: ኢየሱስ የተጠመቀው ለምን ነበር? ምክንያቱን ኢየሱስ ራሱ



ተናግሮአል:- ማቴ 3÷13 «ይህን በማድረግ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናል» ይላል:: ይህ ያለ ጥርጥር ኢየሱስ ለእግዚአብሔር ዕቅድ መታዘዙን ያመለክታል:: ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ መገለጡንም በማያጠራጥር ሁኔታ ይመሰክራል (ዮሐ 1÷31-34 ጋር ያነ):: እና መከተል የሚገባንን ምሳሌ ከማስቀመጥ ጋር የተያያዘም አንድ ነገር ይኖረዋል:: ይሁን እንጂ ምንባቡ ከዚህ የበለጠም የሚያመለክተው ያለ ይመስላል:: ኢየሱስ የእስራኤል ሕዝብ በቀይ ባሕር ውስጥ ያደረገውን ጉዞ በድጋሚ የሚተገብር ይመስላል:: በጥምቀቱ አማካይነት አዲስ የእግዚአብሔር ኅብረተ ሰብ ተፈጠረ::[1]

ከዚህ ሁሉ ይበልጥ አስፈላጊ የሆነው ግን ለንስሐና ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈጸመውን ለሆነው ለዮሐንስን ጥምቀት ኢየሱስ ራሱን የመስጠቱ እውነት ነው:: ምንም ኃጢአት የሌለበት ንስሐ እንዲገባ ማስፈለጉ ግራ የሚያጋባ ነው:: የኢየሱስ የተጠመቀው ምሳሌ ሊተወልን በማሰብ እንጂ እርሱ መጠመቅ ስላስፈለገው አይደለም በማለት አንዳንዶች ጉዳዩን እንዳለ ለማድበስበስ ጥረት አድርገዋል:: ታዲያ ጉዳዩ የታይታ ነበር ማለት ነው?! ኢየሱስ በዮሐንስ የተጠመቀው ለንስሐ ካልሆነ ነገሩ ሁሉ እንደ ቀልድ ነበር:: ሆኖም ኢየሱስ ኃጢአት የሌለበት የእግዚአብሔር ልጅ ነው:: ይህን እርስ በርሱ የሚጋጭ የሚመስል ሁኔታ እንዴት ነው የምንረዳው? በምዕራባውያን አስተሳሰብ ንስሐ ምን ጊዜም ግላዊ ጉዳይ ነው:: እንደ ማኅበረ ሰብ ተሳስረው በሚኖሩበት በምሥራቅ ባሉ አገሮች ግን አንድ መሪ እንደ እውነቱ ለተከታዮቹ ጭምር ንስሐ መግባት ይችላል:: ዳንኤል፣ ነህምያ፣ ሙሴና ኤርምያስ ይህን አድርገዋል:: በግል ላልፈጸሙት ኃጢአት ጸልየዋል አልቅሰዋል፣ ጸመዋል፣ ንስሐ ገብተዋል:: እንደ እግዚአብሐር ሕዝብ መሪዎች ስለ

[1] C.G Dennison, "How is Jesus the Son of God? Luke's Baptism Narrative and Christology" *CTJ* 17 (After 1982): 6-25.

ሕዝቡ ኃጢአት ኃላፊነት ወስደዋል። እዚህ ላይ የሆነውም ይህንኑ ይመስላል። ኢየሱስ በስብዕናው እስራኤልን በመወከል፣ እንደ መሲሐዊ የእግዚአብሔር ሕዝብ ተወካይ መጥቷል። ይህም በመሆኑ ከእግዚአብሔር በኰበለለችው አገር ፋንታ ንስሐ የመግባት ኃላፊነትም መብትም ይኖረዋል። ይህ ትክክል ከሆነ ደግሞ የኢየሱስ መጠመቅ የአገልግሎቱን ጅማሬ ያበስራል ጽድቅን ሁሉ ይፈጽማል፣ የመስቀል ላይ ሞቱንም የወደፊት ዕጣ ፈንታ ያመለክታል።

[21]ሕዝቡ ሁሉ ከተጠመቀ በኋላ ኢየሱስም ተጠመቀ፤ እየጸለየም ሳለ (ከውሃ በሚወጣበት ጊዜ -ማር) ሰማይ ተከፈተ [22]መንፈስ ቅዱስም በአካላዊ ቅርጽ እንደ ርግብ በእርሱ ላይ ወረደ፣ ከሰማይም «የምወድህ ልጄ አንተ ነህ በአንተ ደስ ይለኛል» የሚል ድምፅ መጣ [23]ኢየሱስ አገልግሎቱን ሲጀምር ዕድሜው ሠላሳ ዓመት ያህል ነበር።

ሉቃ 3÷21-23 ከ ማር 1÷10፤ ማቴ 3÷16 ጋር

የኢየሱስ ጸሎት ብርቱ ነበር። በተለይም ደግሞ በሉቃስ ወንጌል ከፍተኛ ፋይዳ ካላቸው ነገሮች በፊት ይጸልይ እንደነበር ተገልጾአል። ለምሳሌ ዐሥራ ሁለቱን ደቀመዛሙርት ከመጥራቱ በፊት ሌሊቱን በሙሉ ሲጸልይ አድሮ ነበር (ሉቃ 6÷12)። ስለ ማንነቱ ከመግለጡ በፊት ሲጸልይ ነበር (ሉቃ 9÷18) ኢየሱስ በተራራው ላይ እየጸለየ እያለ ነበር ፊቱ የተለወጠው (ሉቃ 9÷29)። ከመያዙና ከመሰቀሉ በፊት በጌቴሴማኒ መሬት ላይ ተደፍቶ ሲጸልይ እናገኘዋለን (ሉቃ 22÷41-44)። የኢየሱስ ኃይል ምንጭ ጸሎት ነበር። ስለዚህም ኢየሱስ እንደ ጸለየ (ሉቃ 3÷21) ወዲያውኑ ሰማያት ቢከፈቱ (ማርቆስ እንዳለው) ከመጠን በላይ ልንደነቅ አይገባንም። ይህ የመጀመሪያው ምልክት ነበር።

ይህ የአምላካዊ ራእይ አምሳያ ነበር (ሕዝ 1÷1፤ ሐሥ 7÷56፤



10÷11)። ማርቆስ የተጠቀመው (ስኪዞሜኖስ [*Schizomenous*, 1:10]) ሲሆን ትርጉሙም «ሰማያት ተቀድደው ተከፈቱ» ማለቱ ነው የሚል ገላጭ ቃል ኢየሱስ ከውሃው ውስጥ እየወጣ ሳለ ከዚህ ክፍተት መንፈስ ቅድስ ከሰማይ ወረደ። አራቱም ወንጌሎች መንፈስ ቅድስን በርግብ አምሳል ገለጠውታል። የሁለተኛው ምልክት ነገር መለኮታዊ አንድምታ በጣም ግልጽ አይደለም። ምናልባትም የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ የርግብን እንቅስቃሴ ይመስላል ማለት ሊሆን ይችላል። መንፈስ ቅዱስ በእሳትም ተመስሎአል (ሐሥ 2÷3) በውሆች ላይ ሰፍፎ እንደ ነበርም ተነግሮአል (ዘፍ 1÷2)። ከዚህም የሰፋ ሃሳብ ተንፀባርቆ ይሆናል። ርግብ የንጽሕና፣ የየዋህነትና የሰላም ተምሳሌት ናት። ሉቃስ ግን እንዲያውም ከተምሳሊትነት ያለፈ አካላዊ ቅርጽ እንደ ነበረ ነው የሚነግረን።

ዮሐንስ ይህን የመንፈስ ቅዱስ መገለጥ ዓይቶአል ምናልባት ሕዝቡም ሳያዩ አይቀሩም። ይህ ደግሞ ኢየሱስ ዮሐንስ እንደ ተናገረለት ለመሆኑ አንድ ትልቅ ማረጋገጫ ነበር። ይህ ሁኔታ ሕዝቡ ትኩረታቸውን ከዮሐንስ ይልቅ ወደ ኢየሱስ ዞር እንዲያደርጉ ሊያደርግ ይችላል (ዮሐ 1÷32-34 ጋር ያነ)።

ሦስተኛው ምልክት ከሰማይ የመጣው ድምጽ ነው። እግዚአብሔር ሦስት ጊዜ ከሰማይ ስለ ኢየሱስ ማንነት ማረጋገጫ ሳጥቷል ሉቃ 3÷22፤ 9÷35፤ ዮሐ 12÷28)። ኢየሱስን በተመለከተ የምንሰጠው ምስክርነት እግዚአብሔር ከሰጠው ምስክርነት የተለየ መሆን እንደሌለበት የወንጌል ጸሐፊዎቹ ያመለክታሉ። እግዚአብሔር ስለ ኢየሱስ የሰጣቸው ሦስቱም ምስክርነቶች የብሉይ ኪዳን መሰረት ያላቸው ነበሩ። «አንተ ልጄ ነህ[2] ... በአንተ ደስ ይለኛል» የሚለው

[2] "Adoptionism" ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው የተጠመቀ ጊዜ ነው የሚለውን ሃሳብ የሚያንፀባርቅ ነው። ይሁን እንጂ ከሦስቱ ተወራራሽ ወንጌሎች አንዱም እንኳ ይህን አይደግፍም። ሦስቱም ቀድሞውንም ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ነው የሚነግሩን። በተጨማሪም ማቴዎስና

በመዝሙር 2÷7 እና በኢሳይያስ 42÷1 ላይ የተመሰረተ ነው:: እግዚአብሔር ለልጁ ያለው ጥልቅ ፍቅር ዘፍጥረት 22ን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል::[3] እዚህ ላይ ምንም አዲስ ነገር የለም:: ሆኖም ሁሉም ስለ መሲሑ በሚናገረው በብሉይ ኪዳን ትንቢት ላይ የተመሠረቱ ክቡርና የበለጸጉ ቃላት ናቸው:: ከዚህም በላይ ኢየሱስ ሲጠመቅ የታዩት እነዚህ ሦስት ምልክቶች (ሰማይ መከፈቱ፣ የእግዚአብሐር ድምፅ ከሰማይ መምጣቱና መንፈስ ቅዱስ መውረዱ) መሲሕ ሲመጣ ይፈጸማሉ ብለው አይሁድ የሚጠብቋቸው ነበሩ::[4] *Testaments of the Twelve Patriarchs,* የሚለው መጽሐፍ ስለ መሲሑ የሚናገረውን በመጥቀስ ቲ.ሌዊ ሲናገር፣

> ሰማያት ይከፈታሉ፤ ከክብር መቅደስ ቅድስና በእርሱ ላይ ከአባታዊ ድምፅ ጋር አብርሃም ለይስሐቅ በተናገረው ዓይነት ይወርዳል:: የልዑል ክብር በታላቅ ኃይል ይወርድበታል:: የማስተዋልና የቅድስና መንፈስ ያርፍበታል (ውሃ ውስጥ እያለ):: ምክንያቱም በእውነት ለዘላለም ልጆቹ ለሆኑት የእግዚአብሔርን ግርማ ይሰጣልና::

በተጨማሪ (*T. Jud*) ቲ.ጁድ (24:3)፣ «ሰማያት ተከፍተው የቅዱስ አባቱ በረከት የሆነው መንፈስ በእርሱ ላይ ይፈስሳል:: በእናንተም ላይ

---

ሉቃስ ስለ ኢየሱስ መወለድ በሚያቀርቡት ትረካ በተፀነሰ ጊዜ እንኳ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ነበር ይናገራሉ:: ዮሐንስና ጳውሎስም ኢየሱስ ሰው ከመሆኑ በፊት አምላክ እንደ ነበር በድጋሚ አመልክተዋል::

[3] W. Stegner, "The Baptism of Jesus: A Story Modeled on the Binding of Isaac," *BR* 1 (Fall 1985): 36-46. ዘፍጥረት 22 አስመልክቶ በኋላ የተሰጠው የአይሁድ ትርጉም (Targums) ስለ ኢየሱስ መጠመቅ መሠረት የሚሆኑ ነጥቦችን ያቀርባል ብለዋል:: ይህ ትክክል ከሆነ የኢየሱስ መጠመቅ ከመስቀሉ ጋር ይያያዛል ማለት ነው፣ ከማር 10÷38፤ 15÷37-38 ጋር ያነ::

[4] J.R. Edwards, "The Baptism of Jesus According to the Gospel of Mark," *JETS* 34/1 (Mar 1991): 43-57.



የጸጋውን መንፈስ ያወርዳል» ይላል:: ስለሆነም በዚያ ዘመን የነበሩ አይሁድ እነዚህን ሦስት ምልክቶች የመሲሑ ማረጋገጫ እንደ ሆኑ አድርገው ይተረጉሟቸዋል:: በዚህ ዓይነት የኢየሱስ አገልግሎት ጅማሬ በይፋ ታውጆአል፤ ሁሉም የሥላሴ አካላት በአጀማመሩ ተሳትፈዋል:- እግዚአብሐር በምጡቅነቱ፣ ወልድ በተሠግዎ፣ መንፈስ ቅዱስ በመውረዱ ተሳትፈዋል:: በሉቃስ አጻጻፍ እንደ ተለመደው በዚህ ጊዜ ኢየሱስ ሠላሣ ዓመት ያህል ይሆነው እንደ ነበር የዘመን አቈጠር «ማስታወሻ» ይተውልናል::

**§ 25**
**የኢየሱስ መፈተን**
**(ማቴ 4÷1-11፤ ማር 1÷12-13፤ ሉቃ 4÷1-13)**

ስለ ኢየሱስ መጠመቅ የቀረበው ታሪክ እርሱ ክርስቶስ መሆኑን ያስተምረናል:: ስለዚህም ከዚያ ወቅት በኋላ ጥያቄው ኢየሱስ መሲሕ መሆን አለመሆኑ ሳይሆን፣ «ምን ዓይነት መሲሕ ነው?» የሚል ነበር:: ኢየሱስ ባገለገለበት ዘመን የነበሩ ሰዎች የፖለቲካ ጀግና ይሆናል ብለው ተስፋ አድርገው ነበር:: እዚህ ላይ እያየን ያለነው ግን እንዲህ ዓይነት መሲሕ አይደለም:: ኢየሱስ በስብዕናው የምድረ በዳ ልምምዳቸውን በመኖር እስራኤልን ወክሎ ነበር (ዘዳ 6-8 ጋር ያነ):: የእስራኤል ምድረ በዳ ሕይወት ዐርባ ዓመት ነበር፤ የኢየሱስ ግን ዐርባ ቀን ነው:: ምንም እንኳ ያንን የማድረግ መብት ቢኖረውም እንደ እግዚአብሔር ለመሆን በተፈተነ ጊዜ ኢየሱስ ፈተናውን ያሸነፈ ሁለተኛው አዳም[5] ነው (ፊልጵ 2÷6-7):: ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ነጻ ያወጣ አዲሱ ሙሴ ነው (ዘዳ 34÷1-8 ከዘዳ 18÷15፣ 18 ጋር ያነ)::[6]

---

[5] ጥንት በጁስቲን ማርቲር ዘመን እንኳ *(Dialogue with Trypho 103)* የኢየሱስ መፈተን በኤደን አትክልት ስፍራ ከነበረው አዳም ጋር ተያይዞ ቀርቧል:: የአዳምን ገጽታ እንደሚያቀርቡት የአቡቀለምሲስ መጻሕፍት ሁሉ ሮሜ 5÷12-21 እና 1ኛ ቆሮ 15÷45-49 ይህንኑ ንጽጽር ያቀርባሉ::

[6] J.W. Van Henten, "The First Testing of Jesus: A Rereading of Mk 1:12-13," *NTS* 45 (1999): 349-366.

ውጊያው ተጀምሮአል:: ኢየሱስ የመሲሕነት ተግባሩን ለመፈጸም ሲነሣ፣ ሰይጣን ደግሞ ጠላትነት[7] ሥራውን ጀመረ:: ከጥምቀቱ በኋላ ኢየሱስ ከማጥመቂያው ገንዳ ወደ ፈተና ወላፈን ነበር የተሸጋገረው:: በእያንዳንዱ ፈተና ኢየሱስ ቀላሉን መንገድ በመከተል ወደ መሲሕነት አገልግሎቱ እንዲያመራ ሰይጣን አቋራጭ እያቀረበለት ነበር:: ይሁን እንጂ እነዚህ አቋራጭ መንገዶች ከእግዚአብሔር እቅድ የሚያስወጡ «አጨናጋፊዎችም» ነበሩ:: በጣም ደስ የሚለው ግን ኢየሱስ ሁሉንም አልተቀበለም:: ከዚህም ባሻገር ኢየሱስ «በማንኛውም ሁኔታ እንደ እኛ» የተፈተነ ነበረ:: ስለዚህም የእኛን ትግልና ውጣ ውረድ ይረዳል:: በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት ፈተናን ማሸነፍ እንደምንችል አርአያ ሆኖልናል::

[1]ከዚህ በኋላ («በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ»[ሉቃ]) መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን («ወዲያውኑ»[ማር]) በዲያብሎስ ይፈተን ዘንድ ወደ ምድረ በዳ ወሰደው:: [2]አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከጾመ በኋላ ተራበ:: («ከአራዊትም ጋር ነበረ»[ማር]) [3]ፈታኙም («ሰይጣን»[ማር]) ወደ ኢየሱስ ቀርቦ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ እነዚህን ድንጋዮች እንጀራ እንዲሆኑ እዘዝ» አለው

ማቴ 4÷1-4ከ
ማር 1÷12-13፤
ሉቃ 4÷ 1-2

[4]ኢየሱስም «ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም»[ሀ] ተብሎ ተጽፎአል» ሲል መለሰለት::

*[ሀ]4 ዘዳ ፰÷3*

[7] P.Pokorny, “The Temptation Stories and their Intention,” *NTS* 20 (1973-1974): 115-127. በሃይማኖት ታሪክ መሠረት አዲስ ጅማሬና መፈተን ተያያዥ ነገሮች መሆናቸውን ያመለክታል:: ብዙ ክርስቲያኖችም ተመሳሳይ ልምምድ አላቸው:: «ከተራራ ሕይወት» ልምምድ በኋላ ብዙ ጊዜ ከፍተኛ ፈተና ይገጥመናል::



በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ (ሉቃ 4÷1) ኢየሱስ ወደ በረሃ ተወሰደ:: ማርቆስ የተጠቀመበት ሐረግ ሥዕላዊ ገላጭነት ያለው ነው:: ቃል በቃል ከወሰድነው ኢየሱስ ወደ ምድረ በዳ «አሽቀነጠረው» ወይም «ገፈተረው» ነው የሚለው:: በምድረ በዳ ኢየሱስ ፊት ለፊት ከሰይጣን ጋር ተጋፈጠ:: ሉቃስ የተጠቀመው «ዲያብሎስ» የሚለውን የግሪክ ቃል ሲሆን (ዲያብሎስም ማለት «ተሳዳቢ» ወይም «በሐሰት የሚከሰስ» ማለት ነው):: ማቴዎስ «ዲያብሎስ» የሚለውን የግሪክ ቃልና «ሰይጣን» የሚለውን አቻ ትርጉም ያለውን የዕብራይስጥ ቃል (*Satanos* ማለትም «ባላጋራ» ማለት ነው) ተጠቅሟል:: ሰይጣን ባደረበት ከፍተኛ ትዕቢት ምክንያት ከሰማይ የተጣለ (ኢዮ 1-2፤ ኢሳ 14÷12 ፤ ሉቃ 10÷18፤ 1ጢሞ 3÷6) ኃይለኛ መልአክ ነው (2ቆሮ 11÷14 ፤ 2ተሰ 2÷9፤ ይሁዳ 6፤ ራእ 13÷13-14):: የዚህን ዓለም የጨለማ ኃይላት ይገዛል (2ጴጥ 2÷4፤ ይሁዳ 6፤ ከ2ቆሮ 4÷4 ጋር ያነ)፤ የእግዚአብሔርንም ቤተ ክርስቲያን ማጥፋት ይፈልጋል (1ጴጥ 5÷8፤ ራእ 12÷13-17):: ያም ቢሆን ከእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ነው (ኢዮ 1÷12፤ 2÷6፤ ማቴ 12÷29)::

ውጊያው ፍትሐዊ አይመስልም:: ኢየሱስ አርባ ቀንና ሌሊት በመጾሙ በጣም ደክሞ ነበር:: ያም ሆኖ ሰይጣን በዚያን ጊዜ እንኳ ከፍተኛ ጉስቁልና ውስጥ ነበር:: አንዳንዶች ኢየሱስ በእርግጥ አርባ ቀንና ሌሊት ጾሟል ወይ ብለው ይጠይቃሉ:: ይሁን እንጂ እንደዚያ ለማድረግ እርሱ የመጀመሪያው አልነበረም (ሙሴ፣ ዘፀ 34÷28 እና ኤልያስ፣ 1ነገ 19÷4-8 ጋር ያነ) የመጨረሻውም አይደለም:: በዘመናችንም ለአርባ ቀን ያህል የዘለቁ የጾም ወቅቶች መኖራቸው አላስፈላጊ ጥርጥሮችን ማስወገድ ችለዋል:: ማርቆስ የሚገርም ፍንጭ ያወጣል፤ «ከአራዊትም ጋር ነበር» ይላል:: በሌላ አነጋገር ኢየሱስ ብቻውን ነበር በጣም ተርቦም ነበር:: በአካላዊ ደረጃ ባዶ ነበር፤

በመንፈሳዊ ሕይወት ደረጃ ግን ሙሉ ነበር:: የእኛ ሕይወት ግን ብዙውን ጊዜ የተገላቢጢሽ ነው::

እያንዳንዱን በተናጠል ከማየታችን በፊት እነዚህን ሦስት ፈተናዎች በተመለከተ ልናስተውላቸው የሚገቡን በርካታ ጉዳዮች አሉ:: በመጀመሪያ ሦስቱንም ፈተናዎች «ከሆንክ» ወይም «ከሆነ» በሚል ሁኔታ የቀረቡ ናቸው:: የመጀመሪያዎቹ ሁለት ፈተናዎች «የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ» የሚል ቃል ይዘዋል:: ምናልባትም፣ «ለእግዚአብሔር ልጁ ከሆንህ» ተብሎም ሊቀርብ ይችላል:: ከዚህም ባሻገር አነጋገሩ አሻሚ ሊሆን ይችላል:: ሰይጣን በኢየሰሱ ላይ እያሾፈበት ነው:: በአጭር አነጋገር፣ «ማንነትህን አረጋግጥ» እያለው ነበር::

ሁለተኛው፣ ሦስቱም ፈተናዎች በ1ዮሐንስ 2÷15-17 ካለው ጋር ተነፃፃሪ ናቸው:-

> ዓለምን ወይም በዓለም ያለውን ማንኛውንም ነገር አትውደዱ ማንም ዓለምን ቢወድ የአብ ፍቅር በእርሱ ዘንድ የለም፤ ምክንያቱም በዓለም ያለው ሁሉ የሥጋ ምኞት፣ የዐይን አምሮትና የኑሮ ትምክሕት ከዓለም እንጂ ከአብ የሚመጣ አይደለም:: ዓለምና ምኞቱ ያልፋሉ፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚፈጽም ግን ለዘላለም ይኖራል::

ይህ በዘፍጥረት 3÷6 ሔዋን በምድረ በዳ የተፈተነችባቸውን ሦስት ፈተናዎችንም ያመለክታል፤ «ሴቲቱ የዛፉ ፍሬ ለመብል መልካም፣ ለዐይን የሚያስደስትና ጥበብንም ለማግኘት የሚያጓጓ እንደሆነ ባየች ጊዜ ከፍሬው ወስዳ በላች፤ ከእርሷም ጋር ለነበረው ለባሏ ሰጠችው፤ እርሱም ባላ::» ይህ ሰይጣን እኛንም የሚፈትንበት በእነዚህ ሦስት መንገዶች ብቻ እንደሆነ እንድናምን ሊመራን ይችላል:- በሥጋ ምኞት፣ በዐይን አምሮትና በኑሮ በመመካት::



ሦስተኛ፣ ምንም እንኳ ሰይጣን ፈታኝ ቢሆንም እኛም ተጠያቂዎች ነን:: ያዕቆብ 1÷14 «ነገር ግን እያንዳንዱ የሚፈተነው በራሱ ክፉ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ነው» ይላል:: ሰይጣን አሳስቶኝ አደረግሁት» ማለቱ ምክንያት ሊሆን አይችልም:: ከዚህም ባሻገር፣ «ኢየሱስ ኃጢአት ያላደረገው የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነ ነው» የሚሉም ይኖራሉ:: ይሁን እንጂ የመጀመሪያው አዳም ኃጢአትን አለማድረግ ይችል እንደ ነበር ሁሉ ሁለተኛውም አዳም ኃጢአት ማድረግ ይችል እንደ ነበር መዘንጋት የለብንም::

አራተኛ፣ ኢየሱስ እነዚህን ፈተናዎች አንድ በአንድ የተቃወመው ከቅዱሳት መጻሕፍት በመጥቀስ እንደ ነበር ሊስተዋል ይገባል:: እኛም ከዚያ ያነሰ ማድረግ አይጠበቅብንም (ኢየሱስ በመጨረሻ ከዘዳግም 6÷13 የጠቀሰው የተብራራ ፍቺ ከመሆኑ ውጪ ከእግዚአብሔር ቃል የተጠቀሱት ሁሉ ከዕብራይስጡም ሆነ ከሰብዓ ሊቃናት ትርጉም አንጻር ቃል በቃል የተወሰዱ ናቸው):: በሕይወታችን የሚያስቸግረን ኃጢአት ካለ መልሱ የቅዱሳት መጻሕፍትን ክፍል በቃል ማጥናትና ራስን ለመንፈስ ቅዱስ ምሪት ማስረከብ እንጂ ያንን ኃጢአት ለማሸነፍ የሚያስችለንን ራስን የመግዛት ችሎታ ለማዳበር ትግል ማድረግ አይደለም:: ከሰይጣን ጋር ትንንቅ ለመያያዝ የምናስብ ከሆንን አደገኛ ሞኝነት ተጠናውቶናል:: ከላይ የተመለከትነው ክፍል ሰይጣን ጮሌ፣ አንደበተ-ርቱዕና የቅዱሳት መጻሕፍት ዕውቀት ያለው መሆኑን ያሳያል::

በመጨረሻም፣ ማቴዎስና ሉቃስ ሁለተኛውንና ሦስተኛውን ፈተና ያቀረቡት በተቃራኒ ቅደም ተከተል ነው:: ለዚህ ምክንያቱ ሁለቱም ታሪኩን ያቀነባበሩት ከፍተኛ ጡዘት ላይ ደርሶ እንዲያበቃ ለማድረግ በመፈለጋቸው ነበር:: የሉቃስ አቀራረብ ሰይጣን ኢየሱስን ወደ መቅደስ እንደ ወሰደውና (የሉቃስ ትኩረት ነጥብ) ጥቅስን በተሳሳተ መልክ መጥቀሱን በማሳየት ሲሆን ማቴዎስ ግን ትረካውን ጡዘት ላይ

የሚያደርሰው (ሀ) እንደ ስድብ በሚቈጠር አሳፋሪ ሁኔታ ኢየሱስ ወድቆ እንዲሰግድለት ሰይጣን እንደ ጠየቀውና (ለ) «ከፊቴ ራቅ» (ቁ 10) በማለት ኢየሱስ ሰይጣንን እንዳዘዘው በማሳየት ነው::

## ፈተና 1 - የሥጋ ምኞት

በተአምር ራሱን እንዲመግብ ለኢየሱስ ጥያቄ ቀርቦለት ነበር:: መጀመሪያ ላይ፣ ጉዳዩ ሲታይ ይህን ማድረጉ ኃጢአት ላይመስል ይችላል:: አብዛኛው ሕዝብ ይህንን ማድረጉን በወደደለት ነበር:: ሕዝቡን ለማበልጸግ መሲሕ እንዲህ ያሉ አስደናቂ ነገሮችን ያደርጋል ተብሎም ሲጠበቅ ነበር:: ሆኖም ይህንን ማድረግ መለኮታዊ ኃይሉን በተሳሳተ መልክ እንደ መጠቀም ይሆንበት ነበር:: አገልግሎቱ ጅማሬ ላይ ኢየሱስ ኃይሉን ግላዊ ፍላጐቱን ለሟሟላት ከተጠቀመበት እስከ ጌቴሴማኒ በመሄድ ጉዞውን የሚፈጽምበት መንገድ አይኖርም ነበር:: በተጨማሪም እንደዚያ ቢያደርግ ከሰብዓዊ ሕልውና ክልል ይወጣ ነበር:: ከዚያ ወዲያ እንደ ማንኛችንም ሁሉ መከራን ተቀብሎአል (ዕብ 4÷15-16) ሊባልለት አይችልም ነበር፤ ምክንያቱም እርሱ በተአምራዊ ሁኔታ ማምለጥ ሲችል እኛ ግን እንደዚያ ማድረግ አንችልም::

በዘዳግም 8÷3 ሙሴ እስራኤላውያንን ራሳቸውን ዝቅ እንዲያደርጉና እምነታቸውን በራሳቸው ላይ ሳይሆን በእግዚአብሔር ላይ እንዲያደርጉ ያሳስባል:: እግዚአብሔር በምድረ በዳ መና እንደ ሰጣቸው ያስታውሳቸዋል:: ስለሆነም የኢየሱስ መፈተን እስራኤላውያን በምድረ በዳ ካሳለፉት ልምምድ ጋር ተነጻጽሮአል:: በዚህ ደረጃ በርካታ ተነጻጻሪ ገጠመኞች አሉ፣ አርባ ቀኖች ከአርባ ዓመታት፣ በመንፈስ ተመርቶ ወደ ምድረ በዳ መሄድና በምድረ በዳ መፈተን ተነጻጽረዋል::

5ቀጥሎም ዲያብሎስ ኢየሱስን ወደ ቅድስተ ከተማ በመውሰድ በቤተመቅደሱም ዐናት ላይ አውጥቶ፣

**ማቴ 4÷5-7ከ**
**ሉቃ 4÷9-10 ጋር**



6«የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ ራስህን ወደ መሬት ወርውር፤ እንዲህ ተብሎ ተጽፎአልና፤ «እግርህ በድንጋይ እንዳይሰናከል፣ በእጃቸው ያነሡህ ዘንድ፣ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝልሃል::»

7ኢየሱስም፣ «እንደዚሁም በመጽሐፍት፣ እግዚአብሔር አምላክህን አትፈታተነው ተብሎ ተጽፎአል» በማለት መለሰለት::

## ፈተና 2 - የኑሮ ትምክሕት

የመቅደሱ ዐናት ከየትኛው ስፍራ እንደነበር እርግጠኞች አይደለንም:: ሦስት አማራጭ ሐሳቦች ይኖራሉ:- (1) የመቅደሱ ጫፍ፣ (2) የሰሎሞን ባለ ምሰሶ አዳራሽ ጫፍ፣ (3) የቤተ መንግሥቱ ዕድሞ ዐናት (Josephus. *Ant.* 15.412-413 ይመ):: አይሁድ መሲሑ በተአምራዊና በአስደናቂ ሁኔታ ከመቅደሱ ዐናት ላይ ይገለጣል የሚል ትውፊት ነበራቸው:: ስለሆነም ኢየሱስ ያንን ቢያደርግ ኖሮ በሕዝቡ ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት ያለው መሲሕ በሆነ ነበር:: ብዙ ጊዜንና በችግር የተጨናነቀ በርካታ አገልግሎትን ማዳን ይችል ነበር:: ችግሩ ግን ሰዎች ፍጹም በተሳሳተ ሁኔታ ይረዱት ነበር፤ የእግዚአብሔርም ዕቅድ ሊጨናገፍ ይችል ነበር::

ሰይጣን አሁን ከቅዱሳት መጻሕፍት የመጥቀስ ተግባር ይዟል፤ ያንንም ተግባር በተለመደው አሳሳችነቱ ያከናውን ነበር:: ከመዝሙር 91÷11 የጠቀሰ ቢሆንም፣ «በመንገድህ ሁሉ» የሚለውን ሐረግ ግን ገድፎታል:: ግድፈቱን የፈጸመው ሆን ብሎ ሊሆን ይችላል:: የእግዚአብሔር የሆነ ማንኛውም መንገድ ትዕቢትንና የራስን ፈቃድ መፈጸምን አይጨምርም:: ይሁን እንጂ እዚህ ድረስ ሰይጣን ትክክል ነበር- እግዚአብሔር «በጠባቂ» መላእክት አማካይነት ረድኤትንና ማዳንን ያደርጋል (ኢዮ 1÷10፤ 2ነገ 6÷8-17፤ መዝ 34÷ 7፤ ይሁዳ 9 ጋር ያነ)::

[5]ከዚያም ዲያብሎስ ወደ አንድ ከፍታ ቦታ አውጥቶት የዓለምን መንግሥታት ሁሉ በቅጽበት አሳየው፤ [6]እንዲህም አለው፤ «የእነዚህ መንግሥታት ሥልጣንና ክብር ሁሉ ለእኔ ተሰጥቶአል፤ እኔም ለምወደው ለምሰጥ ለአንተ እሰጥሃለሁ፤ [7]ስለዚህ ብትሰግድልኝ ይህ ሁሉ የአንተ ይሆናል።»

ሉቃ 4÷5-8፣13 ከ
ማቴ 4÷10-11፤
ማር 1÷13ለ ጋር

[8]ኢየሱስም መልሶ (ከፊቴ ራቅ»[ማቴ]) «ለጌታ ለአምላክህ ስገድ፤ እርሱንም ብቻ አምልክ» ተብሎ ተጽፎአል አለው። [13]ዲያብሎስም ፈተናውን ሁሉ ከጨረሰ በኋላ ሌላ አመቺ ጊዜ እስኪያገኝ ድረስ ከእርሱ ተለየ (መላእክትም መጥተው አገለገሉት [ማቴ፣ማር])።

## ፈተና 3 - የዐይን አምሮት

ሰይጣን እጅግ ከፍወዳለ ተራራ አውጥቶ (ማቴ)፣ የዓለምን መንግሥታት ሁሉ በቅጽበት አሳየው (ሉቃ)። ምናልባትም ይህ ተአምራዊ ራእይ እንደነበረ የሚያመለክት ይመስላል። ይሁን እንጂ ሼፓርድ የተባሉት ደራሲ ትክክል ከሆኑ (ገጽ 73) ኳራንቲየኒያ ከሚባል ተራራ ጫፍ ላይ በመውጣት አስደናቂ የነበረችውን የፓለስቲና ከተማ ዙሪያ ገባውንና በዚያ ዘመን በሚታወቀው ዓለም ዋና ዋና ወደ ነበሩ መንግሥታት ማለት ወደ ሮም፣ ግሪክ፣ ፋርስና አሦር የሚያመሩትን መንገዶችን ማየት ችሎ ነበር።

ሰይጣን የምድር ሁሉ ገዢ መሆኑን ይናገራል። በመሠረቱ ለጊዜውም ቢሆን ይህ እውነት ነበር። ይሁን እንጂ የሰይጣን የመቆጣጠር ዐቅም ውሱን መሆኑን መዘንጋት የለብንም። በውሻ ማሰሪያ ገመድ የታሠረ ያህል ነው። ገመዱ ሊዘረጋ ከሚችልበት አድማስ ውጪ ያለው ሁኔታ ሁሉ ከእርሱ ግዛት ውጪ ነው (ዮሐ 12÷31፤ 14÷30፤ 16÷11፤ 2ቆሮ 4÷4፤ ኤፌ 2÷2፤ 1ዮሐ 4÷4፤ 5÷19 ጋር ያነ)። ይህን በተመለከተ ማክጋርቪ እንዲህ ብሏል:-

> ሰይጣንና ባለሟሎቹ በዓመፅ ዓለምን መቆጣጠራቸው እውነት ነው፤ ኢየሱስ ግን የእግዚአብሔር ወራሽ እንደ መሆኑ መጠን



ዓለምን የመግዛት መብት አለው (ማቴ 21÷33-43)። ከሰይጣን ይልቅ የበረታ በመሆኑ በድርድር ሳይሆን ድል በማድረግ እንደ ገና መንግሥቱን ለማስመለስ መጥቶአል (ሉቃ 11÷19-22)። ሆኖም እርሱ የሚፈልገው መንግሥት መንፈሳዊውን እንጂ ዓለማዊውን አይደለም (ገጽ 98)።

ሰይጣን እንዲሰግድለት መጠየቁ ፍጹም የሚያስቆጣ ነበር። ይሁን እንጂ ጥያቄውን ያቀረበው ረቀቅ ባለ መንገድ ነበር። ሰይጣን ኢየሱስን የጠየቀው እየሰገደለት እንዲኖር ሳይሆን በዚያች ቅጽበት ብቻ እንዲሰግድለት ነበር።

በፈተናው መጨረሻ ላይ ኢየሱስ ሰይጣንን ከእርሱ ዘወር እንዲል አዘዘው። ደግሞ ለጌታ መታዘዝም ይገባዋል። አመቺ ጊዜ እስኪያገኝ ድረስ ከእርሱ ተለየ በማለት ሉቃስ ዘግቧል። ከቅዱሳት መጻሕፍት መጥቀስ ሰይጣንን ያባርራል (ያዕ 4÷7 ጋር ያነ)። የመጀመሪያውን ዕድል ሲያገኝ በኢየሱስ እንዳደረገው ሁሉ ተመልሶ ይመጣል። ይሁን እንጂ ፈታኙን ድል ለማድረግ ቁልፉ የእግዚአብሔር ቃል ነው።

እዚህ ላይ እንደ ማቴዎስ ሁሉ ማርቆስም ወደ ታሪኩ በመመለስ መላእክት መጥተው ኢየሱስን እንዳገለገሉት ይነግረናል። እንዲህ ያለ ሁኔታ ቀጥሎ የምናነበው በሌላው የኢየሱስ ወሳኝ የሽግግር ወቅት በጌቴሴማኒ የአትክልት ስፍራ ይሆናል (ሉቃ 22÷43)።

§ 26
ስለ ዮሐንስ ማንነት
የተነሣ ጥያቄ
(ዮሐ 1÷19-28)

[19]አይሁድ ማንነቱን እንዲጠይቁት ካህናትንና ሌዋውያንን ከኢየሩሳሌም ወደ እርሱ ሲልኩ፣ ዮሐንስ የሰጠው ምስክርነት ይህ ነበር። [20]ከመመስከርም ወደ ኋላ አላለም፤ «እኔ ክርስቶስ አይደለሁም» ብሎ በግልጽ መሰከረ። [21]እነርሱም፣ «ታዲያ አንተ ማን ነህ? ኤልያስ

ነህ?» ብለው ጠየቁት:: እርሱም «አይደለሁም» አለ:: እነርሱም፣ «ታዲያ ነቢዩ ነህ?» አሉት:: እርሱም፣ «አይደለሁም» ሲል መለሰ:: [22]በመጨረሻም፣ «እንግዲያስ ማን ነህ? ለላኩን ሰዎች መልስ እንድንሰጥ ስለ ራስህ ምን ትላለህ?» አሉት [23]ዮሐንስም በነቢዩ በኢሳይያስ እንደ ተነገረው፣ «'ለጌታ መንገድ አቅኑለት' እያለ በምድረ በዳ የሚጮኽ ድምፅ እኔ ነኝ» ሲል መለሰ::

ዮሐንስ የሕዝቡ መነጋገሪያ ሆኗል:: እርሱን ለማነጋገር በትንሹ ሦስት የተለያዩ ወገኖችን ማለትም ሕዝቡን (ሉቃ 3፡15)፣ ሰዱቃውያንና (ዮሐ 1፡19-23) ፈሪሳውያንን (ዮሐ 1፡24-27) የሚወክሉ መጥተዋል:: እያንዳንዱ ወገን፣ «አንተ መሲሑ ነህን» የሚል ጥያቄ ይዞ ነበር የመጣው:: ዮሐንስ «አይደለሁም» በማለት ሲመልስላቸው «ታዲያ አንተ ማን ነህ፣ እያደረግህ ያለውን የምታደርገው ለምንድን ነው?» በማለት ሁለተኛ ጥያቄ አቀረቡ ::

በዮሐንስ 1፡19-23 የራሳቸውን ጥያቄ የያዙ የሁለተኛው ወገን ሰዎች መምጣታቸውን እንመለከታለን፤ እነርሱም ካህናትና ረዳቶቻቸው ሌዋውያን ነበሩ:: በፖለቲካ አመለካከታቸው በአመዛኙ ከሰዱቃውያን ጋር ይመሳሰላሉ፤ ሌላው ቀርቶ መሲሕ በአካል እንደሚመጣ እንኳ አያምኑም ነበር:: የመጡት ከዮሐንስ ለመማር ወይም ለኃጢአታቸው ንስሐ ለማድረግ አልነበረም:: እንደ እስራኤል ሃይማኖት መሪነታቸው ክልላቸውን ማስጠበቅ ነበር የሚፈልጉት::

ዮሐንስ ክርስቶስ አለመሆኑን በግልጽ ነግሮአቸዋል:: «ክርስቶስ» የተሰኘው ግሪክ ቃል «መሲሕ» የሚለው የዕብራይስጥ ቃል ትርጉም ሲሆን፣ «የተቀባ» ማለት ነው:: በብሉይ ኪዳን ሦስት ሹመቶች የሚሰጣቸው የተቀቡ እንደሆኑ ይታሰብ ነበር፤ መሲሑ ደግሞ ሦስቱም ሹመቶች ይሰጠዋል፤ እነርሱም፣ ነቢይ (ዘዳ 18፡15፣18) ካህንና (መዝ 110፡4) ንጉሥ ናቸው (መዝ 2 ፤ ኢሳ 2፡1-4፤ 9፡6-7) ::



«ኤልያስ ነህን?» በማለት ጠየቁ:: ዮሐንስ «አይደለሁም» አለ:: ኤልያስ ሊሆን ይችላል ብለው ያሰቡት ለምንድን ነው? ሰፊ ተቀባይነት የነበረው የአይሁድ ነገረ-መለኮት ኤልያስ ተመልሶ እንዲመጣ ይጠብቅ ነበር:: ኤልያስ እንዳልሞተ ይታወቃል:: ሚልክያስ እንደሚመለስ ትንቢት ተናግሮለታል (ሚል 3፡1፤ 4፡5):: በዚያን ወቅት ኤልያስ ሲመለስ የሚኖረውን ድርሻ በተመለከተ ትንሽ ግራ መጋባት ነበር:: (ሀ) መሲሕ ይሆናል (ለ) ለመሲሑ መንገድ የሚያዘጋጅ ይሆናል (ሚል 3፡1) ወይም ደግሞ (ሐ) የፍርድ መምጣት ምልክት ይሆናል (ሚል 4፡5)?

ዮሐንስ፣ «ይመጣል የተባለው ኤልያስ» መሆኑን ኢየሱስ ተናግሮአል (ማቴ 11፡14)፣ ይህንንም ለማረጋገጥ ከሚልክያስ 3፡1 ጠቅሶአል (ማቴ 11፡10):: ዮሐንስ ግን ኤልያስ መሆኑን ክዶአል:: ይህን ልዩነት እንዴት ነው የምናስታርቀው? (1) ምናልባት ዮሐንስ የሥራ ድርሻውን በሚገባ አልተረዳም ማለት ይቻላል:: ይሁን እንጂ ስለ ማንነቱ ለመናገር ከኢሳይያስ 40፡3 መጥቀሱን ግምት ውስጥ አስገብተን ስናስበው ይህ የሚያስኬድ አይደለም:: (2) ምናልባትም በሚልክያስ 3፡1 እና 4፡5 መካከል ልዩነት ሊኖር ይችላል:: ሰዱቃውያን የጠየቁት ሚልክያስ 4፡5 ላይ ያለውን ትንቢት ማሟላቱን ከሆነና ምንባቡ የሚናገረው ገና ወደ ፊት ስለሚመጣው ምስክር ከሆነ (ራእ 11፡3 አንዳንዶች እንደሚያስቡት) ዮሐንስ ያ ሰው እንዳይደለ መናገሩ ትክክል ነበር ማለት ነው:: (3) ከሁሉም ይልቅ ተቀባይነት አግኝቶ የነበረው የተሳሳተ አስተሳሰብ ኤልያስ የሚመጣው መሲሕ ነው የሚለው ነበር:: የሰዱቃውያን ሦስት ጥያቄዎች በመሲሑ፣ በኤልያስና በነቢዩ መካከል ያለውን ልዩነት ያገናዘቡ አይመስልም (ዘዳ 18፡15፣18):: ስለዚህም ኤልያስ ነው ብለው የሚያስቡት ሰው እርሱ አለመሆኑን ዮሐንስ መናገሩ ትክክል ነበር::

የነበራቸው ግምት በሙሉ ትክክል እንዳልነበር ሲረዱ፣ በመጨረሻ «እንግዲያስ ማን ነህ?» በማለት ጠየቁ (ዮሐ 1፥22)፡፡ ዮሐንስ፣ «'ለጌታ መንገድ አቅኑለት' እያለ በምድረ በዳ የሚጮህ ድምጽ እኔ ነኝ» (ኢሳ 40፥3) የሚለውን የነቢዩ ኢሳይያስን ቃል በመጥቀስ ነበር ምላሽ የሰጣቸው፡፡

ዮሐ 1፥24-28

24ከተላኩትም ፈሪሳውያን አንዳንዶቹ 25«ታዲያ፣
ክርስቶስ ወይም ኤልያስ ወይም ነቢዩ ካልሆንህ ለምን
ታጠምቃለህ?» ብለው ጠየቁት፤
26ዮሐንስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፣ «እኔ በውሃ አጠምቃለሁ፤ እናንተ
የማታውቁት ግን በመካከላችሁ ቆሟል፤ 27ከእኔ በኋላ የሚመጣው፣ የጫማውን
ማሰሪያ ለመፍታት እንኳ የማልበቃ እርሱ ነው፡፡» 28ይህ ሁሉ የሆነው ዮሐንስ
ሲያጠምቅ በነበረበት ከዮርዳኖስ ማዶ በቢታንያ ነበር፡፡

አሁን ደግሞ ሦስተኛው ወገን ማለትም ፈሪሳውያን የዮሐንስን ማንነት ለመጠየቅ መጥተዋል (ዮሐ 1፥24-27)፡፡ መሲሕ አለመሆኑን ሲናገር ሰምተውታል፡፡ ይሁን እንጂ የሚያደርገው አንድ ዓይነት ሥልጣን እንዳለው ዓይነት ነበር፡፡ «እሺ፣ መሲሑ ካልሆንህ፣ ኤልያስ ወይም ነቢዩ ካልሆንህ ታዲያ፣ ለምን ታጠምቃለህ?» በማለት ጠየቁት፡፡

ለሦስተኛው ጥያቄ የሰጠው ይህ የዮሐንስ መልስ ለሰዱቃውያን ጥያቄ ከሰጠው መልስ ጋር በጣም ተመሳሳይ ነበር፤ «እኔ ለመሲሑ ዝግጅት እያደረግሁ ነው፤ የእኔ ጥምቀት ለመሲሑ ጥምቀት የሚያዘጋጁ ነው» በማለት ነበር የመለሰላቸው፡፡ ከዚያ በኋላ ደግሞ ኢየሱስ ከእርሱ እጅግ የላቀ መሆኑን በድጋሚ ተናገረ፡፡ የዮሐንስ አድማጮች ቀደም ሲል ኢየሱስ ከመጠመቁ በፊት ይህን ሰምተው ነበር [የክፍል 23ን ማብራሪያ፣ ማቴ 3፥11፤ ማር 1፥7፤ ሉቃ 3፥16 ይመ]፡፡ ሆኖም ዮሐንስ ቀደም ሲል፣ «ይመጣል» ነበር ያለው፤ አሁን ግን፣ «በመካከላችሁ ይገኛል» አለ፡፡



## § 27
## ዮሐንስ ኢየሱስን አወቀው
ዮሐ 1፥29-34

29ዮሐንስ በማግሥቱ፣ ኢየሱስ ወደ እርሱ ሲመጣ
አይቶ እንዲህ አለ፤ «እነሆ! የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ
የእግዚአብሔር በግ፤ 30ከእኔ በኋላ የሚመጣው ከእኔ በፊት
ስለነበር ከእኔ ይበልጣል ያልሁት እርሱ ነው፣ 31እኔ ራሴ
አላወቅሁትም ነበር፤ በውሃ እያጠመቅሁ የመጣሁትም እርሱ
በእስራኤል ዘንድ እንዲገለጥ ነው፡፡»

ዮሐንስ ስለ ማንነቱ ከተጠየቀና ከእርሱ ወደሚበልጠው ካመለከተ በኋላ (ዮሐ 1፡19-27) ኢየሱስ ወደ እርሱ ሲመጣ አየ፡፡ «እነሆ! የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ» በማለትም ጮኸ፡፡ እንዲህ በፍጥነት እንዴት ኢየሱስን ማወቅ ቻለ? ሁለቱ ሲገናኙ ይህ የመጀመሪያ አልነበረም፡፡ ከአርባ ቀን በፊት ዮሐንስ ኢየሱስን አጥምቆ ነበር (ቁ 32 ጋር ያነ)፡፡ አንዳቸው ለሌላው እንግዳ አልነበሩም፡፡ ሕፃናት በነበሩ ጊዜ በቤተሰቦቻቸው መካከል ጥብቅ መቀራረብ ነበር፡፡ የሕፃንነታቸው ታሪክ በቤተሰቦቻቸው በኩል ሳይተላለፍላቸውም አልቀረም፡፡

«የእግዚአብሔር በግ» የሚለው ቃል ጥልቅ ተምሳሌታዊ ትርጉም ያለው ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ «በግ» የሚለውን ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ የምናገኘው ይስሐቅ የመሥዋዕቱ በግ የት እንዳለ አብርሃምን በጠየቀው ጊዜና አብርሃምም ትንቢታዊ በሆነ መልኩ፣ «ለሚቃጠለው መሥዋዕት የሚሆነውን በግ እግዚአብሔር ራሱ ያዘጋጃል» በማለት በመለሰበት በዘፍ 22፥7-8 ነበር፡፡ ለሁለተኛ ጊዜ ቃሉ በዋናነት የተጠቀሰው የፋሲካው በግ በበኩር ልጆች ምትክ መሥዋዕት እንደሆነ በተገለጸበት በዘፀአት (12፥3-4 ጋር ያነ) ውስጥ ነበር፡፡ ደግሞም በእርግጥ በብዛት በዘሌዋውያንና በዘኁልቁ ውስጥ (ሰላሳ አራት ጊዜ) ነውር የሌለበት የአንድ ዓመት በግ ለኃጢአት መሥዋዕት ሲቀርብ እንደሚገባ በማስመልከት ተጠቅሷል፡፡ ኢሳይያስም በግ የሚለውን ተምሳሌታዊ ቃል የተጠቀመበት መከራ የሚቀበለውን የእግዚአብሔርን

ባሪያ ለማመልከት ሲሆን (ኢሳ 53፥7) ከዚሁ ጋር በተያያዘ በ1ኛ ቆሮንቶስ 5፡7 የፋሲካ በግ ተብሎአል:: ይህን በግ በተመለከተ ሁለት አስገራሚ ነገሮች አሉ:: በመጀመሪያ ኢየሱስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰውን «የበግ» ጥላ/አካል አቀራረብ በትክክል መወከሉ ነው:: እንደ የኃጢአት መሥዋዕት ሆኖ በእኛ ቦታ መከራ ተቀበለ:: እንደ ፋሲካ በግ ለበኩር ልጆች ነፃ መውጣት የሚገባውን አድርጓል:: እግዚአብሔር ራሱ ያዘጋጀው በግ በመሆን የእኛ ምትክ ሆኖ ኢሳይያስ 53፥7ንና ዘፍጥረት 22፡8ን ፈጸመ:: ከኢየሱስ አገልግሎት ጅማሬ አንስቶ ዓላማው ጥረት ባለ ሁኔታ ተለይቶ መታወቁ በጣም የሚገርም ነው:: ዮሐንስን ያደምጡ ከነበሩት ሰዎች የእግዚአብሔር በግ ሲል ምን ማለቱ እንደነበር እንዴት ሊጠፋቸው ይችላል? በጣም የሚገርመው ሌላው ነገር ደግሞ «በግ» የሚለው ቃል በዮሐንስ ራዕይ ሃያ ስድስት ጊዜ መጠቀሱ ነው:: ይህ በዝምታ የታረደ መሥዋዕታችን ድል አድራጊና ፍጹም ሉዓላዊ ሆኗል ::

**ዮሐ 1፥32-34**

32ከዚያም ዮሐንስ እንዲህ ሲል ምስክርነቱን
ሰጠ፤ «መንፈስ እንደ ርግብ ከሰማይ ወረደ በእርሱ ላይ
ሲያርፍ አየሁ፣ 33በውሃ እንዳጠምቅ የላከኝም ፣በመንፈስ
ቅዱስ የሚያጠምቀው፣ መንፈስ ሲወርድና በእርሱ ላይ
ሲያርፍ የምታየው እርሱ ነው፣ ብሎ እስከነገረኝ ድረስ
እኔም አላውቅሁትም ነበር፤ 34አይቻለሁ፣ እርሱ
የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እመሰክራለሁ::»

ዮሐንስ ኢየሱስን ሊያጣው አይችልም:: በርግብ አምሳል የሚወርድ መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር መለኮታዊ ድንጋጌ የተወሰነ የመሲሑ ልዩ መታወቂያ ነበር:: ዮሐንስ ይህን ላለፉት አርባ ቀኖች ሲያሰላስል ኖሯል ::



**§ 28**
**የኢየሱስ የመጀመሪያዎቹ ደቀ መዛሙርት**
**ዮሐ 1፥35-51**

ይህ በዮሐንስ መጀመሪያ ምዕራፍ ከተጠቀሱ አራት ተከታታይ ቀኖች ሦስተኛው ነው (ከቁ 29፣35፣43 ጋር ያነ):: ኤደርሻይም እንደሚለው (I:345) በተለመደው የአይሁድ ባህል መሠረት ባልዋ የሞተባት ሴት የምትዳረው ሐሙስ ሲሆን ልጃገረድ የምትዳረው ግን ረቡዕ ዕለት ነበር:: በዮሐንስ 2፡1-11 ስለ አንድ ሠርግ እንመለከታለን:: ከግብገሩ ሁኔታ እንደምንረዳው የተደረገው ረቡዕ የሚፈጸም የልጃገረድ ሠርግ ሳይሆን አይቀርም:: ይህ እውነት ከሆነ ደግሞ ወደ ኋላ ተመልሰን ብንቆጥር ከሚከተለው የሁኔታዎች ቅደም ተከተል ላይ እንደርሳለን፤ (1) ሐሙስ ከአይሁድ ሸንጎ ከተላኩ ሰዎችና ከዮሐንስ ቃለ-ምልልስ የተደረገበት ቀን ነበር፤ ቁ. 19-28፤ (2) ዓርብ ኢየሱስ ከምድረ በዳ የተመለሰበት ቀን ነበር፤ ቁ. 29-34፤ (3) ቅዳሜ በተከታታይ ለሁለተኛ ቀን በትኩረት እየተመለከተው ኢየሱስ የእግዚአብሔር በግ መሆኑን የመሰከረበት ቀን ነበር፤ ቁ. 35-42:: በዚህ ጊዜ ዮሐንስ ሁለት ደቀ መዛሙርት ብቻ እንደነበሩት ግልጽ ይመስላል:: ምናልባት የተቀሩት የሰንበት ዕረፍት ወስደው ይሆናል:: ያም ሆነ ይህ እነዚህ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ኢየሱስን ለመከተል የመጀመሪያዎቹ ነበሩ:: ወንጌሎች ከሚያቀርቡት መረጃ ማየት እንደሚቻለው ይህ ምርጥ ከሚባሉት የዮሐንስ ሁለት ደቀ መዛሙርት ጋር ኢየሱስ ሲሄድ ዮሐንስ ለመጨረሻ ጊዜ ያየበት ወቅት ነበር፤ (4) እሑድ በፊልጶስ በኩል ናትናኤልንና ሌሎች ጥቂት ደቀ መዛሙርትን (እንድርያስ፣ ዮሐንስ፣ ጴጥሮስ፣ ያዕቆብ፣ ፊልጶስና ናትናኤል) አገኝና ያላቸውን ነገር ይዘው ከኢየሱስ ጋር ወደ ገሊላ ተመለሱ (ቁ 43-51):: ከሦስት ቀን በኋላ በቃና በነበረው ሠርግ እርስ በርሳቸው ይገናኛሉ (ዮሐ 2፥1)::

[35]በማግስቱ ዮሐንስ ከሁለቱ ደቀ መዛሙርቱ ጋር
እንደ ገና እዚያው ቦታ ነበር፤ [36]ኢየሱስንም በዚያ ሲያልፍ
አይቶ «እነሆ! የእግዚአብሔር በግ» አለ።

ዮሐ 1፥35-40

[37]ሁለቱ ደቀ መዛሙርትም ይህን ሲናገር ሰምተው ኢየሱስን ተከተሉት
[38]ኢየሱስም ዘወር ብሎ ሲከተሉት አየና፣ ምን ትፈልጋላችሁ? ብሎ ጠየቃቸው።
እነርሱም «ረቢ፣ የት ትኖራለህ?» አሉት፤ «ረቢ» ማለት መምህር ማለት ነው።
[39]እርሱም «ኑና እዩ» አላቸው። ስለዚህም ሄደው የት እንደሚኖር አዩ።
በዚያም ዕለት አብረውትዋሉ፤ ከቀኑም ዐሥር ሰዓት ያህል ነበር።
[40]ዮሐንስ የተናገረውን ሰምተው፣ ኢየሱስን ከተከተሉት ከሁለቱ አንዱ
የስምዖን ጴጥሮስ ወንድም እንድርያስ ነበር።

## የእንድርያስና የዮሐንስ መጠራት

ሁኔታው ከአጫጭር ዝርዝር ነገሮቹ ጋር ሲታይ አስቂኝ ይመስላል። ወደ ኋላ ዘወር ብሎ ኢየሱስ፣ «ምን ትፈልጋላችሁ?» አላቸው። ትክክለኛው ጥየቄ ግን፣ «ማንን ትፈልጋላችሁ?» የሚል ነው። የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት የሚፈልጉት ሰው እንጂ፣ «አንዳች ነገር» አይደለም። ኢየሱስ በድንገት ያንን መጠየቁ ሳያስደነግጣቸው አልቀረም። ምናልባትም ለጥቂት ጊዜ በድንጋጤ የሚናገሩት አጥተው ከቆዩ በኋላ ግን እነርሱም «የት ትኖራለህ?» የሚል ገራገር ዓይነት ጥያቄ አቀረቡ። እንደ ገና የኢየሱስ መልስ በጣም አጭር ነበር፤ «ኑና እዩ» ወይም፣ «ብትከተሉኝ፣ የት እንደምኖር እናንተ ራሳችሁ ታያላችሁ!» አላቸው።

ከቀኑ ዐሥር ሰዓት ላይ (ከፀሐይ መውጣት አንሥቶ ሲቈጠር)[8]

---

[8] ሔንድሪክሰን (ገጽ 104-105) እና ዌስትኮት (ቅጽ 2፣ ገጽ 324-326) ዮሐንስ የተጠቀመበት ጊዜ አቈጣጠር ከእኩለ ሌሊት አንሥቶ ቀንን መቍጠር የሚጀምረውን የሮማውያንን ሕዝባዊ ሰዓት አቆጣጠር ነው ሲል ሙግታቸውን ያቀርባሉ። እንዲህ ከሆነ ደግሞ ይህ ሁኔታ የተፈጸመው 10 ሰዓት ሳይሆን 4 ሰዓት ላይ ነበር ማለት ነው። ይህ የአቆጣጠር መንገድ የቀኑን ትክክለኛውን ሰዓት በገለጠባቸው ሌሎች የዮሐንስ ምንባቦችም ከሁሉም የተሻለው አቆጣጠር ነው (ዮሐ 4፥6፤ 4፥52 እና በተለይም



ኢየሱስ እንድርያስን ጠራ (ቁ 39-40)። ስሙ ያልተጠቀሰው ባልንጀራው ዮሐንስ ሊሆን ይችላል። ዮሐንስ ሆን ብሎ የራሱን ስም ከታሪኩ ውስጥ ያስቀራል (ዮሐ 13፥23፤ 19፥26:35፤ 21፥7፣20፣24)። ከዚህም በላይ ዮሐንስ ኢየሱስን መከተል የጀመሩበትን ትክክለኛ ሰዓት ጠቅሷል። ይህ አጭር የዓይን ምስክርነት ዘገባ ለዮሐንስ ሁኔታው ምን ያህል መታሰቢያነት ያለው እንደ ነበር ያመለክታል። መጀመሪያ የተጠራበት ሁኔታ ሕይወቱን በጥልቀት የነካ በመሆኑ ሌለው ቀርቶ ያ የሆነበትን ትክክለኛ ሰዓት ማስታወስ ችሏል። ከዚህ በኋላ ዮሐንስ ራሱ በዓይኑ የተመለከተውን ዝርዝር ጉዳይ ያቀርባል። ይህ ዮሐንስ ለደቀ መዝሙርነት የተጠራበት ጊዜ ባይሆን ኖሮ በዝምታ ያልፈው ነበር።

[41]እንድሪያስ በመጀመሪያ ያደረገው ወንድሙን ስምዖንን
ፈልጎ «መሲሑን አገኘነው» ብሎ መንገር ነው፤ መሲሕ
ማለት ክርስቶስ ማለት ነው። [42]ወደ ኢየሱስም
አመጣው። ኢየሱስም ተመለከተውና «አንተ የዮና ልጅ
ስምዖን ነህ፤ ኬፋ ተብለህ ትጠራለህ» አለው፤ ኬፋ ማለት
ጴጥሮስ ማለት ነው።

ዮሐ 1፥41-42

*42ኬፋ የሚለው የአረማይክ ቃልና ጴጥሮስ የሚለው የግሪክ ቃል ዐለት ማለት ነው።*

---

19፥14)። ችግሩ ግን ለሕዝባዊ የሮማውያን ጊዜ አቆጣጠር ዘዴ ምንም ድጋፍ በፍጹም ያልነበረ መሆኑ ነው። በእውነትም ፕሊኒ እንደሚለው (*Natural History*, 2.79.188) ሮማውያን ካህናት ለሕጋዊ ዓላማ ሕዝባዊውን ቀን የሚቆጥሩት ከእኩለ ሌሊት እስከ እኩለ ሌሊት ድረስ ነበር። ይሁን እንጂ ቀደም ባለው ዐረፍተ ነገሩ፣ «በየትኛውም ቦታ ያሉ የአገሬው ሰዎች» የቀኑን ሰዓት የሚቆጥሩት ከንጋት እስከ ውድቀት ያለውን ነው ብሏል። በእርግጥም ያለ ልዩነት ሁሉም የሮማውያን የፀሐዩ አቅጣጫ ሰዓት መቁጠሪያ የሚያንጸባርቁት ይህንን ነው። እኩለ ቀን የሚባለው ስድስት (VI) እንጂ አሥራ ሁለት (XII) አልነበረም። በአይሁድ አካባቢ ግን የቀኑ ሰዓት ከንጋት ወይም ከውድቀት አንሥቶ ሊቆጠር ይችላል። የቀኑ ሰዓት ከእኩለ ሌሊት አንሥቶ ለመቆጠሩ ግን ምንም ምሳሌ የለም (R.T. Beckwith, "The Day, Its Divisions and Its Limits, in Biblical Thought," *EvQ* 43 [1971]: 218-227.

## የጴጥሮስና የያዕቆብ መጠራት

እንድርያስ ሄዶ ለወንድሙ ለጴጥሮስ፣ «መሲሑን አገኘነው» ብሎ ነገረው (ዮሐንስ «መሲሕ» የሚለውን የዕብራይስጥ ቃል፣ «ክርስቶስ» ወደሚለው አቻ የግሪክ ቃል ተርጉሞታል):: እንደ ልማዱ እንድሪያስ ጴጥሮስን ወደ ኢየሱስ አመጣው (ዮሐ 6÷8፤ 12÷22 ጋር ያነ)::

ቃል በቃል ሲወስድ ቁ 41፣ «በመጀመሪያ የገዛ ወንድሙን ስምዖንን አገኘው» ይላል:: እንድሪያስ ሌላ ሰው ስለ ማግኘቱ አልተነገረንም:: ምናልባትም ዮሐንስ ለማለት የፈለገው ወንድሙን በማምጣት የመጀመሪያው እንድርያስ ሲሆን፣ ዮሐንስ ግን ወንድሙን ለማምጣት ሁለተኛው መሆኑን መግለጽ ሳይሆን አይቀርም:: በሌላ አነጋገር እንድርያስ ሄዶ ወንድሙ ጴጥሮስን አመጣ፤ ዮሐንስም ወንድሙን ያዕቆብን አመጣ ማለት ነው:: ይህ አገላለጽ በኋላ የተጠሩት አራት ዓሣ አጥማጆች ጴጥሮስ፣ እንድርያስ፣ ያዕቆብና ዮሐንስ (ማቴ 4÷18-22፤ ሉቃ 5÷1-11) እንዲሁም የኢየሱስ የቅርብ ደቀ መዛሙርት የተጠሩበትን ሁኔታ ይገልጻል::

ኢየሱስ ጴጥሮስን ባገኘው ጊዜ፣ «ኬፋ» የሚል አዲስ ቅጽል ስም ሰጠው፤ የስሙም ትርጉም «ዐለት» ማለት ነው:: ከከሃዲነት ወደ ታላቅ ሰባኪነት እስከ ተለወጠበት ከትንሣኤው በኋላ እስካለው ወቅት በስሙ በእውነት ሊጠራበት አይገባውም ነበር:: በዚያን ጊዜ ስሙ ጴጥሮስ የሚለው የተስማማው ይመስላል::

ዮሐ 1÷43-51

[43]በማግሥቱ ኢየሱስ ወደ ገሊላ ለመሄድ ፈለገ፤
ፊልጶስንም አግኝቶ «ተከተለኝ» አለው:: [44]ፊሊጶስም
እንደ እንድርያስና እንደ ጴጥሮስ ሁሉ የቤተ ሳይዳ ከተማ
ሰው ነበር:: [45]ፊልጶስ ናትናኤልን አግኝቶ፣ «ሙሴ በሕግ
መጻሕፍት፣ ነቢያትም ስለ እርሱ የጻፉለትን የዮሴፍን ልጅ
የናዝሬቱን ኢየሱስን አግኝተነዋል» አለው::



[46]ናትናኤልም፣ «ከናዝሬት በጐ ነገር ሊወጣ ይችላልን?» አለ:: ፊልጶስም፣
«መጥተህ እይ» አለው:: [47]ኢየሱስም፣ ናትናኤል ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ፣ «እነሆ
ተንኰል፣ የሌለበት እውነተኛ እስራኤላዊ» አለ:: [48]ናትናኤልም፣ «እንዴት አወቅኸኝ?»
ሲል ጠየቀው:: ኢየሱስም፣ «ከበለስ ዛፍ ሥር ሳለህ፣ ገና ፊልጶስ ሳይጠራህ አየሁህ»
ሲል መለሰለት:: [49]ናትናኤልም መልሶ፣ «ረቢ! አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ፤ አንተ
የእስራኤል ንጉሥ ነህ» አለ:: [50]ኢየሱስም፣ «ያመንኸው ከበለስ ዛፍ ሥር አየሁህ
ስላልሁህ ነውን?» ገና ከዚህ የሚበልጥ ነገር ታያለህ አለው፤ [51]ጨምሮም፣ «እውነት
እላችኋለሁ፣ ሰማይ ተከፍቶ የእግዚአብሔርም መላእክት በሰው ልጅ ላይ ሲወጡና
ሲወርዱ ታያላችሁ» አለው::

## የፊልጶስና የናትናኤል መጠራት

ፊልጶስ ከአንድ ቀን በፊት ኢየሱስን መከተል የጀመሩት የአራቱ ዓሣ አጥማጆች (ጴጥሮስ፣ እንድርያስ፣ ያዕቆብና ዮሐንስ) ጓደኛ ሳይሆን እንደማይቀር ይታሰባል:: እርሱም ቢሆን፣ ከትንሿ የዓሣ አጥማጆች መንደር ከቤተ ሳይዳ ነበር:: እንደ ገና ወደ ገሊላ በመመለስ ላይ እያሉ ኢየሱስ ፊልጶስንም ጠራው:: ከሐዋርያቱ ሁሉ የግሪክ ስም የነበራቸው ፊልጶስና እንድርያስ ብቻ መሆናቸው የሚገርም ነው (ሔንድሪክሰን ገጽ 108):: በዮሐንስ 12÷20-22 እንደምንመለከተው ከኢየሱስ መስማት ፈልገው የነበሩ ግሪኮች እነዚህ ሁለቱን ለምን መጥተው እንዳናገሩ ይህ ሁኔታ ሊገልጽ ይችላል::[9]

መረዳት እንደሚለው ኢየሱስ ፊልጶስን በጠራበት ጊዜ ከከተማ እየወጣ እንዳልነበር ግልጽ ይመስላል:: ፊልጶስ ሄዶ ናትናኤልን ለማግኘት በቂ ጊዜ ነበረው::[10] የሚያደናግር ግብዣ በማቅረብ ሊያጓጓው ሞከረ::

---

[9] የሐዋርያቱ ዝርዝር ካለበት ውጪ (ማቴ 10÷3፤ ማር 3÷18፤ ሉቃ 6÷14 እና ሐሥ 1÷13) ፊልጶስ በሌሎች ሦስት ሁኔታዎች ስሙ ተጠቅሷል፤ ዮሐንስ 6÷5፣7፤ 12÷21-22 እና 14÷8-9::

[10] ናትናኤል ሦስቱ ተነፃፃሪ ወንጌሎች በርተሎሜዎስ እያሉ የሚጠሩት ሰው ሳይሆን አይቀርም:: ለዚህ አራት ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል:: (1)

ሙሴ የጻፈለትን መሲሕ ማግኘታቸውን ተናገረ:: የፊልጶስ አነጋገር መጓጓትን ሊያነሳሳ፣ የመቆጣት አዝማሚያን ግን ሊቀንስ በሚችል መልክ በጥንቃቄ የተቀናበረ ነበር:: ይህም ማለት የዓረፍተ ነገሩ መጀመሪያ፣ «መሲሕ» የሚለው ሲሆን የመጨረሻው ቃል ደግሞ «ናዝሬት» የሚል ነበር:: ሆኖም ኢየሱስ ከናዝሬት መሆኑን ናትናኤል በዋዛ አልነበረም የተመለከተው:: ከዚያ ምንም ዓይነት መልካም ነገር ይገኛል ብሎ አያምንም ነበር:: ምናልባትም በተራራማው ገሊላ ምድር ስለምትገኘው ይህች ትንሽ ከተማ በዘመኑ የነበረውን የንቀት አስተሳሰብ እያንጸባረቀ ሊሆን ይችላል:: የገሊላ ሰዎች ግን ናዝሬትን በንቀት ዓይን ይመለከቷት እንደ ነበር ምንም ማስረጃ የለም:: ምንም እንኳ ናትናኤል፣ «ተንኰል» የሌለበት ቢሆንም (ቍ 47) በዚያን ወቅት ግን ወደ ሰሜን ጥቂት ኪሎ ሜትሮች ርቀት ላይ ትገኝ በነበረችው በእርሱ ከተማ በቃና እና (ዮሐ 21፡2) በናዝሬት መካከል የነበረውን በአንባቢው የታወቀ ፉክክር እየገለጠ ነበር:: በመጨረሻ ግን ፊልጶስ «መጥተህ እይ!» የሚል አጭር ጥሪ በማቅረብ ከኢየሱስ ጋር እንዲገናኝ ናትናኤልን አባበለው::[11]

ናትናኤል ከኢየሱስ ጋር ያደረገው ንግግር አስደናቂ ነበር:: በአንድ አይሁዳዊ ጆሮ ማድመጥ ብንችል ኖሮ የብሉይ ኪዳኑ ያዕቆብ ንግግር ሲያስተጋባ እናደምጥ ነበር:: ናትናኤል ወደ ኢየሱስ ሲመጣ ተንኰል የሌለበት እውነተኛ እስራኤላዊ በማለት ነበር የጠራው:: ትሩዲንገር እንዲህ ይላል:-

ናትናኤል የቤተሰብ ስሙ ነበር፤ ስለዚህም ሌላ ስም ሊኖረው የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል:: (2) ዮሐንስ በርተሎሜዎስ የሚለውን ስም አያነሣም፤ ሦስቱ ተነፃፃሪ ወንጌሎችም ናትናኤል የሚለውን ስም አያነሡም:: (3) ሦስቱ ተናፃፃሪ ወንጌሎች የሐዋርያቱን ስም በሚዘረዝሩበት ክፍል በርተሎሜዎስን የምናገኘው ከፊልጶስ ቀጥሎ ነው:: (4) በዚህ ምዕራፍ የምናገኛቸው ደቀ መዛሙርት ሁሉ ሐዋርያት ሆነዋል::

[11] ማቴዎስና ሉቃስ ኢየሱስ በቤተ ልሔም የነበረውን ትሑት ጅማሬ እንደሚነግሩን ሁሉ፣ ዮሐንስም በናዝሬት የነበረውን ትሑት ጅማሬ ይገልጻል::



> በትውፊታዊ የያዕቆብና የኤሳው ታሪክ ያዕቆብ 'አታላይ' ለሚለው ቃል አቻ ሆኖ ነበር የቀረበው:: በዘፍጥረት 27፥36 ኤሳው፣ «ይህ ሰው ያዕቆብ መባሉ ትክክል አይደለምን? እኔን ሲያታልለኝ ይህ ሁለተኛ ጊዜው ነው» በማለት ሲያማርር እንመለከታለን:: ይሁን እንጂ ይኸው አታላዩ ያዕቆብ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ድነት ባዘጋጀው ዕቅድ ቁልፍ ሰው ሆነ በኋላም በታሪኩ ውስጥ እግዚአብሔር እንደ ገና «እስራኤል» ብሎ ጠርቶታል:: ስለዚህም የኢየሱስ ሰላምታ፣ «ከያዕቆብ አታላይነት ቀንጣት እንኳ የሌለበት እስራኤላዊ!» በሚል መልኩ እንደተናገረ አድርጎ መግለጽ ይቻላል:: ናትናኤልን ያስደነገጠውም ይኸው ነበር::[12]

ኢየሱስ ስላወቀው ናትናኤል በጣም ተገርሟል:: ኢየሱስ ግን፣ «ይህ ምንም ማለት አይደለም፤ እንዲያውም እስቲ አስበው ገና ፊልጶስ ሳይጠራህ ከበለስ ዛፍ ሥር ሆነህ አይቼሃለሁ!» በማለት በዝርዝር ነገረው:: ይህ ደግሞ ናትናኤልን ይበልጥ ስላስደነቀው ኢየሱስ የእግዚአብሔር መሲሕ መሆኑን መሰከረ:: ከእግዚአብሔር ወይም ከመልአክ መገለጥ ሳያገኝ እንዲህ ያለ ምስክርነት ሲቀርብ እሱ የመጀመሪያው ሰው ነበር:: ታዲያ አስገራሚው ነገር ምንድነው? ከበለስ ዛፍ ሥር እያለ ኢየሱስ አይቶታል? ለፓለስቲና ሰዎች ችፍግ ያለው የበለስ ዛፍ ቅጠል ተወዳጅ የዕረፍት ቦታ ነበር:: ስለዚህም ለማሰላሰልና ቶራን ለማጥናት እንዲህ ወዳለው ቦታ ይሄዱ ነበር *(Ecclesiastes Rabbah 5:15)::* ከዚህም በላይ የበለስ ዛፍ የእስራኤልና የመሲሑ ትእምርት (ምሳሌ) ነበር (ሚክ 4፥4፤ ማቴ 24፥32፤ ሉቃ 13፥6-9):: ምንም እንኳ ግምታችንን ብቻ የምንሰነዝር ብንሆንም ኢየሱስ የተናገረው መጀመሪያ ከተረዳነው የጠለቀ ትርጉም ሊኖረው እንደሚችል ማሰብ

[12] L.P. Trudinger, "An Israelite in Whom There Is No Guile: An Interpretive Note on John 1:45-51," *EvQ* 54 (Apr 1982): 117-120.

**ይቻላል**:: ምናልባትም ናትናኤል መጽሐፍ ቅዱስን እያጠና እንደነበረ እንዲሁም የያዕቆብን ታሪክ መሠረት አድርጐ ስለ መሲሑ እያሰላሰለ እንደ ነበር ኢየሱስ ሳያውቅ አይቀርም:: ያም ሆነ ይህ በጣም ግልጽ የሆነው እውነት ናትናኤል ከልቡ መሲሑን ይናፍቅ እንደ ነበር ኢየሱስ ተረድቶአል:: ኢየሱስ ወደ ናትናኤል አእምሮ ወይም አስተሳሰብ ውስጥ ዘልቆ ገብቶ ነበር፤ ይህ ደግሞ ናትናኤልን በኢየሱስ እንዲያምንና የእርሱ ተከታይ እንዲሆን አደረገው::

እንደ ገና ኢየሱስ ፊልጶስንና ናትናኤልን ወደ ኋላ ወደ ያዕቆብ ወሰዳቸው:: መላእክት ሲወጡና ሲወርዱ እንደሚያዩ ነገራቸው:: ይህ በኢየሱስ አገልግሎት ዘመን ቃል በቃል ይፈጸማል ብለን የምንጠብቅ ከሆነ ምንም ነገር አናገኝም:: የያዕቆብ መሰላል በጣም የጠለቀ ትርጉም አለው:: የጠቅላላ ሐሳቡን ዐውድ ለማየት ዘፍጥረት 28ን መመልከት ይኖርብናል:: ያዕቆብ ሕልም ውስጥ እያለ እግዚአብሔር ያዕቆብ ያይ በነበረው ሕልም መካከል፣ «የምድርም ሕዝቦች ሁሉ በአንተና በዘርህ አማካይነት ይባረካሉ» በሚለው ቃል ላይ ያተኮረ የበረከት ተስፋ ነገረው:: ኢየሱስ የዚህ የ2000 ዓመት የሆነው ራእይ ፍጻሜ ነበር:: ያ ቦታ ለናትናኤል፣ «ቤቴል» ነበር ማለትም ይቻላል (ዘፍ 28÷19 ጋር ያነ)::

በዚህ ምንባብ ኢየሱስ፣ «የእግዚአብሔር በግ»፣ «የእግዚአብሔር ልጅ»፣ «መሲሑ» እና፣ «የእስራኤል ንጉሥ» ተብሎአል:: ይሁን እንጂ ኢየሱስ ራሱን፣ «የሰው ልጅ» ነበር የሚለው:: ይህ መጠሪያ የተወሰደው ከዳንኤል 7÷13-14 ካለው ነበር:: ኢየሱስ ስለ ራሱ ሲናገር 76 ጊዜ ያህል ይህንን ስም ተጠቅሞአል:: «የሰው ልጅ» የሚለው መጠሪያ ኢየሱስ ከሰው ልጆች ጋር ያለውን ዝምድና ያጐላል:: ስለሆነም ከዮሐንስ 1÷1 እስከ 1÷51 ባለው የምንመለከተው እግዚአብሔር በሙላት ወደ ምድር መውረዱንና የሰውን ልጅ ሥጋ መልበሱን ነው::



**§ 29**
**ሰርግ በቃና**
**(ዮሐ 2÷1-11)**

እስከዚህ እስከደረስንበት ድረስ ያለው ትዕይንት እንድናመነታ የሚያደርገን ነው:: ብዙ ያልተመለሱ ጥያቄዎች አሉ፤ የማርያም ድርሻ ምን ነበር? እነዚህ ባልና ሚስት እነማን ነበሩ? ከዚያ በፊት ኢየሱስ ያውቃቸው ነበር? እንዴት? ወዘተ የዓይን ምስክር እንደ መሆኑ መጠን ዮሐንስ ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ መስጠት ይችል ነበር:: ይሁን እንጂ ትኩረቱን ኢየሱስ ላይ ማድረግን ነበር የመረጠው:: በዚያ ሠርግ ግብዣ ዋናው እንግዳ እርሱ ነበር፤ እንደ እውነቱ ከሆነም ፋይዳ ሊሰጠው የሚገባውም እርሱ ነበር::

**ዮሐ 2÷1-5**

1በሦስተኛው ቀን፣ በገሊላ አውራጃ በቃና ከተማ
ሰርግ ነበር፤ የኢየሱስም እናት በዚያ ነበረች፤ 2ኢየሱስና
ደቀ መዛሙርቱም ወደ ሰርጉ ተጠርተው ነበር:: 3የወይን
ጠጅ ባለቀ ጊዜም የኢየሱስ እናት፣ «የወይን ጠጅ እኮ
አለቀባቸው» አለችው::
4ኢየሱስም «አንቺ ሴት ሆይ፣ ምን አድርግ ትይኛለሽ? ጊዜዬ ገና አልደረሰም»
አላት:: 5እናቱም በዚያ የነበሩትን አገልጋዮች፣ «የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ» አለቻቸው::

ከሰርግ ግብዣ የበለጠ ምን ደስ የሚል ነገር ይኖራል? ኢየሱስ የመጀመሪያውን ተአምር ለማድረግስ ከዚያ የተሻለ ቦታ ምን ሊኖር ይችላል? ኤደርሼይም (1:345) ትክክል ከሆነ ይህ ረቡዕ ቀን የተደረገ የልጃገረድ ሰርግ መሆኑ ነው:: የሰርጉ ግብዣ ምሽት ላይ ይጀምርና ሰባት ቀን ይቆያል (ዘፍ 29÷27፤ መሳ 14÷12):: ከዮርዳኖስ እስከ ቃና[13] ሦስት ቀን ከተጓዙ በኋላ ኢየሱስ ከመጀመሪያዎቹ ስድስት ደቀ

[13] ዮሐንስ የኢየሱስን አገልግሎት መጨረሻ ሳምንት ዝርዝር ጉዳዮች እንዳቀረበ ሁሉ (ዮሐ 12÷1) እዚህም ላይ የአገልግሎቱን መጀመሪያ ሳምንት ዝርዝር ጉዳይ አቅርቧል (ዮሐ 1÷29፣35፣43፤ 2÷1)::

መዛሙርት ጋር ሠርጉ ላይ ተገኘ:: ቃና የሚባለው ቦታ የት እንደ ሆነ በስተ ሰሜን ከናዝሬት ከስድስት እስከ ሃያ ዘጠኝ ኪሎ ሜትር ድረስ የሚገኙ ብዙ ቦታዎች ቃና በሚል ስም ይታወቃሉ:: ከእነዚህ መሐል የትኛውም ቦታ ቢሆን ለማርያም ቅርብ ስለ ነበር በሠርጉ ዝግጅት ላይ እንድትገኝ ጥሪ ሊቀርብላት ይችላል:: ከዚህም በላይ ወደ ቃና ሲሄድ ኢየሱስ ናዝሬት ላይ ቆይታ ለማድረግ ሰፋ ያለ ጊዜ ይኖረዋል::

ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ግብዣው ላይ እንዲገኝ ኢየሱስ ተጋብዞ ነበር:: ምናልባትም የጋበዘው አገሩ ቃና የነበረው ናትናኤል ሊሆን ይችላል:: ምናልባትም የሙሽሮቹ ዘመድ ወይም የቅርብ ወዳጅ ሊሆንም ይችላል:: ወይም ደግሞ ኢየሱስ ስለ ሰርጉ የሰማው ናዝሬት ላይ ቆይታ ባደረገ ጊዜ ሊሆን ይችላል::

ለግብዣው የተዘጋጀው ወይን በማለቁ የገጠማቸውን አስደንጋጭ ሁኔታ ማርያም ለኢየሱስ ነገረችው፤ ይህ ውርደት ከመሆኑ በላይ ክስ እንዲመሠረትባቸው እንኳ ምክንያት ሊሆን የሚችል ነበር::[14] ምናልባትም ማርያም የግብዣ ዝግጅቱን በመቆጣጠር ተሳትፎ ሳታደርግ አልቀረችም፤ ስለ ወይኑ ሁኔታ ያወቀችው በዚህ ምክንያት ሊሆን ይችላል::[15] ወይም ደግሞ ወይኑ ያለቀው ከኢየሱስ ጋር ተጨማሪ እንግዶች በመምጣታቸው ሊሆን ይችላል:: ኢየሱስ ምንም ነገር እንዲያደርግ ሳትጠይቅ ማርያም አንድ ነገር እንዲያደርግ ነገረችው::

በመሠረቱ ማርያም ኢየሱስን የጠየቀችው ተአምር እንዲያደርግ አልነበረም:: ምናልባት የሰርጉን ግብዣ ካዘጋጀው ቤተ ሰብ አንድ ሴት ወደ ማርያም መጥታ ካሉበት አስደንጋጭ ሁኔታ መውጣት የሚችሉበት መንገድ ካለ እንድትነግራቸው ጠይቀዋት ይሆናል:: በዚህ ጊዜ ማርያም እንደ አማላጅ ችግሩን ለኢየሱስ ነገረችው:: ሊረዳቸው ከቻለ ችግሩን

[14] K.T. Cooper, "The Best Wine: John 2:1-11," *WTJ* 41 (Spr 1979): 364-380.

[15] ምንም እንኳ ቤተ ሰቡ በሙሉ (ልጆቹ) በሰርጉ ዝርዝር ዝግጅት እናታቸውን እየረዱ እዚያ ቢሆኑም (ዮሐ 2÷12) ታሪኩ ውስጥ ዮሴፍ አልተጠቀሰም:: ምናልባትም በዚህ ጊዜ ዮሴፍ ሞቶ ይሆናል::



ከማቃለል በተጨማሪ ለሥጋ ዘመዶቹም ማኅበረ-ሰባዊ ክብሬታ ያስገኝላቸዋል:: እንደ ፓለስቲናዊት ሴት ማርያም የምትገነዘበው እንዲህ ያለ ጥያቄ ማቅረብ የቤተ ሰብነት መብቷ መሆኑን ነው:: ይሁን እንጂ ኢየሱስ ቤተ ሰቡ ክብር ለማግኘት በሚያደርገው መፍጨርጨር መወሳሰብ አልፈለገም:: ይልቁንም በመሲሐዊ አገልግሎቱ አዲስ ቤተ ሰብ እየመሠረተ ነበር:: ዊልያምስ የተባለ ሰው ኢየሱስ፣ «ጊዜዬ ገና አልደረሰም» በማለት የተናገረውን ቃል፣ «ይህ ለእኔ ጊዜው አይደለምን?»[16] ማለቱ እንደ ነበር አመልክቷል:: ስለዚህም ይህን ተአምር በማድረግ ኢየሱስ እናቱ ለጠየቀችው ቀና ምላሽ ሰጥቷል ራሱንም ከቤተ ሰቡ ለየ::

ኢየሱስ ማርያም ላቀረበችው፣ «ጥያቄ» አይሆንም የሚል መልስ አለመስጠቱ ግልጽ ነበር:: ይሁን እንጂ ጥያቄውን ለመጠየቅ ያነሳሳትንና እየጠበቀች የነበረውን ጉዳይ እየመዘነ ነበር:: ለማርያም የሰጣት አጭር መልስ ሦስት ክፍሎች አሉት:: በመጀመሪያ፣ እንደ አንዲት «ውድ ሴት» ብሎ ጠራት እንጂ «እማዬ» በማለት አልነበረም ያናገራት:: «እማማ» የማለት ያህል ጨዋ አጠራር ቢሆንም (ዮሐ 19÷26 ጋር ያነ) በመካከላቸው ያለውን ቀረቤታ የሚያመለክት ነበር:: በዚህ ጊዜ እንደ «ልጅ» ልትመራው ሳይሆን ክርስቶስ እንደመሆኑ ፈቃዱን ልትቀበል ይገባት ነበር:: ከዚያ በኋላ ኢየሱስ «እኔን እዚያ ውስጥ የምታስገቢኝ ለምንድነው?» አለ:: በመሠረቱ ይህ በግርድፉ «ይህ ለእኔ ምኔ ነው?» የሚል ትርጉም ያለው የተለመደ የዕብራይስጥ የአነጋገር ፈሊጥ ነበር:: በመሠረቱ ኢየሱስ በመካከላቸው ስላለው ዝምድና በጥንቃቄ እንድታስብ ማርያምን መጠየቁ ነበር:: በመጨረሻም፣ ጊዜው እንዳልደረሰ ተናገረ:: በሌላ አነጋገር፣ «ማርያም ሆይ፣ ገና ስለሆነ በአደባባይ መገለጤን አትጠብቂ» ማለቱ ነበር (ዮሐ 7÷6፣9 ጋር ያነ):: የኢየሱስ የሕይወት

[16] Ritva H. Williams, "The Mother of Jesus at Cana: A Social Science Interpreation." *CBQ* 59 (1997): 679-692.

ጉዞ ቀድሞውኑ የተወሰነ ነበር:: በትክክለኛው ጊዜ ከመስቀል ላይ ሞቱ ይደርስ ዘንድ በሰው አካል መገለጡና (ገላ 4÷4) አገልግሎቱ በጥንቃቄ የታቀደና ቀጠሮ የተያዘለት ነበር:: ዮሐንስ፣ «ሰዓት» እና፣ «ጊዜ» የተሰኙትን ቃላት መጠቀሙ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ለኢየሱስ በተለይም ሞቱን በሚመለከት ዕቅድ የነበረው መሆኑን ነው (ዮሐ 2÷4፤ 7÷6፣8፣30፤ 8÷20፤ 12÷23፣27፤ 13፥1፤ 17፥1) ነበር::

ማርያም፣ የሰጠችው ምላሽ ችግሩን በመፍታት ረገድ ኢየሱስ አንድ ነገር እንደሚያደርግ እየጠበቀች እንደ ነበር ያሳያል:: ምናልባትም በንግግሩ ድምፀት፣ በአመለካከቱ ለእኛ ግልጽ ባልሆነ ሁኔታ እንደሚረዳቸው ነግሯት ሊሆን ይችላል:: ይሁን እንጂ፣ ማርያም የሰጠችው ትእዛዝ ቢኖር ይሄ ብቻ ነው «የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ»:: ይህን ማለቷ ድንቅ ነው!

ዮሐ 2÷6-10

[6]በአይሁድ የመንጻት ሥርዓት መሠረት፣ ከሰባ
ሰምንት እስከ አንድ መቶ ሀሥራ ሰምንት ሊትር የሚይዙ
ከድንጋይ የተሠሩ ስድስት ጋኖች በዚያ ነበሩ:: [7]ኢየሱስ
አገልጋዮቹን፣ «ጋኖቹን ውሃ ሙሏቸው» አላቸው፤
እነርሱም፣ ጋኖቹን እስከ አፋቸው ሞሏቸው::
[8]እርሱም፣ «ከላይ ቀድታችሁ ለድግሱ ኀላፊ ስጡት» አላቸው:: እነርሱም
እንዳዘዛቸው አደረጉ::
[9]የድግሱ ኀላፊም ወደ ወይን ጠጅ የተለወጠውን ውሃ ቀመሰ፤ ሆኖም ከየት
እንደ መጣ አላወቀም፤ ውሃውን የቀዱት አገልጋዮች ግን ያውቁ ነበር:: እርሱም
ሙሽራውን ለብቻው ጠርቶ፣ [10]«ሰው ሁሉ በመጀመሪያ የሚያቀርበው ጥሩውን ወይን
ጠጅ ነው፤ እንግዶቹም ብዙ ከጠጡ በኋላ መናኛውን የወይን ጠጅ ያቀርባል፤ አንተ
ግን ጥሩውን የወይን ጠጅ እስከ አሁን አቆይተሃል» አለው::

ኢየሱስ ለመንጻት ሥርዓት የሚውል ውሃ የሚቀመጥባቸውን ስድስት የድንጋይ ጋኖች አመለከተ:: እያንዳንዳቸው ከአርባ እስከ ስድሳ



ሊትር ይይዙ ነበር:: ይህም በጠቅላላው ከሁለት መቶ አርባ እስከ ሦስት መቶ ስድሳ ሊትር ወይን ጠጅ መሆኑ ነው:: በጊዜው የነበረውን ችግራቸውን ከማስወገድም ባሻገር ይህ የተትረፈረፈ የጋብቻ ስጦታ ይሆናል:: ኢየሱስ እስከ አፋቸው ድረስ ጋኖቹ ውሃ እንዲሞሉ አዘዘ:: ይህ የሚያመለክተው፣ (1) ግብዣው የተትረፈረፈ መሆኑንና፣ (2) ምንም የጐደለ ነገር አለመኖሩን፣ (3) ጋኖቹ ለመንጻት ጉዳይ የሚውሉ ምቋሸናቸው ውሃ እንጂ ወይን ጠጅ አልያዙም:: ስለሆነም ውስጣቸው ምንም የወይን ጭላጭ ሊኖር አይችልም::

ጋኖቹ ውስጥ ከነበረው፣ «ውሃ» ተቀድቶ፣ «ለድግሱ ኀላፊ» ተሰጠው፤ ይህ ሰው ሦስት ኀላፊነቶች ነበሩበት፤ (1) ለሰዎች ሊቀርብ የሚገባ መሆኑን ለማጣራት ማንኛውንም የምግብ ዓይነትና ወይን ጠጅ መቅመስ፣ (2) ግብዣው ሥርዓት በጠበቀ ሁኔታ እንዲጠናቀቅ ማድረግ፣ (3) የግብዣ ሥነ ሥርዓቱን መምራት:: ይህ ሰው በምንም መልኩ የኢየሱስን ርዳታ የሚፈልግ አልነበረም:: ወደ ወይን ጠጅ የተለወጠውን ውሃ ሲቀምስ የሚያረካ እንደ ነበር አወቀ:: «ጥሩ»ነቱ በማስከር ዐቅሙ ላይ ሳይሆን በጣዕሙ ላይ ነበር:: እንዲያውም የፓለስቲና ወይን ጠጅ በጣም ቀጭን በመሆን ነበር የሚታወቀው:: ምንም እንኳ አንድ ሰው ይህን ጠጥቶ መስከር ቢችልም ከዚህ ይልቅ የሚበልጥ ኀይል ያላቸው የአልኮል መጠጦች ነበሩ:: ወይን ጠጅ ከማንኛውም ምግብ ጋር በአንድነት የሚቀርብ መጠጥ ነበር:: «የድግሱ ኀላፊ» ሙሽራውን ለብቻው ጠርቶ እስኪያመሰግነው ድረስ ወይን ጠጁ በጣም ጥሩ ነበር:: በለተምዶ እንደሚደረግ ጥሩ የሆነው የሚታደለው መጀመሪያ እንጂ በኋላ አልነበረም::

ዮሐ 2÷11

[11]ኢየሱስም ይህን የታምራዊ ምልክቶቹ
መጀመሪያ በገሊላ አውራጃ በቃና ከተማ አደረገ፤
ክብሩንም ገለጠ፤ ደቀ መዛሙርቱም በእርሱ አመኑ::

ኢየሱስ ብዙ ምልክቶችና ድንቆችን አድርጓል። ይህ ዮሐንስ ከመረጣቸው ሰባቱ የመጀመሪያው ነበር (ቍ 11)። እንደ ሌሎቹ ስድስት ሁሉ ይህም በግል ለደቀ መዛሙርቱ ለማሳየት የተደረገ ተአምር ነበር። ዮሐንስ የመዘገባቸው ሰባ «ምልክቶች» ዓላማ ኢየሱስ እንደ እግዚአብሔር ልጅ ያለውን ሥልጣን ለማረጋገጥ እንጂ ኃይሉን ለማሳየት አልነበረም።

እነዚህ ምልክቶች የኢየሱስ ማንነት ከማረጋገጥ ወይም በሕይወቱ የተፈጸሙ አንዳንድ ሁኔታዎችን ከማጽናት የበለጠ ፋይዳ አላቸው። ብሉምበርግ የሚናገረው ትክክል ከሆነ እንደ ምሳሌዎቹ ሁሉ ኢየሱስ ያደረጋቸው ተአምራቶችም የእግዚአብሔር መንግሥት ተለዋጭ ዘይቤ ናቸው። በሌላ አነጋገር በተግባር የታዩ ምሳሌዎች ነበሩ።[17] እንዲህ ሲባል ታዲያ በታሪክ ውስጥ በእውነት የተፈጸሙ አይደሉም ማለት አይደለም። መለኮታዊ አሠራርን አጠያያቂ አድርጎ የመመልከት አዝማሚያ ምንም ዓይነት ሳይንሳዊና ፍልስፍናዊ ሙግት ሊቀርብበት የማይችል መሆኑን በቅርቡ ታላላቅ ምሑራን አመልክተዋል። የሚያሳየው መሲሐዊ አገልግሎቱ ምን ማለት እንደ ነበር ያመለክተዋል። የሚያሳየው የመሲሐዊ አገልግሎቱ ምሥጢር ምን እንደ ነበር ያመለክታሉ ብሎ ያሰባቸውን የተወሰኑ የኢየሱስ ተአምራቶችን ለመግለጽ ዮሐንስ መምረጡን ነው።

ስለዚህም፣ «ይህ ምልክት የሚያመለክትው ምንድነው?» ብለን መጠየቅ አለብን። ቱሴንት አንዳንድ ጠቃሚ ሐሳቦችን አቅርቧል።[18] በመጀመሪያ፣ በሰርጉ ግብዣ ላይ የነበረው ወይን ጠጅ የሚመጣውን መንግሥት ያመለክታል። በብሉይ ኪዳን ውስጥ በወይን ተመስሎአል

[17] C.L. Blomberg, "New Testament Miracles and Higher Criticism: Climbing up the Slippery Slope," *JETS* 27/4 (Dec 1984): 425-438.
[18] S.D. Toussaint, "The Significance of the First Sign in John's Gospel," *BibSac* 134 (Jan 1977): 45-51.



(ኢሳ 25፥6፤ 55፥1፤ ኢዩ 3፡18፤ አሞ 9፥13)። በአዲስ ኪዳንም በግብዣ በተለይም በሰርግ ግብዣ ተመስሎአል (ማቴ 8፡11፤ 22፡1-14፤ ሉቃ 13፡29፤ 14፥15-24፤ ራእ 19፡7-9)። አዲስና ከአሮጌው መንግሥት የተለየ ይሆናል (ማር 2፡21-22 ጋር ያነ)። ሁለተኛ፣ ኢየሱስ በጣም ልቆ ሄዷል። ከሚያስፈልገው የበለጠ ወይን ጠጅ አቅርቦላቸዋል። ይህ መትረፍረፍ ደግሞ የእግዚአብሔር መንግሥት መገለጫ ነው (ፊልጵ 4፡7፤ ሮሜ 5፡20፤ 1ጴጥ 1፡8፤ ከአሞ 9፡13 ጋር ያነ)። ስለዚህም ማርያም ባቀረበችው ጥያቄ መሠረት በአደባባይ ሳይሆን በግል ለደቀ መዛሙርቱ ታምራታዊ አገልግሎቱን መጀመሩን አበሠረ። ይህን በማድረጉ የሚመጣው መንግሥት ምን እንደሚመስል ሥዕላዊ መግለጫ ሰጠ። እንዲህ የደስ ደስ ያለውና ፈንጠዝያ የታየበት ሰርግ የተደረገው በሦስተኛው ቀን መሆኑ ራሱ የተለየ ግምት የሚሰጠው ነው።

### § 30
### ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ቅፍርናሆም መሄዳቸው (ዮሐ 2፥12)

12ከዚህ በኋላ ከእናቱ ከወንድሞቹና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ቅፍርናሆም ወረደ፤ በዚያም ጥቂት ቀን ተቀመጡ።

ኢየሱስ ከኮረብታዋ ቃና የተከተሉት ስድስት ደቀ መዛሙርት መናኸሪያ ወደ ነበረችው የባሕር ዳርቻዋ ገሊላ ሄደ። ከስድስቱ ጋር የኢየሱስ አራት ወንድሞችና እናቱም አብረው ነበሩ። እኅቶቹ አለመጠቀሳቸው ምናልባት ባለ ትዳር ሳይሆኑ እንዳልቀሩና ከዚህም የተነሣ በተለያዩ ኀላፊነቶች በመያዛቸው ሊሆን እንደሚችል ሊያመለክት ይችላል።

የጌታ ወንድሞች ዘጠኝ ጊዜ ተጠቅሰዋል። ስድስት ጊዜ በቀጥታ ከማርያም ጋር በተያያዘ ሲሆን (ማቴ 12፥46፤ 13፥55፤ ማር 3፥32፤ 6፥3፤ ሉቃ 8፥19-20፤ ዮሐ 2፥12)፣ ሦስት ጊዜ ግን ከእርሷ ጋር

በተያያዘ ሁኔታ አልነበረም (ዮሐ 7፥3፣5፣10፤ 1ቆሮ 9፥5፤ ገላ 1፥19):: እነዚህ ልጆች የእኅት ወይም የወንድም፣ ወይም ደግሞ ዮሴፍ ቀደም ሲል ከነበረ ትዳሩ የወለዳቸው ላለመሆናቸው ይህ ጥሩ ማመላከቻ ነው:: መስቀል ላይ በነበረ ጊዘ (ዮሐ 19፡25-27) ኢየሱስ ማርያምን በአደራ ለዮሐንስ መስጠቱ ወንድሞቹ ለእርሱ ደንታ ያልነበራቸው መሆኑን ወይም በጣም ትንንሾች በመሆናቸው የዮሐንስን ያህል ማርያምን መርዳት አለመቻላቸውን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል::

ማክጋርቪ (በገጽ 120) እንደሚለው ይህ አጭር የቅፍርናሆም ጉብኝት በርካታ ነገሮችን ያሳያል፤ (1) በቃና ኢየሱስን ሊያገኘው ፈልጎ የነበረው ትልቅ ሰው ከእርሱ ጋር እንዴት መቀራረብ እንደቻለ ያሳያል (ዮሐ 4፡46-54):: (2) ኢየሱስ ከናዝሬት ወደ ፊት «የአገልግሎቱ ማዕከል» ወደትምሆነው ቅፍርናሆም መንቀሳቀሱን ያሳያል (ማቴ 4፥13፤ 9፡1፤ ማር 2፥1):: በተጨማሪም ኢየሱስ በተከታዮቹ ወቅቶች ናዝሬትን ሊጎበኝ እንደሚችል እንደዚሁም በናዝሬትና በቅፍርናሆም በነበሩ ደቀ መዛሙርቱ የነበረው የ የግንኙነት መጠን የሚያሳይ ሊሆን ይችላል:: (3) ቢያንስ እስከሚቀጥለው ፋሲካ ኢየሱስ ከሥጋ ዘመዶቹ ጨርሶ አለመለያየቱን ሊያሳይ ይችላል::

**§ 31**
**መቅደሱን ለመጀመሪያ ጊዜ ማንጻቱ**
**(ዮሐ 2፥13-22)**

ጥንት እንደ ነበሩት እንደ ኢዮስያስና እንደ ሕዝቅያስ ሁሉ ኢየሱስም የእግዚአብሔርን መቅደስ አነጻ:: ይህ ደግሞ ኢየሱስ መሲሕ መሆኑን ማመልከት የሚችል ቀራጥ እርምጃ ነበር (ሚል 2፥2-3 ጋር ያነ)::[19] የዚህ ሁነት ዋናው የትኩረት አቅጣጫ ኢየሱስና ማንነቱ ላይ የመሆኑን ያህል በመቅደሱና ይከናወን

[19] R.H. Hiers, "Purification of the Temple: Preparation for the Kingdom of God," *JBL* 90 (1971): 82-90.



በነበረው ሕገ ወጥ አሠራር ላይ አልነበረም:: ቃና ከነበረው ሰርግ ጋር በማያያዝ ስናነብ በጥቂቱም ቢሆን ኢየሱስ በሁለቱም ቦታዎች ስለ ነበረው አገልግሎት ፍንጭ እናገኛለን:: በአንድ በኩል የተትረፈረፈ፣ አስደሳች ልግሥና ያለበት መንግሥት ታላቅ መሲሕ ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ በአይሁድ መሪዎች ከተናቀና ከደቀቀ በኋላ በሦስተኛው ቀን ከሙታን የተነሣ መከራን የተቀበለ አገልጋይ ነበር::

አራቱም ወንጌሎች ስለ መቅደሱ መንጻት ጽፈዋል:: ሆኖም ሦስቱ ተነፃፃሪ ወንጌሎች ያስቀመጡት በኢየሱስ አገልግሎት ማብቂያ ላይ እንጂ እንደ ዮሐንስ በመጀመሪያው ላይ አይደለም (ማቴ 21፡12-13፤ ማር 11፥15-17፤ ሉቃ 19፡45-46) ኢየሱስ መቅደሱን ያነጻው ምናልባት አንዴ ብቻ ሊሆን ይችላል፤ ዮሐንስ እዚህ ላይ ያሰፈረው ቅደም ተከተላዊ ሂደቱን በመጠበቅ ሳይሆን ነገረ መለኮታዊ ፋይዳ ስላለው አጽንኦት መስጠት በመፈለጉ ነው:: ከዚህም በላይ በሁለቱ መካከል ግልጽ በሆነ ምክንያት ተመሳሳይነት አለ (ለምሳሌ ያህል ስፍራው፣ እንስሳቱና ገንዘብ መንዛሪዎች):: በርካታ ልዩነቶችም አሉ:: ለምሳሌ ያልህ ፣ በመዝሙር 69፥9 ስላለው ጅራፍ የማበጀቱ እንዲሁም የመቅደሱን መፍረስ ትንቢት አስመልክቶ የሚነግረን ዮሐንስ ብቻ ነው:: ሦስቱ ተነፃፃሪ ወንጌሎች ማንም ዕቃ ተሸክሞ በቤተ መቅደሱ ቅጥር ግቢ ውስጥ እንዳያልፍ ኢየሱስ መከልከሉን ማርቆስ ከሚናገረው በተጨማሪ በኢሳይያስ 56፥7 እና በኤርምያስ 7፥11 የተነገሩትን ትንቢቶች ይጠቅሳሉ:: ይህ ደግሞ ኢየሱስ ቤተ መቅደሱን ያነጻው በእርግጥም ሁለት ጊዜ መሆኑን እንድንቀበል ያደርገናል:: ይህ ድፍረት የሞላበት ተግባር የአደባባይ አገልግሎቱን የመጀመርና የመደምደም አገልግሎት ሰጥቶአል::

የተገኘባቸውን በዓላት መሠረት በማድረግ የኢየሱስን አገልግሎት ዘመን በቅርብ እንድንከታተል የሚረዳን ዮሐንስ ብቻ ነው (1)

የመጀመሪያ ፋሲካ (2፥13)፤ (2) ሁለተኛው ፋሲካ (በቂ ማስረጃ ባይኖርም) (5፥1)፤ (3) ሦስተኛው ፋሲካ (6፥4)፤ (4) የዳስ በዓል (7፥2)፤ (5) የቤተ መቅደስ መታደስ በዓል (10፥22)፤ (6) አራተኛው ፋሲካ (11፥55)። ከዚህም በላይ የመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት ከ26 ዓ.ም. (ሉቃ 3፥1) ምናልባትም ክረምት (fall) ጀምሮ እንደጀመረ መቍጠር ይቻላል። ኢየሱስ የተጠመቀው በዚያው ክረምት ሊሆን ይችላል። አርባ ቀን በምድረ በዳ (ማቴ 4፥2)፤ ሰባት ቀን የመጀመሪያዎቹን ደቀ መዛሙርት በማሰባሰብና በቃና በነበረው ሰርግ በመገኘት አሳልፎአል (ዮሐ 1፥29፤35፤43፤ 2፥1)። ለአጭር ቀናት ቅፍርናሆምን ጎብኝቶ (ዮሐ 2፥12) ከዚያ በኋላ በ15ኛ በኒሳን ወር በ15ኛ ው ቀን በሚውለው (የሚያዝያ ወር መባቻ) ፋሲካ በዓል ላይ ለመገኘት ወደ ኢየሩሳሌም ይገሠግሳል።

ዮሐ 2፥13-17

[13]የአይሁድ ፋሲካም እንደ ተቃረበ፣ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ። [14]በቤተ መቅደሱ አደባባይ ከብቶችን፣ በጎችንና ርግቦችን የሚሸጡ እንዲሁም ተቀምጠው የገንዘብ ምንዛሬ የሚያከናውኑ ሰዎች አገኘ። [15]የገመድ ጅራፍ አበጅቶ በጎችንና ከብቶችን ሁሉ ከቤተ መቅደሱ ግቢ አበረረ፤ የመንዛሪዎችን ገንዘብ በተነ፤ ጠረጴዛቻቸውንም ገለበጠ። [16]ርግብ ሻጮችንም፣ «እነዚህን ከዚህ አስወጧቸው፣ የአባቴን ቤት የንግድ ቤት አታድርጉት!» አላቸው።

[17]ደቀ መዛሙርቱም፣ «ለቤትህ ያለኝ ቅናት ያቃጥለኛል» ተብሎ የተጻፈው ትዝ አላቸው።

*[17]መዝሙር 69፥9*

በአንድ መልኩ ስንመለከተው ይህ የኢየሱስ የአገልግሎት ጅማሬ ንግግር ነበር። በዓሉ ከመድረሱ አንድ ወር ቀደም ብለው የአውራ ጎዳና ሠራተኞች ይሄዱና መንገዶችንና ድልድዮችን ያድሱ ነበር። መንገደኞቹ



ሳያውቁ ላያቸው ላይ እንዳይቆሙና ራሳቸውን እንዳይረክሱ መቃብሮች ቀለም ይቀባሉ (Edersheim I:367)። ኢየሱስና አብረውት የነበሩት ከባሕር ወለል በታች ስድስት መቶ ጫማ ያህል ከነበረችው ከቅፍርናሆም፣ ከባሕር ወለል በላይ 2550 ጫማ ያህል ከፍታ ላይ ወደ ነበረችው ወደ ኢየሩሳሌም ሲወጡ በደስታ ይዘምሩ ከነበሩት ሕዝብ ጋር ይቀላቀላሉ። ወደ ላይ ከፍ እያሉ ወደ ቅድስቲቱ ከተማ ሲወጡም ሐላል (መዓርግ) በመባል የሚታወቀውን መዝሙር ይዘምራሉ (መዝ 120-134)።

## ምግባረ ብልሹነት

ኢየሱስ ወደ ቤተ መቅደሱ ሲገባ የከብቶች በረት ገጽታና ጠረን ነበረው። መሠዊያው አካባቢ ደም ተረጭቶ፣ በሬዎችና በጎች ያጓሩ፣ ወፎች ይንጫጩ፣ ያስንኩና፣ ሰዎች ሲነኩዋቸው ላባዎቻቸውን ያርገፈግፉ ነበር። ከተለያየ የሮም ግዛት የመጡና የዚያው አካባቢ ተወላጅ ሕዝቦች በዚያ ነበሩ። እነዚህ ሰዎች ለአምላካቸው መሥዋዕት ማቅረብ ስለሚፈልጉ ለዕረፍት ጊዜ የሚሆናቸው ገንዘብ ይዘው ይመጡ ነበር። ሀብት ለነበራቸው አማኞች ይህ በዓመት አንዴ የሚሆን ጉዳይ ነበር። ለድሆች ግን ምናልባት በሕይወት ዘመናቸው አንዴ ብቻ የሚሆን ልምምድ ነበር። ለእነዚህ ሁሉ ሰዎች ሁኔታው ምን ያህል ተስፋ የሚያስቆርጥ ይሆንባቸው ይሆን።

ትዕይንቱ ሁሉ በአንድነት ሆኖ፣ «የሐና ንግድ ማዕከል» (Bazaar of Annas)[20] የሚል መጠሪያ ተሰጥቶታል። ይህ ሰው የአይሁድ ሊቀ ካህናት ነበር። ከነበረው ኃይል ይልቅ ገንዘብ ወዳድነቱና ስግብግብነቱ የላቀ ነበር። እሱ የተከበረና የተፈራ ሰው ነበር። በመቅደሱ አደባባዮች ጥቅም የሚያስገኙለት መረቦችን ዘርግቶ ነበር። የጥቅም ማግኛ ዘዴው እንዲህ ነበር (Edersheim, I:369 ጋር ያነ)፤ አንድ ሰው መሥዋዕት

[20] J. MacArthur, *Matthew,* Vol. 3 (Chicago: Moody, 1988), p. 268.

የሚያቀርበውን እንስሳ ይዞ ሲመጣ፣ ሥርዓቱን የሚያስፈጽመው ካህን (ማምቼህ) ከዚያ እንስሳ ያለ ምንም ጥርጥር አንድ ዓይነት ጉድለት ፈልጐ ስለሚያገኝ ያንን እንስሳ በዝቅተኛ ገንዘብ እንዲሸጥለት ይጠይቀዋል። ከዚያ በኋላ ያ እንስሳ በስተ ኋላ ወዳለው የካህናቱ በረት ተወስዶ ይባረክና ለሌላ መሥዋዕት አቅራቢ በጣም ከፍ ባለ ገንዘብ ይሸጣል። መጀመሪያ እንስሳውን ይዞ የመጣው ሰው ምናልባትም ከመጀመሪያው አራት ወይም አምስት እጥፍ በሚሆን ከፍተኛ ገንዘብ ሌላ «ንጹሕ» እንስሳ ይገዛል። ገንዘቡን ከገንዘብ ቦርሳው ሲያወጣ የገንዘብ ኖቱ የፓለስቲና ከሆነ ትክክለኛውን ምንዛሬ ፍለጋ ወደ ገንዘብ መንዛሪዎች እንዲሄድ ይደረጋል። እንደዚያ በሚያደርግበትም ጊዜ ለምንዛሪው ከአስራ አምስት እስከ ሃያ በመቶ የሚደርስ የምንዛሪ አገልግሎት እንዲከፍል ይጠየቅ ነበር። ይህ ሁሉ ቀላል ገቢ አልነበረም።

ከመሥዋዕቱ በተጨማሪ እያንዳንዱ አይሁድ በየዓመቱ ግማሽ ስቅል የመቅደስ ግብር ገቢ እንዲያደርግ ይጠየቅ ነበር (ዘፀ 30፥13፤ ማቴ 17፥24)። በሌሎች አገሮች የሚኖሩና የተለየ ዓይነት ገንዘብ ያላቸው (ለምሳሌ - በፋርስ፣ በጢሮስ፣ በሶሪያ፣ በግብፅ፣ በግሪክና በሮም) አይሁድ የምንዛሪ ዋጋ መክፈል ነበረባቸው። ሐሚልተን እንደሚለው ከሆነ በኢየሩሳሌም የነበረው ቤተ መቅደስ በዘመኑ እንደ ነበሩት የአረማውያን ሃይማኖት ቤተ መቅደሶች ሁሉ እንደ ማዕከላዊ ባንክ ያገለግል ነበር (2 መቃ 3፥6-15 ጋር ያነ)።[21] እነዚህ መንገደኞችን ገንዘብ ለመዝረፍ ብዙ ወረበሎች አሰፍስፈው ይጠብቁ ነበር።

ይህን የመሰለው ጉዳይ ለሃይማኖታዊ ጉዳይ የሚመጡትን ሰዎች በጣም ያማርራቸው ነበር። ሆኖም ሃይማኖታዊ ግዴታቸውን ለመወጣት የሚፈልጉ ከሆነ ከዚህ ሌላ ምንም አማራጭ አልነበራቸውም። የእንስሳቱ ዋጋ በውል የሚታወቅ አለመሆኑ ደግሞ

[21] N.Q. Hamilton, "Temple Cleansing and Temple Bank," *JBL* 83 (1964): 356-372.



ነገሩን ይበልጥ የከፋ ያደርገዋል። ሁሉም ነገር ለቀማኞች የተመቸ ነበር። ስለሆነም ዋጋን በተመለከተ ብዙ ጭቅጭቅና ውጣ ውረድ ነበር። የአንዳንዶች ፊት ይቀላል፤ አንዳንዶች በቡጢ ለመማታት ይቃጣቸዋል፤ አንዳንዶች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ይጨቃጨቃሉ፤ ይህ ሁሉ በእግዚአብሔር አምልኮ ስም ይደረግ ነበር።

## የመቅደሱ መንጻት

ኢየሱስ ወደ መቅደሱ ሲገባ ወዲያውኑ ተቆጣ። ከገመድ ጅራፍ ማበጀት ጀመረ። በእነዚያ እንስሳት አካባቢ ብዙ ገመድ ሊገኝ እንደሚችል ግልጽ ነው። ባበጀው ጅራፍ በሚገባና በኃይል በመጠቀም እንስሳቱን ሁሉ ከበረቱ አባረራቸው። ቁጥር 15 ላይ፣ «ሁሉን አባረረ» ሲል ገንዘብ መንዛሪዎችንም ጭምር እንደ ሆነ የሚያጠራጥር አይደለም። እንስሳቱ ምንም አያውቁም፤ ሥርዐት መያዝ የነበረባቸው እነዚያ የቀወሱት ሰዎች ነበሩ።

ኢየሱስ በቁጥር እጅግ በሚበልጡት መካከል ብቻውን ሆኖ ሳለ እንዴት እንደዚያ ማድረግ ቻለ? ይህን አስመልክቶ በርካታ መግለጫዎችን መስጠት ይቻላል፤ (1) በሥጋዊ አካሉ እያለ እንኳ የኢየሱስ ንጽሕናና ቅንዓት መለኮታዊ ነበር። ይህ ብቻውን አስደንጋጭ ነበር። (2) ገንዘብ መንዛሪዎቹ ቅጥረኞች ነበሩ። አደጋ የሚያጋጥማቸው ከመሰላቸው ይሸሹ ነበር። ከዚህም በላይ የሚሠሩት ትክክል አለመሆኑን ስለሚያውቁ አንዳንዶቹ ልቦናቸው ውስጥ ጥልቅ የበደለኝነት ስሜት ሳይኖርባቸው አይቀርም። (3) ኢየሱስ የገንዘብ መንዛሪዎችን ጠረጴዛ ሲገለብጥና ምንዛሪ ሳንቲሞች ወለሉ ላይ ሲዘረገፉ ይመለከቱ የነበሩ ሰዎች የሆታ ድምፅ ሳያሰሙ አልቀሩም። ሁኔታው የሕዝባዊ እንቅስቃሴ ገጽታ ነበረው፤ በቁጣ በገነፈለው ቅንዓታቸው ሕዝቡ እንደሚደነፋው ግልጽ ነበር። (4) በአንቶኒያ ማማ ላይ ሆኖ ሁኔታዎችን ሁሉ የሚከታተል የሮም ወታደሮች ካምፕ በአካባቢው ነበር። ቀደም ሲልም

ኢየሱስ ትኩረታቸውን ስቦት ነበር:: ሰዱቃውያን ከምንም ይልቅ የሚጠሉት ነገር ቢኖር እንዲህ ያለው መቀጣጠሉን ነበር:: አንድ ችግር ቢፈጠር ሥልጣናቸውን ከዚያም ባለፈ ሕይወታቸውን እንኳ ሊያጡ ይችላሉ:: ጊዜው አስጨናቂ ነበር:: ሰዎች አዳኝ እየፈለጉ ነበር የሚፈልጉትን ካገኙትም ሊዋጉለት ዝግጁ ነበሩ::

«የአባቴን ቤት የንግድ ቤት አታድርጉት!» አላቸው[22] በቁጥር 17 ዮሐንስ ታሪኩን ከራሱ ማብራሪያ ጋር ያያይዘዋል:: ደቀ መዛሙርቱ፣ በመዝሙር 69÷9 «ለቤትህ ያለኝ ቅናት ያቃጥለኛል» የሚለውን አስታወሱ:: ከተለያዩ ምክንያቶች የተነሣ ይህ ጥቅስ አስደናቂ ጥቅስ ነው:: በመጀመሪያ መዝሙር 69 መሲሐዊ ነው (ከቁ 21 ጋር ያነ):: ቀደም ሲል ስለ ኢየሱስ ከተረዱት እውነት አንዱ ይህ ነበር:: ሁለተኛው «ያቃጥለኛል» የሚለው ቃል በቃል፣ «በላኝ» ማለት ነው:: ይህ ጥቅስ ኢየሱስ ለቤተ መቅደሱ አንድ ከፍተኛ መቆርቆር እንደነበረው ብቻ የሚያመለክት አይደለም:: ጥንት በነበረው ዐውዱ ስንመለከተው የሕመምና የጣዕር ጩኸትን ነው የሚያሳየው:: እንደ ዳዊት ሁሉ ለእግዚአብሔር ያለው ቅንዓት ኢየሱስንም ችግር ውስጥ ሊከተው ነው:: ሦስተኛ፣ «አቃጠለኝ» የሚለው ግሥ በሰብዓ ሊቃናት ትርጉም ከነበረው ኃላፊ አንቀጽ እዚህ በዮሐንስ ወንጌል የወደፊቱን ማሳየት በሚችል መልኩ ተለውጧል:: ለእግዚአብሔር ከነበረው ቅንዓት የተነሣ ዳዊት መዝሙር 69ን በሚጽፍበት ጊዜ መከራ ተቀብሎ እንደነበረ ከታሪክ እንገነዘባለን:: ኢየሱስ ግን ያንኑ ልምምድ ለመጋፈጥ እየተጠባበቀ ነበር:: በዚህ ጊዜ እንኳ የመቅደሱን ማዕከላዊ ባንክ እንቆጣጠራለን የሚሉትን የካህናት አለቃውንና የአገረ ገዥውን ሥልጣን እየተገዳደረ ነበር::

---

[22] ከአሁን የትዕዛዝ አንቀጽ ጋር ሲሆን *me* የሚያመለክተው እየተከናወነ የነበረ ተግባር መቀረጡን ነው::



**ዮሐ 2÷18-22**

18አይሁድም፣ «ይህን ሁሉ ለማድረግ ሥልጣን
እንዳለህ የሚያረጋግጥ ምን ታምራዊ ምልክት
ታሳየናለህ?» አሉት::
19ኢየሱስም፣ «ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት፤
እኔም በሦስት ቀን መልሼ እንሥዋለሁ» ብሎ
መለሰላቸው::
20አይሁድም፣ «ይህን ቤተ መቅደስ ለመሥራት
አርባ ስድስት ዓመት ፈጅቶአል፤ ታዲያ አንተ እንዴት
በሦስት ቀን መልሰህ ታነሣዋለህ?» አሉት:: 21ቤተ
መቅደስ ሲል ግን፣ ስለ ገዛ ሰውነቱ መናገሩ ነበር::
22ሙታንም ከተነሣ በኋላ፣ ደቀመዛሙርቱ ምን እንደ
ተናገረ አስታወሱ፤ መጻሕፍትንና ኢየሱስ ያለውንም ቃል
አመኑ::

አይሁድ[23] (ሰዱቃውያን ካህናት) አስጨናቂ ሁኔታ ገጥሞአቸዋል:: እጅግ በጣም የሚወዱትን በርካታ ገንዘብ አጥተዋል:: በሌላ በኩል ደግሞ ኢየሱስን ከተቃወሙ የበለጠ ውርጅቢኝ ሊገጥማቸው ነው:: ስለዚህም ጥንቃቄ በተሞላው አክብሮት ነበር የቀረቡት:: ማንነቱን ሳይክዱ ለማንነቱ ማረጋገጫ የሚሆን እንዲያሳያቸው ጠየቁት:: ምልክት

---

[23] በዮሐንስ ወንጌል አንዳንድ ጊዜ «አይሁድ» ሲል በጠቅላላው የአይሁድን ሕዝብ፣ የአይሁድን ባሕል ሌላው ቀርቶ ምድረ ይሁዳን እንኳ ያመለክታል:: ብዙውን ጊዜ ግን የማያምኑ የአይሁድ ባለ ሥልጣናትን ለማመልከት በመዋሉ፣ ባላጋራነትን በሚያመለክት መልኩ ነው የቀረበው:: R.A. Culpepper, “The Gospel of John and the Jews,” *Rev & Exp* 84 (Spr 1987): 273-288 እንደሚሉት የዮሐንስን ወንጌል ጠልቀን ባነበብን መጠን፣ አይሁድን አስመልክቶ ያለው አሉታዊ ጐን ይበልጥ ግልጽ እየሆነ ይሄዳል:: ከዚህም በላይ የመጀመሪያዎቹ የዮሐንስ አንባቢዎች (90 ዓ.ም.) ከምኩራብ ተወግደዋል:: ስለሆነም የአይሁድ ባለሥልጣናትን በአሉታዊ ሁኔታ ማቅረቡ (ከታሪክ አንፃር እውነት ከመሆኑም ባሻገር) ለምኩራብ ታማኝ መሆን ለክርስቶስ ታማኝ መሆን ማለት አለመሆኑን ክርስቲያኖችን ለማሳሰብ ይጠቅማል:: ሌላው ኢየሱስ እንኳ በዘመኑ የሃይማኖት መሪዎች መገለል ደርሶበት ነበር::

ለማየት ጠየቁ:: በአይሁድ ዘንድ በነበረው ሕዝባዊ ናፍቆት መሲሕ ሲመጣ ታላላቅ ምልክቶችንና ድንቆችን እንደሚያደርግ ይጠበቅ ነበር:: ስለዚህም በገሐድ መሲሕ ይመጣል ብለው የማያምኑ ሰዱቃውያን እንኳ የሕዝቡን ቁጣ ላለመቀስቀስ ጥንቃቄ ማድረግ ነበረባቸው::

ኢየሱስ ግን የእነርሱን ጨዋታ መጫወት አልፈለገም:: እርሱ የሚሰጠው ምልክት ትንሣኤውን ብቻ ነበር:: የነገራቸውን ቃል በቃል በመውሰዳቸው በተሳሳተ መንገድ ተረድተውታል (ዮሐ 3÷3-4፤ 4÷14-15፤ 4÷32-33፤ 6÷51-52፤ 7÷34-35፤ 8÷51-52፤ 11÷11-12፤ 14÷4-5 ጋር ያነ):: ለመገንባት አርባ ስድስት ዓመት የፈጀውን ሕንፃ ኢየሱስ እንዴት በሦስት ቀን ውስጥ እንደ ገና ሊሠራው እንደሚችል በፍጹም ሊገባቸው አልቻለም:: ይህ ጉዳይ ኢየሱስ እንዲሁም እስጢፋኖስ (ማቴ 26÷61፤ ማር 14÷58፤ ሐሥ 6÷14) ቤተ መቅደሱን እናፈርሳለን ብለዋል ተብለው ለፍርድ በሚቀርቡበት ጊዜ በድጋሚ ይነሣል:: ይሁን እንጂ የኢየሱስን መቃብር ለማስጠበቅ ፈሪሳውያን ጠባቂዎችን በላኩ ጊዜ ምን ለማለት እንደፈለገ ሳይረዱ እንዳልቀረ ማሰብ ይቻላል (ማቴ 27÷62-66)::

ቁጥር 14 ላይ «ቤተ መቅደስ» ሀይሮን (በግሪክ ቋንቋ *hieron*) የሚለው ቃል ቁጥር 19-21 ላይ ናኦስ (በግሪክ ቋንቋ *naos*) ወደሚል መለወጡ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነው:: ሁለተኛው ቃል፣ አማልክት የሚኖሩበት፣ «ቅዱስ ቦታ» እንደማለት ነው:: በ1ኛ ቆሮንቶስ 3÷16-17 እና 6÷19 የክርስቲያንን አካል ለመግለጽ ጥቅም ላይ ውሏል:: ኢየሱስ በግልጽ እየተናገረ የነበረው የራሱ አካል የእግዚአብሔር ማደሪያ መሆኑን ነበር:: የኋላ ኋላ ደቀ መዛሙርቱ ይህ ውይይት ትዝ ብሏቸው የበለጠ በኢየሱስ እንዲያምኑ ታላቅ እምነትን በውስጣቸው አቀጣጥሏል::

ይሄ ጉዳይ ስለ መቅደስ ሕንፃ ሳይሆን ስለ በኢየሱስ ማንነት ላይ ያተኮረ ነበር:: ይሁን እንጂ የኢየሱስ ሞት እንደ እውነቱ መቅደሱንም



ጊዜ ያለፈበት አድርጎታል:: የመጨረሻው መሥዋዕት በመቅረቡ መጋረጃው ለሁለት ተቀዷል:: ከእንግዲህ እግዚአብሔር በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ አይኖርም:: ይልቁንም በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት እግዚአብሔር የሚኖረው በሰዎች ልብ ውስጥ ነው (1ቆሮ 6÷19):: ከዚህም በላይ ኢየሱስን በመግደላቸው የእግዚአብሔር ፍርድ በአይሁድና በቤተ መቅደሳቸው ላይ ወርዷል:: በ70 ዓ.ም. መቅደሱ ሙሉ በሙሉ ሊደመሰስ ነው:: እስከዚህ ጊዜ ድረስ የብሉይ ኪዳን የአምልኮ ሥርዓት በመቅደሱ ውስጥ ዳግመኛ አልቀጠለም::

**§32**
**መጀመሪያ ላይ**
**ለኢየሱስ ተአምራት**
**የተሰጠ ምላሽ**
**(ዮሐ 2÷23-25)**

23 በፋሲካ በዓል በኢየሩሳሌም ሳለ፣ ብዙ ሰዎች ያደረገውን ታምራት አይተው አመኑ፤ 24 ኢየሱስ ግን ሰውን ሁሉ ስለሚያውቅ፣ አይታመንባቸውም ነበር፤ 25 በሰው ውስጥ ያለውን ያውቅ ስለ ነበር ማንም ስለ ሰው እንዲመሰክርለት አላስፈለገውም::

*23 ወይም በስሙ አመኑ*

ከምልክቶቹ የተነሣ ሕዝቡ በኢየሱስ አመኑ (ቁ 23):: እንደ እውነቱ ከሆነ ግን መቅደሱን ከማንጻትና (ሚል 3÷1-3 ጋር ያነ) ለሰዱቃውያን ምላሽ ከመስጠቱ ውጪ ኢየሱስ ምልክቶችን አላደረገም ነበር፤ ሁለቱም ቢሆኑ እንደ እውነቱ ተአምራዊ አልነበሩም:: እንደዚያ ከሆነ ታዲያ እነዚህ ምልክቶች የተባሉት ምን ነበሩ? ኢየሱስ በይሁዳ ከስምንት እስከ ዘጠኝ ወር ያህል በይሁዳ ሊያሳልፍ ነው (ዮሐ 4÷35):: በዚህ ጊዜ በዚያ አካባቢ ብዙ ተአምራት አድርጎ ይሆናል:: ይሁን እንጂ ዮሐንስ እየተናገረ ያለው በበዓሉ ጊዜ በዚያን ጊዜና በዚያ ስፍራ እዚህና አሁን በእርሱ ማመናቸውን ነው:: ምናልባትም በፋሲካው ሰሞን ለእኛ በጽሑፍ ያልተላለፉልን ተአምራቶች ተደርገው ሊሆን ይችላል::

ምንም እንኳ ሕዝቡ በእርሱ ቢያምኑም፤ እርሱ ግን አይተማመንባቸውም ነበር:: ልባቸውን ያውቃል (ዮሐ 1÷42፣47-48፤ 3÷3፤ 4÷29፤ 6÷61፣64፤ 13÷11፤ 21÷17):: እውነተኛ አማኞች ይመስላሉ:: ይህም ማለት እንደ ሌሎቹ እውነተኛ አማኞች ሁሉ ዮሐንስ «በስሙ አመኑ» (ከ1÷12-13፤ 3÷18 ወዘተ ጋር ያነ)[24] ይላል:: ነገር ግን «አማኞችም» አስመሳዮችና የማያስተማምኑ ሊሆኑ ይችላ:: ኢየሱስ በእርሱ እንዲያምኑ ሊፈቅድላቸው ይችላል ነገር ግን አይተማመንባቸውም::

**§ 32ለ ኒቆዲሞስ ከኢየሱስ ጋር ተገናኘ (ዮሐ 3÷1-21)**

ኢየሱስ ከኒቆዲሞስ ጋር ያደረገው ውይይት ለመጨረሻዎቹ ሁለት ቁጥሮች ማብራሪያ ይሆናል (ዮሐ 2÷24-25):: ኢየሱስ ከማይተማመንባቸው «አማኞች» አንዱ እነሆ ወደ እርሱ መጥቷል:: ኒቆዲሞስ የሚያቅማማ ፈሪና ግራ የተጋባ ነበር:: ሆኖም ከመሰሎቹ ምርጥ የነበሩትን መወከል የሚችል ነበር:: ይህ ምዕራፍ ሰንካላ ከሆነ እምነት (ቁ 1-9) ጠንካራ ወደ ሆነ እምነት ያሸጋግረናል::

የምዕራፉ ሂደት ዘገባ ማቅረብ (2÷23-25) ወደ መወያየት (3÷1-12) ከዚያም ለብቻ ወደሚደረግ ንግግር ያሸጋግረናል (3÷17-21):: ከዚያ በኋላም ዘገባ ከማቅረብ (3÷22-24) ወደ መወያየት (3÷25-30) ከዚያም ዮሐንስ ብቻውን ወደሚያደርገው ንግግር ያሸጋግረናል (3÷31-36)::

---

[24] Z.C. Hodges, "Untrustworthy Believers – John 2:23-25" *BibSac* 135 (Apr-Jun 1978): 139-152.



ዮሐ 3÷1-2

1ከፈሪሳውያን ወገን፣ ከአይሁድ አለቆች አንዱ
የሆነ ኒቆዲሞስ የተባለ ሰው ነበረ፤ 2በሌሊትም ወደ
ኢየሱስ መጥቶ፣ «ረቢ፣ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ካልሆነ
ሰው በቀር አንተ የምታደርጋቸውን ታምራዊ ምልክቶች
ማንም ሊያደርግ ስለማይችል፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ
የመጣህ መምህር እንደ ሆንህ እናውቃለን» አለው::

ኒቆዲሞስ በፍጥነት በሚሮጥበት መስክ እየሮጠ ነው:: የአይሁድ ሸንጎ አባል እንደ መሆኑ ሞገስና ተሰሚነት ነበረው:: ኢየሱስ መቅደሱን ማንጻቱን አስመልክቶ (ዮሐ 2÷12-25) እየተጋጋለ በመጣው ክርክርም ውስጥ ዐዋቂ ነበር:: ምናልባትም እንዲህ ያለሥራ የሚበዛበት ሰው ከኢየሱስ ጋር መነጋገር የሚችለው በሌሊት ብቻ ሊሆን ይችላል:: ይሁን እንጂ እሱ ከነበረው ተሰሚነትና በዘመኑ በነበረው ሃይማኖታዊ መድረክ ኢየሱስ ይዙት ከነበረው መካከለኛ ቦታ አንፃር ስንመለከተው ይህ ትክክል መሆኑ ያጠራጥራል:: ይህ ኒቆዲሞስን የመሰለ ሃይማኖት መሪ ሥራ ነበር:: ግን ለምን ነበር በሌሊት ወደ ኢየሱስ የመጣው? ምናልባት ከኢየሱስ ጋር ለማድረግ ለፈለገው ውይይት ጨለማው መልካም ሽፋን ሆኖለት ይሆናል:: አለዚያም በግል ከኢየሱስ ጋር ለመወያየት ለእርሱ ምቹ ጊዜ ያ ጊዜ ብቻ ሊሆን ይችላል:: ያም ሆኖ «ሌሊት» የራሱ ተምሳሌታዊ ፋይዳ አለው::[25]

ኒቆዲሞስ ኢየሱስን በአክብሮት ነበር ያነጋገረው:: ኢየሱስን የመደገፍ ዝንባሌ የነበረወ የአይሁድ ሸንጎ አባል እርሱ ብቻ እንዳልሆነ

---

[25] F.P. Cotterell, " The Nicodemus Conversation: A Fresh Appraisal, "*ExpT* 96 (May 1985): 237-242 ላይ «ሌሊት» የሚለውን በአራት መንገድ መረዳት የሚያስችሉ ነጥቦችን አቅረበዋል፤ (1) ቀላል ጊዜ ቅደም ተከተላዊ ምልክት፣ (2) ኒቆዲሞስ መታወቅ አለመፈለጉን፣ (3) ከ 1÷8-9፤ 3÷19-20፤ 9÷4፤ 11÷10፤ 13÷30 እንደምንመለከተው ምሳሌያዊ አነጋገር ሊሆን ይችላል፤ (4) በዘመኑ የነበሩ የሃይማኖት መምህራን በነገረ መለኮታዊ ጉዳዮች ላይ የሚወያዩት በሌሊት እንደ ነበር::

ግልጽ ነው:: አንዳንድ «ታላላቅ» የሚባሉ ሰዎች ኢየሱስ የነበረውን ኃይል፣ የሥልጣን ስፍራና እንዴት እንደ መጣ ተገንዝበዋል::[26] ኢየሱስ ያደረጋቸው የነበሩ ምልክቶች በፍጹም የሚካዱ አይደሉም፤ እውን ሆነው መኖራቸውም ሆነ እግዚአብሔር በኢየሱስ ሕይወት በረከቱን እንዳኖረ ማስረጃዎች ናቸው:: ተአምራት እንደሚያደርጉ የሚናገሩ ሌሎች የአይሁድ «መምህራንም» ነበሩ፤ ይሁን እንጂ በኢየሱስና በሌሎች መካከል በጣም ሰፊ ልዩነት ነበር::

ምንም እንኳ ኒቆዲሞስ በግልጽ የኢየሱስ ተከታይ ባይሆንም ለእርሱ ጥልቅ አክብሮትና መስጠት ነበረው::[27] በዮሐንስ 7÷50-52 እንደምንመለከተው ኢየሱስ ትክክለኛ ፍትሕ የማግኘት መብቱ ሊከበርለት ይገባል:: በዮሐንስ 19÷38-39 እንደምንመለከተው ለኢየሱስ ቀብር የሚሆን የሽቱ ቅመማ ቅመም ይዞ መጥቶ ነበር:: ኒቆዲሞስ ፈሪ ነበር ብለን ከመውቀሳችን በፊት በእንዲህ ዓይነት ግሃድ ቅንነት ወደ ኢየሱስ የመጣ ፈሪሳዊ እርሱ ብቻ እንደ ነበር ማስታወስ ይኖርብናል::

እዚህ ላይ የምንመለከተው በሁለቱ ሰዎች መካከል ስለ ተደረገው አጭር የሐሳብ ልውውጥ ብቻ መሆኑ ግልጽ ነው:: ወደ አንዱ ወገን እያዳመጠ ሳለ ዮሐንስ ያሰፈረውን ማስታወሻ እንደ ማንበብ ያለ ነገር ነው:: ይሁን እንጂ ዋናውን ሐሳብና እንዲያውም በግንኙነት ወቅት

---

[26] ኢየሱስን የሚያነጋግሩ የኒቆዲሞስ የራሱ ደቀ መዛሙርት ተከትለውት መጥተው ይሆናል:: ስለዚህም፣ «እናውቃለን» የሚለው ብዙ ቁጥር የእርሱን ተማሪዎች እንጂ ሌሎች የአይሁድ ሸንጎ አባሎችን የሚያመለክት ነው ማለት ላይሆን ይችላል:: ምናልባትም ዮሐንስ 2÷23 የተጠቀሰትን አማኞችን በአጠቃላይ የሚመለከት ይሆናል::

[27] J.M. Bassler. "Mixed Signals Nicodemus in the Fourth Gospel." *JBL* 108/4 (1989): 635-646 እንደሚለው ኒቆዲሞስ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ምሳሌ አለማቅረቡን ይገልጻል:: ይህም እየወላወለ ያለ አንባቢን ከዚህ ገጸ ባሕርይ ጋር ተመሳሳይ አቋም እንዲኖረው ያስችለዋል:: Craig Blomberg. "The Globalization of Biblical Interpretation: A Test case – John 3-4" *BBR* 5 (1995): 1-15 ላይ የኒቆዲሞስን እምነት ደካማነት የሚያመለክቱ ሰባት የትረካ ፍንጮችን አቅርቧል::



የነበረውን ስሜት እንኳ መረዳት እስከሚያስችል ሁኔታው በግልጽ ቀርቦልናል:: ዐውዱ ሦስት የሐሳብ ቅብብሎሾችን አስፍሮል ቁ 3-8፤ 9-15፤ 16-21::

**ዮሐ 3÷3-8**

> [3]ኢየሱስም መልሶ «እውነት እልሃለሁ፤ ማንም ዳግመኛ ካልተወለደ″ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም» አለው::
>
> [4]ኒቆዲሞስም፣ «ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት ሊወለድ ይችላል፡ ዳግመኛ እንዲወለድ ተመልሶ ወደ እናቱ ማሕፀንስ ሊገባ ይችላልን?» «አለው» [5]ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰ፤ እውነት እልሃለሁ ማንም ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም፤ [6]ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፤ ከመንፈስ የተወለደም መንፈስ ነው:: [7]ዳግመኛ መወለድ አለባችሁ ስላልሁህ አትገረም፤ [8]ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል፤ ድምፁንም ትሰማለህ፤ ነገር ግን ከየት እንደ መጣ፣ ወዴት እንደሚሄድም አታውቅም፤ ከመንፈስም የተወለደ ሁሉ እንደዚሁ ነው::»

″*በቁ 3 እና በቁ 7 ወይም «ከላይ ካልተወለደ»*

በቁጥር 3 ላይ ኢየሱስ የመለሰው ኒቆዲሞስ ለተናገረው ሳይሆን፣ በውስጡ ለነበረው ጥልቅ ችግር ምናልባትም ስውር መሻቱ ነበር:: ምናልባትም ኢየሱስ ካደረጋቸው ተአምራቶች ሁሉ የኒቆዲሞስን ልብ ማንበብ መቻሉ ይህን ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊያመጣው ይችላል::

ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት አዲስ መወለድን ይጠይቃል:: አኖቴን (*anothen*) የሚለው ቃል በሌሎች ቦታዎች እንደ ተደረገው ሁሉ፣ «ከላይ» ተብሎ ቢተረጐም የተሻለ ይሆን ነበር (ዮሐ 3÷3፣7፣31፤ 19÷11፣23 ጋር ያነ):: ከጊዜ ብቻ ሳይሆን ከባሕርይም አንጻር አዲስ ነው - ሰማያዊ ልደት ነው:: ኒቆዲሞስ ሰው በተለይም

ከሸመገለ በኋላ ዳግመኛ መውለድ እንደማይችል ያውቃል::[28] ኢየሱስ ግን፣ «አዎን፣ የምትለው እውነት ነው፤ ይህ ልደት መንፈሳዊ እንጂ በግዙፍ አካል የሚሆን አይደለም» አለው::

«ከውሃና ከመንፈስ መወለድ» የሚለው ብዙ ሲያከራክር ቆይቷል:: ውሃ ሲባል ምን ማለት እንደሆነ በሦስት ምድቦች ሊቀርቡ የሚችሉ የተለያዩ አስተያየቶች ቀርበዋል:: በመጀመሪያ «ውሃ» ሲባል ሕፃን ሲወለድ ከሚወጣው አምኒዮቲክ ፈሳሽ[29] ወይም የሽንት ውሃ[30] ጋር በማያያዝ ሊሆን ይችላል:: ይሁን እንጂ በአይሁድ ሥነ ጽሑፍ ከተጠቀሰው «ውሃ» ጋር የሕፃን መወለድ መያያዙን የሚያመለክት በግልጽ የተቀመጠ ምሳሌ የለም::

ሁለተኛ፣ ውሃ መንጻትን ሊያመለክት ይችላል:: አንዳንዶች ኢየሱስ ቀደም ሲል የተጠቀሰውን የዮሐንስን ጥምቀት ኒቆዲሞስ እንዲፈጽም እያሳሰበው መሆኑን ይናገራሉ (ዮሐ 1÷23፣26፤ 3÷23):: የዮሐንስ ጥምቀት ከመንፈስ ጋር የተያያዘ ካለመሆኑም ባሻገር ዮሐንስ ራሱ ሰዎችን ከራሱ ይልቅ ወደ ክርስቶስ ማመልከት ጀምሮ ነበር:: ምናልባትም መንጻት የተባለው ሥርዓታዊ መታጠብን ሳይሆን መንፈስ ቅዱስን የሚያመለክት ተምሳሊት ሊሆን ይችላል::[31] እንዲያውም ብሉይ ኪዳን መንፈስ ቅዱስን ብዙውን ጊዜ ከነፋስና ከውሃ ጋር አያይዞ

28 «ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት ሊወለድ ይችላል?» ብሎ በጠየቀ ጊዜ ኒቆዲሞስ በጣም አስፈላጊ ቃል ተጠቅሞአል:: ፓይታጎራስ «ሽማግሌ» [*geron*] የሚለውን ቃል ሲገልጽ ከ60-80 ባሉት ዓመታት መካከል ያለ ሰው ነው ብሏል:: እንግዲህ ይህ ዕድሜ ኒቆዲሞስን ራሱን የሚመለከት ከሆነ በዕድሜ የገፋ ታላቅ ሰው ለመሆኑ ፍንጭ የሚሆነንን ነጥብ እናገኛለን ማለት ነው::

29 ይህን አቋም ስለያዙ ሰዎች R.Fowler, "Born of Water and Spirit (John 3:5)" *ExpT* 82 (1971): 159 እና D.G Spriggs, "Meaning of Water in John 3:5," *ExpT* 85 (1974): 150 ይመ::

30 Leon Morris, *Expository Reflections on the Gospel of John* (Grand Rapids: Baker, 1986) pp. 90-91 ይመ::

31 Z.C. Hodges, "Water and Spirit – John 3:5," *BibSac* 135 (July 1978): 206-220 ይመ::



አቅርቦታል (ዘፍ 1÷2፤ ኢዮ 2÷28-29፤ ኢሳ 44÷3፤ ሕዝ 36÷25-27) በተለይም ደግሞ እነዚሁ ተምሳሌቶች ሰዎችን ወደ ሕይወት በማምጣት ረገድ ቀርበዋል (ኢሳ 32÷15-17፤ 55÷1-3፤ ኤር 2÷13፤ 17÷13፤ ዘካ 14÷8):: በተጨማሪም፣ «መንፈስ» የሚለው ቃል «ነፋስ» ተብሎም ተተርጕሞአል:: ስለዚህም ኢየሱስ አንድ ሰው ከላይ ይወለድ ዘንድ ከነፋስና ከውሃ መወለድ እንደሚገባው መናገሩ ይሆናል:: ሁለቱም ተለዋጭ ዘይቤዎች መንፈስ ቅዱስን ያመለክታሉ ሁለቱም የሚመጡት ከሰማይ ነው፤ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ሁለቱም የመንጻት ምሳሌዎች ናቸው::

ሦስተኛ ውሃ ጥምቀትን ለማመልከት ሊሆን ይችላል::[32] ከሚከተሉት ምክንያቶች የተነሣ እኛም የምንደግፈው ሦስተኛውን ነው:-

(1) ሁለቱም ስሞች (ውሃና መንፈስ) በአንድ መስተዋድድ ይገዛሉ:: ስለዚህም ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ስለ አንድ ልደት እንጂ ስለ ሁለት አይደለም::
(2) ለተቀባዮቹ አዲስ ልብና መንፈስ ስለሚያስገኝላቸው ወደፊት የሚሆነውን መንጻት ሁኔታ የትንቢት ጸሐፊው በሚናገርበት በሕዝቅኤል 36÷25-27 «ውሃ» እና «መንፈስ» የተሰኙት ሁለቱም ቃላት ተያይዘዋል:: ይህ የጥምቀትን ሥርዓት ሕሊናዊ ሥዕል በአግባቡ ያቀርባል::
(3) የጥምቀትን ጽንስ ሐሳብ ቀደም ሲል ዮሐንስ አስተዋውቆ ነበር:: ስለሆነም በውሃና በመንፈስ ስለ መጠመቅ እዚህ ላይ ቢነሳ ሊደንቀን አይችልም (ዮሐ 1÷25-26፣28፣31-33)::
(4) ስለ ጥምቀት በሚናገሩ ሌሎች ምንባቦችም ውሃና መንፈስ ተያይዘው ቀርበዋል (ማቴ 28÷19፤ ሐሥ2 ÷38፤ 19÷1-7፤ቲቶ 3÷5)::

32 L.L. Belleville, "'Born of Water and Spirit': John 3:5," *TrinJ* 1(1980): 125-140.

(5) የግሪክና የላቲን ተናጋሪ የነበሩት አባቶች በአንድ ድምጽ የተረጎሙት ይህ ጥቅስ በውሃ ውስጥ ስለ መጥለቅ እንደሚያመለክት ነበር::

(6) ልክ ይህን ከተናገረ በኋላ በነበረው ምጥን ትረካ ኢየሱስ ሲያጠምቅ እንመለከታለን (ዮሐ 3÷22 )::

(7) የዮሐንስ የመጀመሪያ አንባቢዎች ስለ ጥምቀት ሳያስቡ እነዚህን ጥምር ቃላት (ውሃና መንፈስ) አነበቡ ማለት የማይመስል ነው::[33]

እርግጥ ነው፣ እዚህ ላይ ክርስቲያናዊ ጥምቀት ወቅቱን የጠበቀ አልነበረም (ቁ 10) ኢየሱስ ገና ተግባር ላይ ያልዋለውን ክርስቲያናዊ ጥምቀት ባለመፈጸሙ ኒቆዲሞስን ገስጾት ነበር ማለት አይቻልም:: ይሁን እንጂ የዮሐንስ ጥምቀት (ዮሐ 1÷26) ክርስቲያናዊ ጥምቀት ለሚሆነው ለኢየሱስ ጥምቀት (ዮሐ 1÷33፤ 3÷22) ቦታ ይለቃል (ማቴ 28÷19)::

ኒቆዲሞስ ዳግም እንዲወለድ መጠበቅ በፍጹም ከኢየሱስ የሚጠበቅ አልነበረም:: እንደዚያ ማድረግ የአንድ አገር ፕሬዝዳንት በመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ስለ ሥነ መንግሥት እንዲማር የመጠየቅ ያህል ነበር:: ይህ ሰው በትምህርት ደረጃውም ሆነ በሙያው እዚያ ደርሷል:: አሁን ኢየሱስ አገኘሁ ወይም ደረስኩበት ከሚለው ደረጃው ዝቅ እንዲል ኒቆዲሞስን እያሳሰበው ነው:: ይህ ግን ለአንድ ወደ ይሁዲነት ለገባ አንድ ሰው ወይም ለልጆች እንጂ እንደ ሕግ ዶክተር ለሆነ ሰው የሚመች አልነበረም::

የሐሳብ ቅብብሎሹ እንደገና መንፈስ/ነፍስ ወደሚለው ቃል ይመለሳል:: ቃሉ በዕብራይስጥም ሆነ በግሪክ ተመሳሳይ ነው:: ቃሉ ጠንከር ያለ ሐሳብን ያስተላልፋል:: ነፋስን ዘግነን ለበኋላ እንዲሆነን

[33] በተመሳሳይ መንገድ የዮሐንስ አንባቢዎች ዮሐ 6÷53-54 ሲያነቡ ስለ ጌታ ራት፣ ዮሐ 7÷38-39 ሲያነቡ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ በሰዎች ውስጥ እንደሚኖር ማሰባቸው የማይቀር ነው::



በኪሳችን ማስቀመጥ እንደማንችል ሁሉ መንፈስ ቅዱስንም ልንጨብጥና ከውስጡ የምንፈልገውን ያህል ጨምቀን ልናወጣ አንችልም:: ስለሆነም የመንግሥቱ ዜጋ ለሆነ ሰው መቅረብ ያለበት አስፈላጊ ጥያቄ፣ «መንፈስ ቅዱስን አግኝኻል ወይ?» የሚል ሳይሆን «መንፈስ ቅዱስ አግኝቶሃል ወይ» የሚል መሆን አለበት::

በቁጥር 8 ላይ በነጻነት እንደሚንቀሳቀስ የተነገረለት ከመንፈስ የተወለደ ሁሉ እንጂ ራሱ መንፈስ ቅዱስ ብቻ እንዳልሆነ መረዳት ይኖርብናል:: ይህን መሳዩ ሰው ታዲያ በአንድ ስፍራ ቢገታ፣ እንቅስቃሴው በቅድሚያ ሲታወቅ ወይም በቁጥጥር ሥር ሲውል አይቻልም:: እንደ ነፋስ በነፃነት የሚኖር ምንም የለም::

**ዮሐ 3÷9-15**

9ኒቆዲሞስም፣ «ይህ እንዴት ሲሆን ይችላል?» ሲል
ጠየቀው10 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰለት፣ «አንተ
የእስራኤል መምህር ሆነህ ሳለ እነዚህን ነገሥታት አታውቅምን?
11እውነት እልሃለሁ የምናውቀውን እንናገራለን፣ ያየነውንም
እንመሰክራለን እናንተ ግን ምስክርነታችንን አትቀበሉም 12ስለ
ምድራዊው ነገር ነግሬአችሁ ያላመናችሁ ስለ ሰማያዊው ነገር
ብነግራችሁ እንዴት ታምናላችሁ? 13ከሰማይ ከወረደው ከሰው ልጅ በቀር ወደ ሰማይ
የወጣ ማንም የለም:: 14ሙሴ በምድረ በዳ እባብን እንደ ሰቀለ፣ የሰው ልጅም
እንዲሁ ሊሰቀል ይገባዋል፤ 15ይኸውም በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት
እንዲኖረው ነው::

በመጀመሪያ መንደርደሪያ ንግግሩ ኒቆዲሞስ ሁለት ጥያቄዎችን ጠየቀ:: አሁን የተፈቀደለት ግን «ይህ እንዴት ይሆናል?» የሚለውን ጥያቄ ብቻ እንዲጠይቅ ነው:: ኒቆዲሞስ የአይሁድ መምህራን አስተሳሰብና ሃይማኖታዊ ፖለቲካ የዘለቀው ሰው ስለነበረ የእግዚአብሔር መንግሥትን መሠረታዊ እውነቶች መረዳት አልቻለም:: ሊማረው የሚገባው ትምህርት ይሄ ነበር (ቁ 13)፣ የእግዚአብሔርን ልብ በእርግጥ

መረዳት እንችል ዘንድ ኢየሱስን ማድመጥና ለማንነቱ ራሳችንን ልንሰጥ ይገባናል:: ከሰማይ ወደ ምድር የሚያመራውን መንገድ የቀደደው እሱ ብቻ ነው፣ ወደዚያም የመመለሻውንም መንገድ የሚያውቀው እሱ ነው::

በቁ 10 ላይ ኢየሱስ ረጋ ያለ አልነበረም:: «እስራኤል» እና «መምህር» የሚሉትን ቃላት የያዘውን ሐረግ በመጠቀም ኢየሱስ ኒቆዲሞስን አበክሮ በመተቸት አዝማሚያ ላይ ነበር:: አባባሉን እንደዚህ አድርጎ ሳይረዳው አይቀርም:- «ልትለኝ የምትፈልገው አንተ ያን ያህል ታዋቂ የእስራኤል መምህር ሆነህ ሳለ እነዚህን መሠረታዊ ነገሮች መገንዘብ እንደማትችል ነው?»:: እዚህ ላይ ውይይቱ ያቆምና ኢየሱስ ብቻውን መናገር ይቀጥላል::

ኢየሱስ ስለ ምድራዊ ነገሮች እየተናገረ መሆኑን አመለከተ:: ይህም ዳግመኛ መወለድ በምድራዊ ተምሳሊት የቀረበ መንፈሳዊ ክንውን ነው ማለት ነው:: የሚመጣው ግን (ዮሐ 3÷16) ጅማሬው ከሰማይ ነው:: ከዳግም ልደት ይልቅ የእግዚአብሐርን ፍቅር መረዳት ምንኛ ይከብዳል::

ኢየሱስ በሙሴ እባብ ተመስሏል (ዘኁ 21÷8-9):: እስራኤል በተደጋጋሚ ያጉረመርሙ ስለ ነበር እግዚአብሔር ተቆጥቶ ተናዳፊ እባቦችን ሰደደባቸውና ተገደሉ:: ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል ማሰብ ይቻላል - በፍጥነት በንስሐ ተመለሱ:: ሆኖም፣ ያን ያህል ቀላል አልነበረም:: ፈውስ የተከናወነው ሙሴ እንጨት ላይ የሰቀለውን የናስ እባብ በመመልከት ነበር:: በተመሳሳይ ሁኔታ ኢየሱስ (መስቀል ላይ)[34] መሰቀል ነበረበት:: ወደ እርሱ የሚመለከቱ ሁሉ (በእምነት)፣ ከእባብ መነደፍ (ኃጢአት ከሚያስከትለው ቅጣት) ይድናሉ:: ይህ ስለ ኢየሱስ ሞት ዮሐንስ ያቀረበው ሦስተኛው ተምሳሊታዊ መግለጫ ነው (1÷29፤ 2÷19 ጋር ያነ)::

[34] ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ ከፍ ማለት ሲናገር በዚህ ቃል አማካይነት ስለ መስቀሉ መነሣቱና ማረጉ ጭምር መናገሩ ነው::



**ዮሐ 3÷16-21**

[16]በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት
እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን
እስከ መስጠት ድረስ ዓለምን እንዲሁ ወዶአልና፤[35]
[17]እግዚአብሔር ልጁን ወደ ዓለም የላከው በዓለም
ለመፍረድ ሳይሆን፣ ዓለምን በእርሱ ለማዳን ነው
[18]በእርሱ የሚያምን ሁሉ አይፈረድበትም፤ በእርሱ የማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር
ልጅ" ስም ስላላመነ፣ አሁኑኑ ተፈርዶበታል:: .[19]ፍርዱም ይህ ነው፤ ብርሃን ወደ ዓለም
ወጣ፤ ሰዎች ግን ሥራቸው ክፉ ስለ ነበረ፤ ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ወደዱ፤ [20]ክፉ
የሚያደርግ ሁሉ ብርሃንን ይጠላል፤ አድራጎቱም እንዳይገለጥበት ወደ ብርሃን
አይመጣም:: [21]በእውነት የሚመላለስ ግን ሥራው በእግዚአብሔር የተሠራ መሆኑ በግልጽ
ይታይ ዘንድ ወደ ብርሃን ይመጣል::"

*"18 ወይም በእግዚአብሔር አንድያ ልጅ "21አንዳንድ ተርጓሚዎች ትዕምርተ ጥቅሱን ከቁ 15 በኋላ ያደርጋሉ::*

ከቁጥር 16-21 ያለውን ኢየሱስ ይሁን ወይም ዮሐንስ ማን እንደተናገረው ማወቅ ያስቸግራል:: ያም ሆነ ይህ ወንጌል እጥር ምጥን ባለ መልኩነው (ዮሐ 3÷16-18) የአዲስ ኪዳን የእንቁ ጉልላት ነው:: የትም ቢሆን ነገረ መለኮታዊ አስተምህሮ በዚህ መልኩ በቀላሉ ቀርቦ እንዲህ ወዳለ እጅግ የላቀ ምጥቀትም ወጥቶ አያውቅም:: ከእያንዳንዱ ቃል በኋላ የቃለ አጋኖ ምልክት እየጨመርን ማንበብ ሳያስፈልገን አይቀርም::

ዮሐንስ 3÷16ን በተመለከተ ማክጋርቪ (ገጽ 131) እንዲህ ይላል:-

[35] «ወዶአልና» የሚለው ቃል [ግሪክ *houtos*] የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ፍቅር ብዛት ሳይሆን ጥረት ነው:: H.K. Moulton, "John 3:15- God so Loved the World," *BT* 27/2 (Apr 1976): 242, በሚከተለው ሁኔታ ተርጉሞታል፣ «እግዚአብሔር ዓለምን የወደደው እንዲህ ነበር፤ አንድ ልጁን እስከ መስጠት ድረስ ...»::

የእግዚአብሔርን ፍቅር አስመልክቶ የቀረበ ትምህርት ሲሆን፣ 1. የመስፈርት መጠኑ - አንድያ ልጁን መስጠቱ:: 2. የመድረስ ክልሉ - ለኃጢአተኛው ዓለም (ሮሜ 5÷8) መስጠቱ:: 3. አስማድሳቱ - ለሁሉም ማለት ማንንም ሳይለይ ሰጠ (ማቴ 5÷45፤ ሩእ 22÷17):: 4. የሚያስገኘው ብልጥግናዊ ጥቅም - በዘላለም ሕይወት መባረክ:: 5. ገደቡ - የትም ቦታ ቢሆን እግዚአብሔር የማያምኑ ሰዎችን እስከሚያድን ድረስ ወደደ የሚል የለም::

ኢየሱስ የመጣው ለማዳን እንጂ ለመፍረድ አልነበረም:: የዘላለምን ሕይወት ማለት ለረጅም ዘመናት የሚቆይ ብቻ ሳይሆን መለኮታዊ ጥራት ያለውንም ሕይወት መምጣት ፍላጐቱ ነበር:: ሆኖም የእርሱ ቃል የእግዚአብሔር በመሆኑ ለኢየሱስ የሚሰጠው ምላሽ ሰው ሁሉ የሚፈተንበት ማንጠሪያ ሆኗል::

ኢየሱስ ሲበዛ መልካም ነው (3÷19-21):: ሆኖም እንደ ፈለግን የምናደርገው አይደለም:: ይልቁንም ሁለንተናችንን እንድንስጠው ይጠይቃል፤ ሊያሳምመን ቢችልም እውነቱን በሚገባ ይገልጻል፤ ኃጢአትን ይቀጣል፤ አለማመንን በቸልታ አያልፍም፤ ያለማቅማማት ዐመፃችንን የሚገልጥ ብርሃን ነው::[36] አንድ ሰው እርቃኑን ለመሆንና ክርስቶስን ብቻ ለመልበስ ዝግጁ የማይሆን ከሆነ የሚኖረው አማራጭ እየተሸማቀቀ ወደ ጨለማ ማፈግፈግ ነው::

## § 33
## ከዮሐንስ እስከ ኢየሱስ
## (ዮሐ 3÷22-36)

ቀደም ሲል ከ8-9 ወሮች ስለ ወሰደው በይሁዳ ስለ ነበረው የኢየሱስ አገልግሎት የሚነግረን ዮሐንስ ብቻ ነው:: በማቴዎስ 4÷11

[36] ዮሐንስ የተጠቀመበት «ኤሌንቼ» የሚለው ቃል «ወደ ብርሃን መምጣት» የሚለውን ብቻ ሳይሆን፣ የኋላ ኋላ «ቅጣት» በሚያስከትል ሁኔታ በበደል «መያዝ» የሚለውንም ሐሳብ ያካትታል::



እና 12 መካከል ምን እንደ ተደረገ ሦስቱ ተወራራሽ ወንጌሎች የሚነግሩን ነገር የላቸውም (ማር 1÷13-14፤ ሉቃ 4÷13-14 ጋር ያነ):: ኢየሱስ ለፋሲካ ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ (ዮሐ 2÷13 ሚያዝያ አካባቢ) መከር ከመድረሱ በፊት እስከ ነበሩት አራት ወራት እዚያ ቆይቷል (ዮሐ 4÷35):: በዚህ ወቅት ኢየሱስ መቅደሱን አነጻ (ዮሐ 2÷13-22)፣ ብዙ ተአምራቶችን አደረገ (ዮሐ 2÷23፤ 3÷2)፣ ደቀ መዛሙርትን አጠመቀ (ዮሐ 3÷23):: ይሁን እንጂ ስለ ተናገረውም ሆነ ስላደረገው በጣም ጥቂት ዝርዝር ብቻ ነው ያለን::

በዚህ ወቅት የኢየሱስ ታዋቂነት እየገነነ የመምጣቱን ያህል የዮሐንስ ደግሞ በፍጥነት እያሽቆለቆለ ነበር:: ዮሐንስ የፈለገውም በእርግጥ ይህንኑ ነበር:: ሆኖም በመካከላቸው ከነበረው የወዳጅነት ፉክክር የተነሣ የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ይህንን እንደ አንድ ዓይነት ክስረት ነበር የተመለከቱት:: ከምንባባችን በስተጀርባ ለሁኔታዎች መፋጠን ምክንያት የነበረው ይህ ነው::

ዮሐ 3÷22-26

22ከዚህ በኋላ ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ወደ ይሁዳ አገር ሄዱ፤ እዚያም ከእነርሱ ጋር ጥቂት ተቀመጠ፤ አጠመቀም:: 23በዚህ ጊዜ ዮሐንስም በሳሌም አቅራቢያ ሄኖን በተባለ ስፍራ ብዙ ውሃ ስለ ነበረ ያጠምቅ ነበር፤ ሰዎችም ለመጠመቅ ይመጡ ነበር:: 24ይህም የሆነው ዮሐንስ ከመታሰሩ በፊት ነበር:: 25በአንዳንድ የዮሐንስ ደቀ መዛሙርትና በአንድ አይሁዳዊ መካከል ስለ መንጻት ሥርዐት ክርክር ተነሣ፤ 26ወደ ዮሐንስም መጥተው፤ «ረቢ፣ በዮርዳኖስ ማዶ ከአንተ ጋር የነበረው ስለ እርሱም የመሰከርህለት ሰው፣ እነሆ ያጠምቃል፤ ሰውም ሁሉ ወደ እርሱ እየሄደ ነው አሉት::

ኢየሱስ የዮሐንስን ሥራና የማጥመቅ አገልግሎት ማስፋፋቱን ቀጥሏል:: በዚህ ጊዜ ግን ዮሐንስ በሳሌም አጠገብ በሄኖን በትጋት

እያገለገለ ነበር። ሳሌም ማለት፣ «ምንጮች» ማለት ሲሆን፣ ማክጋርቪ ሳሌምን አስመልክቶ እንዲህ ይላል፣ «ረጅም ጊዜ የሚቆይ ፈሳ፣ በሚያልፍበት ሁሉ የሚንዶለዶሉ ፏፏቴዎች የታጀበ፣ በጣም ረጅምና ደረቅ በሆነ የበጋ ወቅት እንኳ «ለማጥመቅ የሚበቃ፣ ብዙ ውሃ» የሚያስገኘው ይኸው ነው» (ገጽ 134)።

ከዚህ ስምንት ወር በኋላ ዮሐንስ ሊታሰር ነው (ማቴ 4÷12፤ ማር 1÷14 ጋር ያነ)። ያለው ጊዜ አጭር ነው። የመንጻት ሥርዐትን አስመልክቶ (ቁ 25) አንድ ስሙ ይልተገለጠ አይሁዳዊ ከዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ጋር ጭቅጭቅ ፈጥሮ ነበር። ይህም ቁጥር 26 ላይ ባለው ሁኔታ ደቀ መዛመርቱ ከዮሐንስ ጋር ቃለ ምልልስ እንዲያደርጉ ከፈተላቸው። ለምን? የመንጻት ሥርዓትን አስመልክቶ የተነሣው ክርክር በዮሐንስ ጥምቀትና በኃጢአት ስርየት ምንነት ዙሪያ የሚሽከረከር ሳይሆን አይቀርም። ይህም ቢሆን ተመሳሳይ መልክ ወደ ነበረው ወደ ኢየሱስ ጥምቀት ማምራቱ የማይቀር ነበር። ያም ሆኖ ዮሐንስ ስለ አዲስ ዓይነት ጥምቀት ማለትም ስለ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ስለ መጠመቅ ተስፋ እየሰጠ ነበር። ከራሳችን አንፃር ስንመለከተው ኢየሱስ በመንፈስ የማጥመቁ ጉዳይ ገና አልተከናወነም። ይህ አይሁድ ግን ወዲያውኑ የሚሆን አድርጎ ሳይጠብቅና በርካታ ነገሮችን ማወቅ ሳይፈልግ አይቀርም። (1) የኢየሱስ ጥምቀት ከዮሐንስ ጥምቀት ጋር የተመሳሰለው ለምንድነው? በመካከላቸው ያለው ልዩነት ምን ነበር? (2) ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት የሚያጠምቀው እንዴት ነው? (3) በውሃ ውስጥ መስጠም የኃጢአት ይቅርታን በማስገኘት ውጤታማ የሚያደርገው እንዴት ነው?

በቁጥር 26 ላይ የምንመለከተው ቅንዓት አዘል አስተያየታቸው ዮሐንስ ከኢየሱስ ጋር በመወገኑ የውስጠ ወይራ ተግሣጽ ያለበት ነበር። እነዚያ አክራሪ የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ሁኔታውን በንቀት እየተከታተሉ ነበር። በተሳሳተ ሁኔታ ቢሆንም ያለ ጥርጥር ለዮሐንስ



ከፍተኛ ክብሬታ ነበራቸው። ስለሆነም ዮሐንስ ለስለስ ባለ መንገድ ሳይሆን እነርሱን በድጋሚ ለኢየስስ አሳልፎ መስጠት ነበረበት። አብረውት የኖሩት ደቀ መዛሙርቱን ከእርሱ የማላቀቅ ችግር ገጥሞታል።

[27]ዮሐንስም እንዲህ ሲል መለሰ፤ «ከላይ
**ዮሐ 3÷27-30** ካልተሰጠው በቀር ማንም አንዳች ሊቀበል አይችልም።
[28]እኔ ክርስቶስ አይደለሁም፤[u] ነገር ግን ከእርሱ በፊት
ተልኬአለሁ እንዳልሁ እናንተ ራሳችሁ ትመሰክሩላችሁ [29]ሙሽራይቱ የሙሽራው ነች፤
ድምፁን ለማስማት በአጠገቡ የሚቆመው ሚዜ ግን የሙሽራውን ድምፅ ሲሰማ እጅግ
ደስ ይለዋል ያ ደስታ የእኔ ነው፤ እርሱም አሁን ተፈጽሞአል። [30]እርሱ ሊልቅ፣ እኔ
ግን ላንስ ይገባል።

*[u]28 ወይም መሲሑ*

እነዚህ በጽሑፍ የተላለፉልን የመጥምቁ ዮሐንስ የመጨረሻ ቃላት ናቸው። የዮሐንስን ክቡር ሰውነትና የኢየሱስን ልቀት ያሳያሉ። «ከላይ ካልተሰጠው በቀር ማንም አንዳች ሊቀበል አይችልም» በማለት በቅድሚያ የተናገረው እርሱ ራሱን ወይም ኢየሱስን የሚመለከት ሊሆን ይችላል። ያንን በተናገረበት ጊዜ ኢየሱስን ማለቱ ከሆነነ «ኢየሱስ አገልግሎቱን የተቀበለው ከእግዚአብሔር ነው፤ ስለዚህም ብዙ ደቀ መዛሙርት በማፍራቱ ደስ ይለኛል» ማለቱ ነው። ዮሐንስ እየተናገረ ያለው ስለ ራሱ ከሆነ ግን፣ «አገልግሎቴን የተቀበልሁት ከእግዚአብሔር ነው። ስለዚህም ራሴን ገናና ማድረግ ወይም ከተወሰነልኝ ዓላማ ገደብ አልፌ የመሄድ መብት የለኝም» ማለቱ ሊሆን ይችላል። ከቁጥር 28-30 ዐውድ አንጻር ስንመለከተው፣ ይኸኛው ይበልጥ አሳማኝ ነው።

በቁጥር 29 የተገለጸውን የዮሐንስን ሁኔታ ስንመለከተው በዘመኑ የተለመደ የደስተኛ ገጽታ ነበር፤ (ኤር 7÷34፤25÷10፤ 33÷11 ጋር ያነ)። ሚዜው ሙሽራው መምጣቱን ያውጃል፤ ሙሽሪት እጇን

እንድትሰጠው ይጠይቃል፤ የአቀባበል ሥርዓቱን ሁሉ ያመቻቻል:: ሆኖም የእርሱ ደስታ ሙሽራውን እንጂ ራሱን ማስተዋወቅ አይደለም:: በተመሳሳይ መልኩ የዮሐንስ ደስታ የራሱ ሳይሆን የኢየሱስ ልቆ መገኘት ነበር:: በዮሐንስ እንደተነገሩት እንዲህ ያሉ ጨዋነትን የሚያንፀባርቁ ቃላት በማንኛውም ቀደ መዝሙር ተነግረው አያውቁም፤ «እርሱ ሊልቅ፣ እኔ ግን ሳንስ ይገባል»::

**ዮሐ 3፥31-36**

[31]ከላይ የሚመጣው ከሁሉ በላይ ነው፤ ከምድር የሆነው የምድር ነው፤ የምድሩንም ይናገራል:: ከሰማይ የሚመጣው ከሁሉ በላይ ነው፤ [32]ያየውንና የሰማውን ይመሰክራል፤ ነገር ግን ምስክርነቱን ማንም አይቀበልም፤ [33]ምስክርነቱን የተቀበለ ሰው፣ እግዚአብሔር እውነተኛ እንደሆነ አረጋገጠ:: [34]እግዚአብሔር መንፈሱን ሳይሰፍር ስለሚሰጥ እግዚአብሔር የላከው የእግዚአብሔርን ቃል ይናገራል:: [35]አብ ወልድን ይወዳል፤ ሁሉንም ነገር በእጁ ሰጥቶታል:: [36]በወልድ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት አለው፤ በወልድ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቁጣ በላዩ ይሆናል እንጂ ሕይወትን አያይም»[ii]

*[ii]36 አንዳንድ ተርጓሚዎች ትዕምርተ ጥቅሱን ከቍጥር 30 በኋላ ያደርጋሉ::*

ዮሐንስ ኢየሱስን አስመልክቶ ያቀረበልን ነገረ መለኮታዊ ዕይታ[37] ድጋሚ እያስደነቀን ነው (ቁ 31-36):: እዚህ ላይ ስለ ኢየሱስ መለኮታዊነትና የእግዚአብሔር ልጅነት እንደሚገባ የዳበረ መረዳትን እንዲሁም ለእርሱ መታዘዝን መሠረት ያደረገ የእምነት ምላሽ አግኝተናል:: አዲሱ መደበኛ ትርጉም፣ «አይቀበልም» (ቍ 36) የሚለውን ፍቺ አዞአል ትርጉም በሆነ መልኩ አስቀምጦታል፤ ይህ

---

[37] እነዚህ ቃላት የመጥምቁ ዮሐንስ እንጂ የወንጌሉ ጸሐፊ የዮሐንስ እንዳይደሉ ታሳቢ በማድረግ ነው::



ማንም የሚመኘው አይደለም:: ይሁን እንጂ ቃሉ፣ «አይታዘዝም» (አፔይቲዩ *apeitheo*) ቢባል ይበልጥ ትክክል ይሆን ነበር:: በሌላ ቦታ «አያምንም» ተብሎ ተተርጕሞአል:: እንደ አቻ ቃሉ «እምነት» ሁሉ ወደ ተግባር የሚመራ እምነትን ያመለክታል (ያዕ 2፥20 ጋር ያነ)::

**§ 34**
**ኢየሱስ ከይሁዳ ወደ ገሊላ ሄደ**
**(ማቴ 4፥12፤ ማር 1፥14፤ ሉቃ 3፥19-20፤ 4፥14፤ ዮሐ 4፥1-4)**

ይህ አጭር ክፍል ሽግግራዊ ይዘት አለው:: በጣም ቀደም ሲል ኢየሱስ ያገኛቸውን ሁለት ሰዎች ማለት በሳል፣ ምሁርና የተከበረ መሪ የነበረውን ኒቆዲሞስንና ኀጥእ፣ ያልተማረች፣ የሌላ አገር ሰው የነበረችውን ሳምራዊት ሴት እንደ ድልድይ ሆኖ ያገለግላል:: እንዲህ ያለ ከፍተኛ ተቃርኖ ባለበት እንደ ወርቃማ ሰንሰለት ሆኖ ሁለቱን የሚያስተሳስራቸው ኢየሱስ ነው:: ከሁሉም ይልቅ እነርሱ ሁለቱም ይፈልጉት ነበር:: ከዚህም በላይ ይህ አጭር ክፍል ጠቅላላውን የወንጌል ትረካ፣ (ሀ) ትኩረትን ዮሐንስ ላይ ከማድረግ ይልቅ ኢየሱስ ላይ ወደ ማድረግ (ለ) በይሁዳ ይሰጥ ከነበረው አገልግሎቱ ወደ ገሊላ አገልግሎት መሸጋገሩን (ሐ) ዮሐንስ ላይ ይሰነዘር ከነበረው ተቃውሞን ኢየሱስ ላይ ወደሚሰነዘር ተቃውሞ፣ (መ) በማቆጥቆጥ ላይ ከነበረው የኢየሱስ አገልግሎት በሙላት እውቅና ወዳገኘበት ደረጃ መምጣቱን ያመለክታል:: ምንባቡ እንደ መቆራቆሻ የሚቆጠር ክፍል ነው:: ዋነኛው የኢየሱስ አገልግሎት መጀመሩን የሚያበስር በመሆኑ ከፍተኛ ፋይዳ የሚሰጠው ነው (ሉቃ 23፥5፤ ሐሥ 10፥37)::

**ሉቃ 3፥19-20**

[19]ነገር ግን ዮሐንስ፣ የአራተኛውን ክፍል ገዥ ሄሮድስን በወንድሙ ሚስት በሄሮድያዳ ምክንያትና ስለ ሌሎች ሥራዎቹ በገሠጸው ጊዜ፣ [20]ሄሮድስ ይህን በሌላው ሁሉ ላይ በመጨመር ዮሐንስን ወህኒ ቤት አስገባው::

[12]ኢየሱስ የዮሐንስን መታሰር በሰማ ጊዜ (በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ[ሉቃ]) ወደ ገሊላ ተመለሰ::

**ማቴ 4÷12 ከሉቃ 4÷14 ጋር**

ከበርካታ ምክንያቶች የተነሣ ኢየሱስ ከይሁዳ ወደ ገሊላ መሄድ ነበረበት:: በመጀመሪያ፣ የዮሐንስ መታሰር ከአሥራ አራት እስከ አሥራ ስምንት ወሮች ያህል ለነበረው አገልግሎቱ መዝጊያ ሆኗል:: ከዮሐንስ ጋር ከነበረው ጥብቅ ቀረቤታ የተነሣ ለኢየሱስ አደጋ የሚጥርበትም ሁኔታ ነበር:: በስድስት ወሮች ብቻ የሚበላለጡ ዘመዳሞች ነበሩ:: ኢየሱስ የአገልግሎቱ ምክንያት እንደነበር ዮሐንስ ተናግሮአል:: ሙያቸውም» አንድ ዓይነት ነበር:: ከዚህም በላይ ሁለቱም በተመሳሳይ ሁኔታ ውሃ ውስጥ በማጥለቅ ያጠምቁ ነበር፤ ሁለቱም ተመሳሳይ አስተምህሮን ማለት ንስሐንና የእግዚአብሔርን መንግሥት ይሰብኩ ነበር:: ሁለቱም በአንድ ሳንቲም እንዳሉ ሁለት ገጽታዎች ነበሩ:: ስለሆነም ጊዜው ሳይደርስ በሄሮድስ እንዳይታሰር ኢየሱስ ከአካባቢው ዘወር አለ (በኋላ ላይ ሁኔታው በእርግጥም አደገኛ እንደ ነበር ታይቷል፣ ሉቃ 13÷31-32 ጋር ያነ):: ከዚህ ያለፈ ጉዳይም ነበር:: ዮሐንስ በሳሌምና በሄኖን እየሰበከ ነበር:: ምንም እንኳ ከነበሩት አማራጭ ቦታዎች የትኛው ዘንድ እንደነበረ በእርግጠኝነት መናገር ባይቻልም በሰማርያና በገሊላ ድንበር አካባቢ አንድ ቦታ ላይ ሳይሆን እንደማይቀር ይታሰባል:: ስለሆነም ኢየሱስ በደቡባዊ ፖለስቲና ሲያገለግል፣ የዮሐንስ አገልግሎት ግን ያተኮረው በመካከለኛው/በላይኛው ፖለስቲና ነበር:: የዮሐንስ መታሰር በአካባቢው ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ለመስበክ ዕድል ያስገኘ መንፈሳዊ ክፍተት ትቶ አልፏል:: ኢየሱስ ይህን ዮሐንስ የተወውን ባዶ ቦታ በሚገባ መሙላት ይችል ነበር::

ሁለተኛ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ይመራ እንደ ነበር በግልጽ ይታያል:: ሉቃስ 4÷14፣ «ኢየሱስም በመንፈስ ኃይል ወደ ገሊላ ተመለሰ» ይላል:: በአገልግሎቱ የእግዚአብሔር ጊዜ ሰሌዳም እንዳለ



ይገነዘባል (ዮሐ 10÷18፤ 1÷31፤ 14÷31):: አስቀድሞ የተወሰነውን የእግዚአብሔር ዕቅድም እየፈጸመ እንደ ነበር ይረዳል (ዮሐ 2÷4፤ 7÷30፤ 8÷20፤ 12÷23):: ገሊላ የኢየሱስ አገልግሎቱን የሚያካሂድበት ቦታ መሆንዋን በትንቢት መነገሩንም እናስታውሳለን (ኢሳ 9÷1-2፤ ማቴ 4÷14-16)::

[1]ፈሪሳውያን ከዮሐንስ ይልቅ ኢየሱስ ብዙ ደቀ መዛሙርትን እንዳፈሩና እንዳጠመቀ ሰሙ፤ [2]ዳሩ ግን ያጠመቀው ኢየሱስ ሳይሆን ደቀ መዛሙርቱ ነበሩ:: [3]ጌታም ይህን እንዳወቀ ይሁዳን ለቆ ወደ ገሊላ ተመልሶ ሄደ [4]በሰማርያም በኩል ማለፍ ነበረበት::

**ዮሐ 4÷1-4**

ኢየሱስ ከይሁዳ ወደ ገሊላ የተሻገረበት ሦስተኛው ምክንያት ይህ ነው:: በአንድ በኩል በቅርቡ ከፈሪሳውያን ጋር ሊኖር የሚችለውን ጭቅጭቅ ማስወገድ የፈለገ ይመስላል:: የኢየሱስ ታወቂነት እያደገ መጥቷል (ዮሐ 3÷26):: በዮሐንስ አገልግሎት ከነበረው የሚሰማው ሕዝብም የበለጠ እያደገ መጥቷል:: ይህ ደግሞ ተፎካካሪና ምቀኛ መንፈሳቸውን ቆጥቁጦታል (ማቴ 27÷18 ጋር ያነ):: «ከገሊላ ይልቅ በይሁዳ የፈሪሳውያን ተሰሚነት በጣም ከፍተኛ ነበር፤ በይሁዳ ቢቆይ ኖሮ የአይሁድ ሸንጐ አባሎች ወዲያውኑ ያስሩት ነበር (ዮሐ 7÷1፤ 10÷39» (Mc Garvey,P.140):: ከዚህም በላይ ዮሐንስ ከታሰረ በኋላ (ማቴ 4÷12፤ ማር 1÷14) የፈሪሳውያን ተንኰልና የደቀ መዛሙርቱም መሰጠት ያነጣጠረው ኢየሱስ ላይ ነበር::

በዚሁ ወቅት ኢየሱስ ሰዎችን ውሃ ውስጥ በማስጠም እያጠመቀ ነበር:: ይሁን እንጂ ኢየሱስ ገና ሞቶ ስላልተነሣ ይህ ጥምቀት ክርስቲያናዊ ጥምቀት አልነበረም (ከሮሜ 6÷1-6 ጋር ያነ):: ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግቢያ ይሆን ዘንድ (ዮሐ 3÷5) ለኀጢአት

ሥርየት ዮሐንስ የጀመረው ጥምቀት ቀጣይ ነበር (ማር 1÷4)። በኋላ ግን የመንግሥቱ መጀመር አብሣሪ በሚሆነው በክርስቲያናዊ ጥምቀት ይተካል (ማቴ 28÷18-20፤ ሐሥ 2÷38፤ ቈላ 2÷11-12)። አሁን ግን እንደ ሕፃን ለመሆንና (ሉቃ 18÷16-17) ዳግም ለመወለድ ፈቃደኛ ለሆኑት (ዮሐ 3÷5) ልዩ ምልክት በመሆን ያገለግላል።

የማጥመቁን ሥራ በውክልና ለደቀ መዛሙርቱ ስለ መስጠቱን ቅንብብ ውስጥ መቀመጥ በሚችል መልኩ የተናገረውን እንመለከታለን (ዮሐ 4÷2)። ይህ ደግሞ ከ1ቆሮንቶስ 1÷14-17 የምንመለከተው ጳውሎስን የገጠመው ዓይነት ጭቅጭቅ እንዳይኖር ይረዳል።

### § 35 ኢየሱስና ሳምራዊቷ ሴት (ዮሐ 4÷5-26)

ኢየሱስ ከዚህች ሴት ጋር ያደረገው ግንኙነት በብዙ መንገድ ከኒቆዲሞስ ጋር ካደረገው ግንኙነት በንጽጽር የሚታይ ነው። እርሷ የውጭ ሰው ነበረች፤ እርሱ ግን የቤት ሰው ነበር፤ እርሱ ስመ ገናና ነበር፤ እርሷ ግን የተጣለች ነበረች፤ እርሷ ወራዳ ሴት ነበረች፤ እርሱ ግን የተከበረ ነበር። ይሁን እንጂ ሁለቱም የመሲሑን መምጣት በናፍቆት ሲጠብቁ የነበሩ መሆናቸው ተመሳሳይ ያደርጋቸዋል። በዚህ ምዕራፍ ቀሪ ክፍል ዮሐንስ ሦስት አስፈላጊ ዐቢይ ሐሳቦችን ያቀርባል - የሕይወት ውሃ፤ እውነተኛ አምልኮና አሕዛብ ስለ መጨመራቸው። እነዚህ ሦስቱም በክርስቶስ ማንነት ተፈጻሚ ይሆናሉ።

ይህን ያህል ትኩረት ስለ ተሰጠው «ውሃ» አንዳድ ነገሮችን መመልከት ይጠቅማል። ምዕራፍ 1 ላይ ዮሐንስ ውሃን የተጠቀመበት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት ለሚረዳ የንስሐ ጥምቀት ነበር። ምዕራፍ 2 ላይ ኢየሱስ ለመንጻት ሥርዓት እንዲሆን ጋኖች ውስጥ የነበረውን ውሃ ወደ ወይን ጠጅ ለወጠ፤ ይህም ወደ ፊት እርሱ የሚመሠርተውን አዲስ መንግሥት የሚያስተዋውቅበት ምሳሌ ነበር።



ምዕራፍ 3 ላይ ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ ዳግመኛ መወለድ እንደሚገባው ኢየሱስ ለኒቆዲሞስ ሲነግረው እንመለከታለን። አሁን ደግሞ በሰማሪያ ውሃ ጉድጓድ አጠገብ ሆኖ እርሱ የሕይወት ውሃ መሆኑን ለሳምራዊቷ ሴት መናገሩን እናነባለን።

ጥቂት ቀደም ሲል ቁጥር 4 ላይ ኢየሱስ በሰማርያ በኩል ማለፍ እንደ «ነበረበት» (ኤዲይ - edei) ዮሐንስ መናገሩን ተመልክተናል። ብዙ አይሁድ ወደ ገሊላ ለመሄድ የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻግረው በፔሪያ በኩል ማለፍን ይመርጣሉ። መንገዱ በጣም ረጅም ቢሆንም በሥርዓቱ መሠረት በሳምራውያን እንዳይረክሱና ምናልባትም ዘርን መሠረት ያደረገ አላስፈላጊ ግጭትን ለማስወገድ ነበር ያንን የሚያደርጉት።[38] ይሁን እንጂ ኢየሱስ አጭር በሆነው መንንገድ መሄድን ነበር የመረጠው፤ ምናልባትም በፍጥነት ወደ ገሊላ ለመመለስ ስለ ቸኰለ ይሆናል (ምንም እንኳ በዚያ አካባቢ ሁለት ቀን መቆየቱ ባይቀርም፣ ቁ 40)። ምናልባትም ፔሪያ ከነበሩ አይሁድ ጋር መገናኘት ባለ መፈለጉ ሊሆን ይችላል፤ ወይም ደግሞ ፔሪያ የሄሮድስ ግዛት ስለ ነበረች በዚያ በማለፍ የሄሮድስን ትኩረት ለመሳብ ስላልፈለገ ይሆናል። ሦስተኛው ምክንያት ግን ከዚህች ሴት ጋር እንዲገናኝ መለኮታዊ ቀጠሮ እንዳለው ኢየሱስ በመገንዘቡ በፖለቲካዊ ሳይሆን በእግዚአብሔር ዕቅድ መሠረት በዚያ እንዲያልፍ ግድ ስለሆነበት ይሆናል።

---

[38] Merilyn L. Hargis, "On the Road: The Inns and Outs of Travel in First – Century Palestine" *ChHist* 17/3 (1998): 28-31 ላይ አይሁዳውያን ተጓዦች በሰማርያ በኩል ማለፍ አይፈልጉም ነበር የሚለውን በሚያሳምን መልኩ አትቀበልም። ይህ አስተሳሰብ የተወሰኑ አይሁድ በሰማርያ በኩል ሲያልፉ ጉዳት እንደ ደረሰባቸው የሚጠቁም የጆሴፈስ ጽሑፍ መሠረት ያደረገ እንደ ሆነ ታመለክታለች። ሆኖም ጥቃቱ የደረሰው በ52 ዓ.ም ከኢየሱስ አገልግሎት ዘመን በኋላ ቆይቶ እንደ ነበር ትናገራለች። ከዚህም በላይ ጆሴፈስ፣ «ለበዓል ወደ ቅድስት ከተማ ሲመጡ ገሊላውያን በሰማርያ በኩል ማለፋቸው የተለመደ ነበር» በማለት መጻፉን ትጠቅሳለች። ይህ እንደ ተጠበቀ ሆኖ ብዙ አይሁዳውያን ዮርዳኖስን ተሻግረው ይሄዱ የነበረው ሳምራውያንን እንደ ርኩስ ይቆጥሩ ስለ ነበር ነው የሚለውን አትቀበልም።

[5]ስለዚህ በሰማርያ፣ ያዕቆብ ለልጁ ለዮሴፍ
በሰጠው ቦታ አጠገብ ወደ ነረበች፣ ሲካር ወደምትባል
ከተማ መጣ፡፡ [6]በዚያም የያዕቆብ የውሃ ጉድጓድ ነበረ፤
ኢየሱስም ከጉዞው የተነሣ ደክሞት ስለ ነበር በውሃው
ጉድጓድ አጠገብ ተቀመጠ፤ ጊዜውም ከቀኑ ስድስት ሰዓት
አካባቢ ነበር፡፡

ዮሐ 4÷5-9

[7]አንዲት ሳምራዊት ሴት ውሃ ለመቀዳት ስትመጣ ኢየሱስ፣ «እባክሽ
የምጠጣው ስጪኝ» አላት፤ [8]ደቀ መዛሙርቱ ምግብ ለመግዛት ወደ ከተማ ሄደው
ነበር፡፡

[9]ሳምራዊቷም፣ «አንተ አይሁዳዊ ሆነህ፣ እኔን ሳምራዊቷን እንዴት ውሃ
አጠይኝ ትላለህ?» አለችው፡፡ ይህን ማለቷ አይሁድ ከሳምራውያን ጋር ስለማይተባበሩ
ነው፡፡

*ፀወይም ሳምራውያን በተጠቀሙበት ሳሕን/ዕቃ አይጠቀሙም ነበር፡፡*

ሲካር ከያዕቆብ ጉድጓድ ሩብ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኝ መንደር ስትሆን (እዚህ ላይ ግን ከተማ ተብላለች) ከኢየሩሳሌም በስተ ሰሜን በግምት ሠላሣ ኪሎ ሜትር ትርቅ ነበር፡፡ ኢየሱስና አብረውት የነበሩት እዚያ የደረሱት ቀትር ላይ ነበር፡፡ ደቀ መዛሙርቱን ወደ መንደር ከላከ በኋላ እርሱ በውሃው ጉድጓድ አጠገብ ዐረፈ፡፡ በአሁኑ ጊዜ ጉድጓዱ ሰባ አምስት ጫማ ጥልቀት ያለው ሲሆን፣ ውሃ የሚኖርበት በክረምት ወቅት ነው፡፡ በድንጋይና በፍርስራሽ ተሞልቶ ነበር፡፡ ኢየሱስ ባገለገለበት ዘመን ምናልባት አንድ መቶ ጫማ ያህል ጥልቀት ሳይኖረው እንደማይቀር ይታሰባል፡፡

በዚያ ጉድጓድ አጠገብ ኢየሱስ ብቻውን ነበር፤ ደቀ መዛመርቱ ምግብ ለመግዛት ወደ መንደር ሄደዋል፡፡ እነርሱ ባልነበሩበት ጊዜ ይህች ሳምራዊት ሴት ውሃ ለመቅዳት መጣች፡፡ ኢየሱስም ውሃ እንድትሰጠው ጠየቃት፡፡ ሴት ከመሆንዋ በተጨማሪ ሳምራዊትም ስለ ነበረች ይህ በፍጹም የማይታሰብ ነበር፡፡[39] በዚያ ዘመን ወንዶች ሌላው ቀርቶ፣ ከሚስቶቻቸው ጋር እንኳ በአደባባይ አይነጋገሩም ነበር፡፡ ከዚህም በላይ ዮሐንስ እንደሚለው፣ «አይሁድ ከሳምራውያን ጋር አይተባበሩም ነበር፡፡» እዚህ ላይ ግሡ «አብረው አይሆኑም» የሚል ነው፤ ይህ ደግሞ ብዙ ጊዜ የሚመለከተው ዕቃን ነው፡፡ ስለሆነም አንድ አይሁዳዊ ሳምራዊ በሚጠጣበት ብርጭቆ አይጠጣም ነበር፤ ኢየሱስ ግን ያንን ነበር እየጠየቀ የነበረው (Hendricksen, P.161)፡፡ አይሁድ ከሳምራውያን ጋር ይገናኙ እንደ ነበር (ለምሳሌ መግዛትና መሸጥን በተመለከተ) ከቁጥር 8 መመልከት ይቻላል፡፡ በሌላ ቦታ ደግሞ ምንም እንኳ ኢየሱስ ሳምራውያንን ከአሕዛብ ጋር በአንድ ምድብ ቢያስቀምጣቸውም (ማቴ 10÷5)፣ እንደ ባዕድና እንግዳ ቢቆጥራቸውም (ሉቃ 17÷18)፣ ይህን መናናቅ የማስወገድ ፍላጐት እንደ ነበረው እንመለከታለን፡፡

[10]ኢየሱስም፣ «የእግዚአብሔርን ስጦታ ብታውቂና
ውሃ አጠይኝ የሚልሽ ማን መሆኑን ብትረጂ ኖሮ፣
አንቺው በጠየቅሽው እርሱም የሕይወትን ውሃ በሰጠሽ
ነበር» ሲል መለሰላት፡፡

ዮሐ 4÷10-15

[11]ሴትየዋም እንዲህ አለችው፤ ጌታዬ መቅጃ የለህም፤ ጉድጓዱም ጥልቅ
ነው፤ ታዲያ ይህን የሕይወት ውሃ ከየት ታገኛለህ? [12]ስመሆኑ አንተ፣ ይህን ጉድጓድ
ከሰጠን፣ ከአባታችን ከያዕቆብ ትበልጣለህን? እርሱ ራሱና ልጆቹ እንስሳቱም ከዚሁ
ጉድጓድ ጠጥተዋል፡፡»

[13]ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላት፤ «ከዚህ ውሃ የሚጠጣ እንደ ገና
ይጠማል፤ [14]እኔ ከምሰጠው ውሃ የሚጠጣ ግን ከቶ አይጠማም፤ እኔ የምሰጠው ውሃ
በውስጡ የሚፈልቅ የዘላለም፣ ሕይወት ውሃ ምንጭ ይሆናል፡፡» [15]ሴትዮዋም፣
«ጌታዬ፤ እንዳልጠማና ውሃ ለመቅዳት እንዳልመላለስ እባክህ ይህን ውሃ ስጠኝ፣»
አለችው፡፡

[39] J.D.M. Derrett "The Samaritan Woman's Purity (John 4:4-52," *EvQ* 60/4 (1988): 291-298.

እዚህ ላይ ኢየሱስ፣ «እኔ ማን መሆኔን ብታውቂ ኖሮ አንቺ ራስሽ የሕይወትን ውሃ ትጠይቂኝ ነበር» በማለት በትክክል የሴትየዋን ስሜት መሳብ ችሏል:: «የሕይወት ውሃ» የሚለው ቃል፣ የምንጭን፣ የፈፋንና የወንዝ ውሃን ለመግለጽ የሚጠቅም ነበር፤ ጉድጓድ ወይም ዕቋሪ ውስጥ ካለ ውሃ ይልቅ ወራጅ ውሃን የሚያመለክት ነው (ዘፍ 26÷19፤ ዘሌ 14÷5):: ኢየሱስ የሚነግራትን ቃል በቃል ነበር የተረዳችው:: «ውሃ መቅጃ የለህም፤ ጉድጓዱ ደግሞ ጥልቅ ነው» በማለት መለሰች:: ከዚያ ጉድጓድ ኢየሱስ የሕይወት ውሃ ሊሰጣት እንደማይችል ግልጽ ነበር:: ይሁን እንጂ በአካባቢው ሌሎች ምንጮችም ነበሩ:: ምናልባት ይህ ፀጉረ ልውጥ ሰው በጣም ጥሩ ውሃ ያለባቸው ምንጮችን ሊያውቅ እንደሚችል አስባለች:: አሁን ያለንበት ላይ ሆነን ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ስለ መንፈሳዊ በተለይ ደግሞ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ተያያዥ ስለሆኑ ነገሮች እንደ ነበር እንረዳለን (ዮሐ 7÷37-39)::

ታላቁ የአይሁድ አባት ያዕቆብ ይህን ጥልቅ ጉድጓድ ለመቆፈር ብዙ ደክሞ ነበር:: ብዙ ጠጠሮችና ጭንጫማ ቦታዎች አልፎ ነበር ከመሬት ጥልቅ ያንን ንጹሕ ውሃ ማግኘት የቻለው:: ጉድጓዱ ቀዝቃዛና ንጹሕ ውሃ ያለበት ነበር:: ይህ ፀጉረ ልውጥ ሰው በምንም ዓይነት ከያዕቆብ ጋር መወዳደር አይችልም (ቁ 12) ይሁን እንጂ ኢየሱስ ያለምንም ማመንታት እርሱ የበለጠ መሆኑን ይናገራል:: እርሱ የሚሰጠው ውሃ ለዘላለም ያረካል፤ ከዚያም አልፎ ይህ የሕይወት ውሃ ከውስጥ የሚመነጭ ይሆናል:: ይህ ምንጭ የዘላለም ሕይወት እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም:: ውይይቱ የተጀመረው በያዕቆብ ጉድጓድ ቢሆንም ወዲያውኑ ሰማያዊና ዘላለማዊ ወደሆኑ ነገሮች ተሸጋገረ::

እንዳለመታደል ሆኖ ግን እርሷ ለእንዲህ ዓይነቱ ታላቅ እርካታ ዝግጁ አልነበረችም፤ ውሃ መቅጃ እንስራዋን ተሸክማ በየቀኑ ወዲያ ወዲህ ከመመላለስ ብታርፍ እርካታ ያለው ሕይወት ሊኖራት እንደሚችል አስባ ነበር:: «እንዳልጠማና ውሃ ለመቅዳት እንዳልመላለስ



እባክህ ይህን ውሃ ስጠኝ» አለችው:: ከቤቷ ውሃ ጉድጓዱ ድረስ የዐ/ሥር ደቂቃ ርቀት ብቻ ቢሆንም፣ በውሃ የተሞላ እንስራ ይዞ በየቀኑ መመላለስ ግን በጣም አታካች ነበር:: ባቀረበችው ሐሳብ ውስጥ፣ «እስቲ፣ የምትናገረውን በተግባር አሳየኝ!» የሚል መልእክት ማንበብ ይቻላል:: እርሱም የጠየቀችውን እንዲያውም ከዚያም ያለፈ ነገር አሳያት::

**ዮሐ 4÷16-18**

16እርሱም፣ «ሂጂና ባልሽን ጠርተሽ ወደዚህ
ተመለሽ» አላት::
17ሴትዮዋም፣ «ባል የለኝም» ብላ መለሰች:: ኢየሱስም እንዲህ አላት፣ «ባል
የለኝም ማለትሽ ትክክል ነው፤ 18በእርግጥ አምስት ባሎች ነበሩሽ፤ ከአንቺ ጋር
ያለውም ባልሽ ስላልሆነ የተናገርሽው እውነት ነው::»

ባልዋን ጠርታ እንድትመጣ ኢየሱስ በዚህ ጊዜ የጠየቃት ለምን ነበር? ለባልዋ መንፈሳዊ አመራር እንድትገዛ ሊነግራት ይሆን? ስለ ኃጢአትዋ ንስሐ እንድታደርግ መናገሩ ነበር? ለኃጢአተኞች ያለውን ፍቅር፣ ታሪኩን የሚያነቡ ሁሉ መረዳት እንዲችሉ ይሆን? ሁሉን ዐዋቂነቱን ለማሳየት በተገኘው ዕድል መጠቀሙ ይሆን? ዓላማው ምንም ይሁን ምን፣ ኢየሱስ የሴትየዋን ትኩረት በመማረክ ወደ ራሱ እየሳባት ነበር:: ኢየሱስ ያለፈ ሕይወቷን በማወቁ ይህን የሕይወት ውሃ የሚለውን ነገር ሊሰጣት እንደሚችል እርግጠኛ ነበረች::

> ሴትየዋ የሰጠችው መልስ ቁርጥ ያለ ነበር:: ብዙ ተናጋሪ የነበረችው ሴት (4÷11፣12፣15ን ልብ ይሏል) በድንገት አፏ ተዘጋ:: በተለያየ ጊዜ መልስ ለመስጠት የተጠቀመችባቸውን ቃላት መቁጠር ራሱ በጣም የሚገርም ነው፤ በግሪኩ መሠረት ቁጥር ዘጠኝ ላይ 11 ቃላት ተጠቅማለች፤ ቁጥር ዐሥራ ሁለት ላይ 42 ቃላት፣ ቁጥር ዐሥራ ሰባት ላይ ግን «ባል የለኝም» የሚሉ ሁለት ቃላት ብቻ ነበር የተጠቀመችው (Hendriksen. P.164)::

በግልጽ ማየት እንደሚቻለው ኢየሱስ የችግሯን ሥረ መሠረት አግኝቷል:: የትኩረት አቅጣጫዋ እዚያ ላይ እንዲሆን በማሰብ ዐረፍተ ነገሩ መጀመሪያ ላይ፣ «ባልሽ» የሚል ቃል አንሥቶአል::

ሴትየዋ አምስት ባሎች የነበሯት መሆኑ ብዙ የሚያስደንቅ አልነበረም:: በዘመኑ በነበሩ ሮማውያን መካከል መፋታት እንደ ቀላል ነገር ይታይ ነበር፤ በቤት ውስጥ ሚስት ብትኖራቸውም በውጭ ግን የተለያዩ ቅምጦች ነበሯቸው:: ልቅነት የሚያጠቃው የሒላል ትምህርት ተጽዕኖ ያሳደረባቸው አይሁዳውያን ዘንድ እንኳ ሚስቶችን መፍታት በጣም የተለመደ እየሆነ መጥቶ ነበር:: ሒላል በመባል ይታወቅ የነበረ አይሁዳዊ መምህር ሌላው ቀርቶ፣ «ምግብ ስትሠራ ወጡ ካረረባት» ሚስትን መፍታት እንደሚቻል ይናገር ነበር:: ጋብቻን በተመለከተ ሳምራውያን የነበራቸው ሥነ ምግባር በሮማውያንና በአይሁዳውያን መካከል የሚዋልል ነበር::

ዮሐ 4÷19-26

19ሴትየዋም እንዲህ አለችው «ጌታዬ፣ አንተ
ነቢይ እንደ ሆንህ አያለሁ፤ 20አባቶቻችን በዚህ ተራራ ላይ
ሰገዱ፤ እናንተ አይሁድ ግን ሰው መስገድ ያለበት
በኢየሩሳሌም ነው ትላላችሁ» አለችው::
21ኢየሱስም እንዲህ አላት፤ «አንቺ ሴት፤ በዚህ ተራራም ሆነ በኢየሩሳሌም
ለአብ የማትሰግዱበት ጊዜ እንደሚመጣ እመኚኝ:: 22እናንተ ሳምራውያን ለማታውቁት
ትሰግዳላችሁ፤ እኛ ግን ድነት ከአይሁድ ስለሆነ ለምናውቀው እንሰግዳለን:: 23በእውነት
የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል፤ አሁንም
መጥቶአል፤ አብም እንደዚህ በእውነት የሚሰግዱለትን ይፈልጋል:: 24እግዚአብሔር
መንፈስ ነው፤ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ይገባል::
25ሴትየዋም፣«ክርስቶስ የተባለ መሲሕ እንደሚመጣ ዐውቃለሁ፤ እርሱ ሲመጣ
ሁሉን ነገር ይነግረናል» አለችው::
26ኢየሱስም፣ «የማነጋግርሽ እኮ እኔ እርሱ ነኝ» ሲል ገለጦ ነገራት::



ኢየሱስ ያሳለፈችውን ሕይወት ዐወቀ:: እርሷም ነቢይ መሆኑን የመሰከረችው ወዲያውኑ ነበር:: እስከዚህ ድረስ ግልጽ ነው:: አሁን ግን ውይይቱ በእርሷ ኃጢአተኝነት ላይ እንዲያተኩር ከማድረግ ይልቅ አንገብጋቢ ወደ ሆነው ነገረ መለኮታዊ ክርክር ማለትም፣ ስለ ትክክለኛ የአምልኮ ቦታ ስትከራከር እንመለከታለን:: አንዳንዶች ከራስዋ ኃጢአት ለመደበቅ እንደ ሞከረች አድርገው ይወቅሷታል:: የጥልቅ ልቦናዋ ዓላማ ግን ከዚያ ያለፈ ሊሆን ይችላል:: እስቲ የሕይወታችሁን ምስጢር በሙሉ ገልጦ ሊነግራችሁ ከሚችል ነቢይ ጋር እንደ ተገናኛችሁ አስቡ:: ምን ዓይነት ጥያቄዎችን ታቀርቡለት ነበር? ይህች ሳምራዊት በአይሁድና በእርሷ ሕዝብ መካከል ሲያጨቃጭቅ የነበረ ጥያቄ ለኢየሱስ ማቅረቧ ሙሉ በሙሉ አግባብ ይመስላል::

በተለይም ደግሞ ይህን ሲነጋገሩ የቀድሞው መቅደስ ከነበረበት 1050' በታች ቆሞ በነበረ የጌባል ተራራ ግርጌ ቆመው እንደ ነበር ስናስብ ጥያቄውን የበለጠ ግለት ይሰጠዋል:: ከቅርብ ርቀት ዮሐንስ ሕርቃነስ በሚባል ሌላ የኢየሩሳሌም አይሁድ በ127 ዓ.ቅ.ክ ተደምስሶ የነበረውን የሳምራውያንን መቅደስ ፍርስራሽ በጣቷ ማመልከት ትችል ነበር::[40] ይህ ደግሞ የሕዝቧን ቁጣ የሚያጭር ጉዳይ ነበር::

አይሁዶች እንደሚያስቡት እግዚአብሔር የወሰነው የአምልኮ ቦታ ኢየሩሳሌም ብቻ ነበር (ዘዳ 12÷5-11፤ 1ነገ 9÷3፤ 2ዜና 3÷1):: ሳምራውያን ግን ጌባል መሆን እንዳለበት ነበር የሚያምኑት::[41]

---

[40] R.J. Bull, “Archaeological Context for Understanding John 4:20” *BA* 38 (May 1975): 54-60.

[41] ምክጋርቢ (ገጽ 147) ላይ ጌባል ተገቢ የአምልኮ ቦታ ነው በማለት ሳምራውያን የሚያቀርቧቸው ምክንያቶችን ዘርዝሮአል፣ «(1) ከነዓን ከገባ በኋላ እግዚአብሔር ለአብርሃም ለመጀመሪያ ጊዜ የተገለጠለት በዚህ ቦታ ነበር (ዘፍ 7÷6-7)? (2) የዕቆብ መጀመሪያ የኖረው እዚህ ነበር (ዘፍ 33÷18):: (3) ዮሴፍ ወንድሞቹን ፍለጋ የመጣው ወደዚህ ነበር (ዘፍ 37÷12-13):: (4) የመማጠኛ ከተሞች የነበሩት እዚህ ነበር (ኢያ 20÷7-9):: (5) ኢያሱ በረከቶችና መርገሞችን ያነበበው እዚህ ነበር (ኢያ 8÷33):: (6) የመጨረሻ

አምልኮ እግዚአብሔርን በማወቅና በመውደድ ልብ የሚዘነበልበት እንጂ፣ አካል በአንድ ቦታ ተወስኖ የሚፈጸም ተግባር እንደሆነ በማሰባቸው አይሁድም ሆኑ ሳምራውያን ተሳስተዋል:: አሁን ግን ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር አዲስ ኅብረት ማድረግ የሚችልበትን (ኤር 31÷31-34፤ ዕብ 8÷8-12) መንፈስ ቅዱስና የሰው መንፈስ መገናኘት የሚችሉበትን መንገድ እያስተዋወቃት ነበር (1ቆሮ 2÷10-14፤ 6÷19)::

ድነት ከአይሁድ መሆኑ እውነት ነው፤ መዝሙር 147÷19-20፤ ኢሳይያስ 2÷3፤ አሞጽ 3÷2፤ ሚክያስ 4÷1-2፤ ሮሜ 3÷1-2፤ 9÷3-5:18 የሚያረጋግጡትም ይህንኑ ነው:: ይሁን እንጂ የቤተ መቅደሱ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች የሚቀደድበትና (ማቴ 27÷51)፣ ድነት ለሁሉም ሕዝብ የሚሆንበት (ሐሥ 10÷34-35) ወቅት በፍጥነት እየመጣ ነበር:: የትኩረት አቅጣጫው ከስፍራ ወደ ሰው ይዛወራል:: እግዚአብሔር በሰው እጅ የተሠራ መቅደስ እንደማይፈልግ፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ ይገነዘባል (ሐሥ 7÷48፤17÷24)::

«እግዚአብሔር መንፈስ ነው::»[42] ትናንሽ ልጆች የሚቀበሉት የነገረ መለኮት ሊቃውንት ግን ጨርሶ የማያስተውሉት ነገረ መለኮታዊ አስተምህሮ ከኢየሱስ አንደበት እየፈለቀ ነበር:: ይህ የእውነት ቅንጣት ይህን ያህል ነበር:: የእግዚአብሔርን ባሕርይ በተመለከተ ብዙ ጥያቄዎችን መመለስ ይቻላል፣ ሆኖም ወደ ሌሎች ብዙ ጥያቄዎች ይመራል::

ለኢየሱስ ምን ዓይነት ምላሽ መስጠት እንደ ነበረባት እርግጠኛ አልነበረችም:: ተስፋዋን አነሣሥቶ ነበር:: እርሷ ግን፣ «መሲሑ ሲመጣ ሁሉንም ነገር ግልጽ ያደርግልናል» በማለት ነገሩን ችላ አለች:: ኢየሱስ ግን፣ «እኔ እኮ መሲሑ ነኝ» አላት:: ማንነቱን አስመልክቶ ኢየሱስ ይህን በመሰለ ግልጽ ሁኔታ በድጋሚ ሲናገር የምንሰማው ከሁለት ዓመት በኋላ ነው (ማቴ 16÷16-18) ሳምራውያን በማስገደድ የፖለቲካ መሪ እንደማያደርጉት ያውቃል (ዮሐ 6÷15 ጋር ያነ):: ከዚህም በላይ እዚያ የሚቆየው ለሁለት ቀን ብቻ ስለ ነበር በዚያ አጋጣሚ ነገሩን ግልጽ ማድረግ ነበረበት:: ሳምራውያን በከፍተኛ ደረጃ መሲሑን እየጠበቁ እንደ ነበር ከሰጡት ምላሽ መረዳት ይቻላል (ሐሥ 8÷9፤ Josephus, Ant. 18.85)::

**§ 35ለ**
**መከሩ ደርሶአል**
**(ዮሐ 4÷27-38)**

27በዚህ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ተመልሰው መጡ፤
ከሴት ጋር ሲነጋገር በማግኘታቸው ተደነቁ፤ ሆኖም ግን፣
«ምን ፈለግህ?» ወይም፣ «ከእርሷ ጋር የምትነጋገረው
ለምንድነው?» ብሎ የጠየቀው ማንም አልነበረም::
28ሴትዮዋም እንስራዋን ትታ ወደ ከተማ ተመለሰች፤ ለሕዝቡም ያደረግሁትን
ሁሉ የነገረኝን ሰው ኑና እዩ፤ እርሱ ክርስቶስ ይሆን እንዴ?» አለች፤ 30እነርሱም
ከከተማ ወጥተው እርሱ ወዳለበት አመሩ::

ደቀ መዛሙርቱ ምግብ ይዘው ተመለሱ:: ኢየሱስ ከዚህች ሴት ጋር ሲነጋገር በማየታቸው በጣም ተገርመዋል:: ሆኖም፣ ማንም ምንም ያለው ነገር አልነበረም:: ካለፉት ዘጠኝ ወይም ዐሥር ወሮች ወዲህ ኢየሱስ የሚያደርገውን እንደሚያውቅ መረዳት ችለዋል:: ምንም እንኳ

---

ንግግሩን ያደረገውም እዚህ ነበር (ኢያ 24÷1):: (7) የዮሴፍ አድም በተቀበረው እዚህ ነበር (ኢያ 24÷32):: (8) ዐሥሩ ነገዶች የተከፋፈሉ ጊዜ አካባቢው ታዋቂ ነበር (1ነገ 1÷21፣25)::» በተጨማሪም ዘመናዊ የሳምራውያን ታሪክ የጌባለ ተራራ፣ ገነት ተራራው ጫፍ ላይ መሆንዋን፣ አዳም የተሠራበት አፋር የዚያ መሆኑን፣ አዳም መሠዊያ መጀመሪያ የሠራው፣ ሴትና ኖኅም፣ የታቦቱ ማረፊያ ቦታና የጥፋት ውሃ ያልነካውና በዚህም ምክንያት በሬሳዎች ያለረከሰ ይህ ቦታ ብቻ ነበር፤ አብርሃም ከመልከጼዴቅ ጋር የተገናኘውና በኋላም ይስሐቅን ለመሥዋዕት ያቀረበው እውነተኛው ቤቴል እዚያ ነበር ይላሉ (McGarvey, p. 147-148)::

[42] እግዚአብሔር ብርሃን (1ዮሐ 1÷5)፣ ፍቅር (1ዮሐ 4÷8፣16)፣ እና እሳት (ዕብ 12÷29 መሆኑም ተገልጦአል::

አንዳንድ ያልተለመዱ ነገሮችን ቢያደርግም በውሳኔው ይተማመኑ ነበር:: ወይም ደግሞ እርሱን ፊት ለፊት ለመቋቋም ድፍረት አልነበራቸው ይሆናል::

ሴትየዋ ለምን እንስራዋን ትታ እንደ ሄደች ብዙ ግምቶች ሲሰነዘሩ ኖረዋል:: አንዳንዶች ከኢየሱስ ጋር በነበራት ውይይት በጣም በመመሰጧ ነው እንስራዋን ትታ የሄደችው ይላሉ፤ ይሁን እንጂ፣ በዚያ ጊዜ ውሃ ቀድታ ስለ ነበር የጠየቃትን ውሃ ለመስጠት ስትል (ቁ 7) እንስራዋን እዚያው መሲሑ ዘንድ ትታ ሄዳም ይሆናል::

በመደነቅ እየሮጠች ወደ ሰፈር ሄደች (ከኢየሱስ ጋር የተገናኘ ሁሉ እንደሚያደርገው):: በእርሷ ባሕል ያለች፣ በተለይ ደግሞ የእርሷ ዓይነት ስም ያላት ሴት በቀላሉ ሌሎችን ማሳመን እንደማይቻላት ስለምታውቅ፣ «ያደረግሁትን ሁሉ የነገረኝን ሰው ኑና እዩ» በሚል ማራኪ አቀራረብ ነበር የተናገረችው ይህ በከፍተኛ ሁኔታ የሰዎችን ስሜት መሳብ ይችላል:: የእርሷ ዓይነት ስም ያላት ሴት ያልሆነ ነገር ተደረገ ብላ የምትናገርበት ምክንያት አይኖርም::

እስከምናውቀው ድረስ ኢየሱስ ያደረገችውን ሁለ ለሴትየዋ አልተናገረም ነበር:: ሆኖም፣ በጥቂቱም ቢሆን የአካለ መጠን ዘመንዋን በሙሉ መዳሰስ ችሏል:: ይህ ደግሞ ሙሉ በሙሉ እንደሚያውቃት እርግጠኛ እንድትሆን አድርጓታል:: ከዚያ በኋላ፣ «እርሱ ክርስቶስ እርግጠኛ እንድትሆን አድርጓታል ከዚያ በኋላ፣ «እርሱ ክርስቶስ ይሆን እንዴ?» በማለት ጠየቀች:: አጠያየቋ አሉታዊ መልስ በመጠበቅ የቀረበ ይመስላል:: ይህች ሴት እንዴት የሰውን ትኩረት እንደምትስብ በሚገባ ታውቃለች (ምናልባትም ከትዳር ልምምዷ የተማረችው ሊሆን ይችላል):: የሰፈሩ ሰዎች ግልብጥ ብለው ኢየሱስን ለማየት ወጡ:: ሆኖም ይህች ሴት ስለ ኢየሱስ የነበራት ግንዛቤ በእንዴት ዐይነት ሁኔታ እያደገ እንደ መጣ እንመልከት፣ ቁጥር 9 - «ይሁዳዊ»፣ 11 - «ጌታዬ»፣ 19 - «ነቢይ»፣ 29 ላይ ደግሞ «ክርስቶስ» አለችው::



**ዮሐ 4÷31-38**

[31]በዚህ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ፣ «ረቢ፣ እህል
ቀመስ እንጂ» አሉት:: [32]እርሱ ግን፣« እናንተ የማታውቁት፣
የምበላው ምግብ አለኝ» አላቸው::[33] ደቀ መዛሙርቱም፣
«ሰው ምግብ አምጥቶለት ይሆን እንዴ?» ተባባሉ::
[34]ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ «የእኔ ምግብ የላከኝን ፈቃድ ማድረግና
ሥራውን መፈጸም ነው፤ [33]እናንተ፣ 'ከአራት ወር በኋላ መከር ይደርሳል' ትሉ የለምን?
እነሆ፣ አዝመራው ለመከር እንደ ደረሰ ቀና ብላችሁ ማሳውን ተመልከቱ እላችኋለሁ::
[36]አጫጁ አሁንም ቢሆን እንኳ ደመወዙን የተቀበለ ነው ለዘላለም ሕይወት ይሆን ዘንድ
አዝመራን ይሰበስባል፤ ይህም ዘሪውና አጫጁ በጋራ ደስ እንዲላቸው ነው:: [37]ስለዚህ፣
አንዱ ይዘራል፤ ሌላውም ያጭዳል የተባለው ምሳሌ እውነት ነው:: [38]ያልደከማችሁበትን
እንድታጭዱ ላክኋችሁ፤ አድካሚውን ሥራ ሌሎች ሠሩ፤ እናንተም የድካማቸውን ፍሬ
ሰበሰባችሁ::»

በዚህ መሓል ደቀ መዛሙርቱ ምግብ አቀረቡለት፣ እርሱ ግን መብላት አልፈለገም:: መሲሕነቱን ለመጀመሪያ ጊዜ በግልጽ ማወጁ ካሳደረበት ደስታ የተነሣ ተፈጥሮአዊ ረሐቡ ጠፍቶ ይሆናል:: በሥጋዊ አንጻር ያስቡ የነበሩት ደቀ መዛሙርት ግን ኢየሱስን አልተረዱትም:: ስለ መንፈሳዊ ውሃ በነገራት ጉዳይ ሴትዮዋ ግራ ተጋብታ ነበር፤ እሷን የመሰሉ ሰዎች ደግሞ ስለ መንፈሳዊ ምግብ ሲነግራቸው ግራ ይገባቸዋል:: ኢየሱስ ሰለ መንፈሳዊ ምግብ ሊያስተምራቸው ጀምሮ ነበር፤ ሆኖም ጊዜ አልነበረም:: የተሰበሰበው ሕዝብ ግልብጥ ብሎ መጣ::

ወሩ ታኅሣሥ (ወይም ጥር መጀመሪያ ላይ) ነበር፤ የፀደይ መከር ደግሞ አራት ወራት ቀርቶት ነበር::[43] ኢየሱስን ግን፣

[43] A.W. Argyle, "A Note on John 4:35," *ExpT* 82 (1971): 247-248 ላይ እንደሚለው ዮሐንስ 4÷35 "a perfect iambic line" (አጭርና ረጅም የግጥም ሐረጎች የሚፈራረቁበት ግጥም) እና ምሳሌያዊ ቅኔ ነው:: ምናልባትም ኢየሱስ ካልታወቀ ግሪካዊ ምንጭ የተገኘ የተለመደ ምሳሌ በመጥቀስ መናገሩ

«አዝመራው ለመከር እንደ ደረሰ ቀና ብላችሁ ማሳውን ተመልከቱ» አለ:: ምናልባት ቀና ሲሉ የተመለከቱት ግን አረንጓዴውን መስክ በማቋረጥ መሲሕ ወደሚሆነው እየመጡ የነበሩትን ነጭ መጐናጸፊያ የለበሱ የሰማርያ ሰዎች ብቻ ሊሆን ይችላል:: በእርግጥ አዝመራው ብዙ ነበር (ማቴ 9፡37-38፤ ሉቃ 10÷2 ጋር ያነ)::

«ዘሪውና አጫጁ በጋራ ደስ ይላቸዋል» የሚለው አነጋገር ከአሞጽ 9፡13 የተወሰደ ነው:: ይህ ምንባብ የሚያመለክተው እጅግ ፍሬያማ በሚሆነውና በአስገራሚ ፍጥነት በሚገኘው አዝመራ ዘሪውና አጫጁ አብረው ስለሚሳተፉበት መሲሐዊ የደስታ ዘመን ነው::[44] «አንዱ ይዘራል፤ ሌላውም ያጭዳል»:: ኢየሱስ በግልጽ ደቀ መዛሙርቱን ለአጨዳ እየጠራ ነው፤ ግን ዘሪዎቹ እነማን ነበሩ? ምላሹ:- ሙሴ፣ ነቢያት፣ መጥምቁ ዮሐንስ፣ አየሱስ ራሱ፣ ሌላው ቀርቶ ሳምራዊቷ ሴት ጭምር የሚል ነው::

**§35ሐ ሲካር ለክርስቶስ እጅ ሰጠች (ዮሐ 4÷39-42)**

39 ሴትዮዋ፣ «ያደረግሁትን ሁሉ ነገረኝ ብላ ስለ መሰከረች ከዚያች ከተማ ብዙ ሳምራውያን በእርሱ አመኑ:: 40 ስለዚህ፣ ሳምራውያኑ ወደ እርሱ በመጡ ጊዜ አብሮአቸው እንዲቆይ አጥብቀው ለመኑት፤ እዚያም ሁለት ቀን ቈየ:: 41 ከቃሉም የተነሣ ሌሎች ብዙዎች አመኑ:: 42 ሴትዮዋንም፣ «ከእንግዲህ የምናምነው አንቺ ስለ ነገርሽን ብቻ አይደለም፤ እኛ ራሳችን ሰምተነዋል፤ ይህ ሰው በእውነት የዓለም አዳኝ እንደ ሆነ እናውቃለን» አሏት::

ይሆናል:: ምናልባትም የግሪክ ቅኔዎችን ያውቅ ስለ ነበረ ኢየሱስ ራሱ ያዘጋጀው ነበር ቢባል የሚያስኬድ ሊሆን ይችላል::

[44] አሞጽ 9÷11-12 በሐዋርያት ሥራ 15÷16-17 ላይ የክርስትና ዘመንን የሚያመለክት መሆኑ በግልጽ ተነግሮአል:: በተመሳሳይ ዐውድ ያለው አሞጽ 9÷13-14 በተለይ እዚህ ላይ ኢየሱስ ከተናገረው አንጻር ስንመለከተው በማቴጥቄጥ ላይ ስለ ነበረችው ቤተ ክርስቲያን እንደሚናገር መቁጠር ምክንያታዊ ይሆናል::



በዚህች ሴት ምስክርነት በሲካር የነበሩ ብዙዎች በኢየሱስ አመኑ:: ከእነርሱ ጋር ሁለት ተጨማሪ ቀን እንዲቆይ የግድ አሉት:: በዚህ ጊዜ ከሌላው ጊዜ ይልቅ ብዙ ሰዎች በእርሱ አመኑ::

እምነታቸው ምን ያህል የጠለቀና የበሰለ መሆኑን ባናውቅም፣ «የዓለም አዳኝ» በማለት ጠርተውታል (ማቴ 1÷21፤ ሉቃ 2፡11፤ ሐሥ 5÷31፤ 13÷23፤ ፊል 3÷20፤ ኤፌ 5፡23፤ ቲቶ 1፡4፤ 2፡13፤ 3÷6፤ 2ጢሞ 1÷10፤ 2ጴጥ 1÷1:11፤ 2÷20፤ 3፡2:18 ጋር ያነ):: በእንዲህ ያለ አጭር ወቅት ስለ ክርስቶስ በጥልቀት ማሰብ የጀመሩ ሌሎችም ሊኖሩ ይችላሉ:: ልባችሁ ከተከፈተ የክርስቶስን ማንነት በእርግጥ ለማወቅ ጊዜ አይወስድባችሁም (ማቴ 8÷5-13፤ ማር 15÷39፤ ሉቃ 1÷42፤ ዮሐ 1÷49፤ ሐሥ 16÷31-34)::

ማክጋርቬ ይህ ምንባብ ሦስት አዳጋች ግድግዳዎችን እንደሚያፈርስ ይናገራል: (1) የዘር መጠላላት፣ (2) የጾታ መናናቅ - ይህች ሴት መንፈሳዊ ትምህርትን መቀበል፣ ሌላው ቀርቶ የእርሱን ማንነትና ክብር ለሌሎች ለመመስከር እንኳ የበቃች መሆንዋን ኢየሱስ ራሱ አረጋግጦላታል፣ (3) ግብረ ገባዊ ጨዋነት:: በእርግጥም ኢየሱስ የመጣው የተናቁትንና የጠፉትን ለማዳን ነበር::